

ፍቅርና
ተስፋን
በሙዳይ

ገጽ 16



ከውትድርና
የጀመረው የሙቶ
አለቃው የስኬት ጉዞ

ገጽ 17





# አዲስ ዘመን

82ኛ ዓመት ቁጥር 238 ሚያዝያ 28 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00 **ቅዳሜ** ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!


# ያለፉ የድል ታሪኮቻችንን
## በዘመናዊ መልኩ በመድገም ለቀጣይ ትውልድ ዐሻራ መጣል ይጠበቅብናል

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- በቀደምት አባቶቻችንና እናቶቻችን የተፈጸሙ ታላላቅ ጀብድና የድል ታሪኮችን በዘመናዊ መልኩ በመድገም ለቀጣይ ትውልድ አሻራ መጣል አስፈላጊ መሆኑን የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ ተናገሩ፡፡ 82ኛው የአርበኞች የድል በዓል በአራት ኪሎ የድል ሐውልት በተለያዩ ሁነቶች በድምቀት ተከብሯል፡፡

በክብረ በዓሉ ተገኝተው ንግግር ያደረጉት የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ክብርት ሳህለወርቅ ዘውዴ እንደገለጹት፤ያለፈ ታሪክን መገንዘብ ያለንበትን ወቅት እንድንረዳና የወደፊቱንም ጊዜ ለማዘጋጀት የሚረዳ በመሆኑ ያለፉ ታላላቅ ገድላትን በስራ፣ በሀገር ወዳድነትና በፍቅር መድገም ያስፈልጋል፡፡

የሀገራችን አርበኞች አምስት ዓመት በዱር በገደል ተዋድቀው ከፍተኛ የህይወት መስዋዕትነት በመክፈል ፋሽስት ኢጣሊያንን ተዋግተው የሀገራችንን ሉዓላዊነት አስከብረዋል ያሉት ፕሬዚዳንቷ፤ በዓሉን ክብራቸውን በሚመጥን መልኩ ማክበርና እነሱ የሰሩትን ታላቅ ጀብድ ዘመኑን በሚመጥን መልኩ በስራ መድገም አስፈላጊ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ አክለውም፣ትውልዱ ዘመኑን በመዋጀት በስራ መድገም እንጂ ጀግኖች አባቶቻችንና እናቶቻችን ባገኙት ገድል ብቻ ተደላድሎ መኖር አስፈላጊ አይደለም ብለዋል፡፡

እንደ ፕሬዚዳንቷ ገለጻ፣ በድል በዓሉ ፋሽስት ጣልያን በዓድዋ የደረሰበትን ሽንፈትና እፍረት ለመበቀል ከ40 ዓመት ቆይታ በኋላ መጥቶ በብዙ ኢትዮጵያዊያን ላይ ከፍተኛ በደል ቢያደርስም ኢትዮጵያዊያን በነበራቸው

ያለፉት የድል ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

ፎቶ፡- ዳኜ አበራ



82ኛው የአርበኞች የድል በዓል በአራት ኪሎ የድል ሐውልት ስር ተከብሯል




# ፕሮጀክቶቹ
## ዘመን ተሻጋሪና የሀገርን ገጽታ የሚገነቡ በመሆናቸው ተሰንደው መቀመጣቸው ጠቃሚ ነው

**ቃልኪዳን አሳዬ**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- በለውጡ ዘመን የተሰሩት ፕሮጀክቶች ዘመን ተሻጋሪ፣ ሁሉን አካታች፣ የሀገርን ገጽታና ኢኮኖሚ በመገንባት ረገድ የሚጠቀሱ በመሆናቸው ተሰንደው መቀመጣቸው ጠቀሜታቸው የጎላ እንደሆነ ተገለጸ፡፡

በጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት የተዘጋጁ ህትመቶችንና የጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ የጽሁፍ ስራዎችን የሚዳስሰው "ቃል፤ ተግባር፤ ትውልድ

ፕሮጀክቶቹ ዘመን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## ኢንዱስትሪ ፓርኮች
### የግብርና ምርቶችን በማቀናበር ዘርፍ፡-

- ለ100 ሺ አርሶ አደሮች ዘላቂ የገበያ ትስስር ፈጥረዋል
- 3 ነጥብ 5 ቢሊዮን ብር የሚያወጡ ምርቶችን ከአርሶ አደሮች ገዝተዋል
- በዘጠኝ ወራት 4 ነጥብ 9 ቢሊዮን ብር የሚያወጣ ተኪ ምርት አምርተዋል

ገጽ 4

# "የኢትዮጵያ አየር መንገድ በአህጉር አቀፍ ደረጃ እያስመዘገበ ያለው ስኬት ለሌሎች ተቋማትም ትምህርት የሚሰጥ ነው"

-ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

<u>አዲስ አበባ</u> ፡- የኢትዮጵያ አየር መንገድ በአህጉር አቀፍ ደረጃ እያስመዘገበ ያለው ስኬት ለሌሎች ተቋማትም ትምህርት የሚሰጥ ነው ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ተናገሩ፡፡

"የኢትዮጵያ አየር... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

ፎቶ፡- አዩብ ተፈሪ








ዶክተር ጳውሎስ ካሱ

## “አካል ጉዳተኞችን በኢኮኖሚው ዘርፍ እኩል ተጠቃሚ የማድረግ ውስንነት አለ”

- የኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸው ማህበር ፕሬዚዳንት

## “ችግሩን ለመፍታት አዲስ ረቂቅ አዋጅ እየተዘጋጀ ነው”

-የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- በሀገሪቱ የሚገኙ አካል ጉዳተኞችን በኢኮኖሚው እኩል ተጠቃሚ የማድረግ ውስንነት መኖሩን የኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸው ማህበር ገለጸ:: የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በበኩሉ ችግሩን ለመፍታት አዲስ ረቂቅ አዋጅ እየተዘጋጀ ነው ብሏል::

የኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸው ማህበር ፕሬዚዳንት ዶክተር ጳውሎስ ካሱ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በኢትዮጵያ 21 ሚሊዮን የሚደርሱ አካል ጉዳተኞች እንዳሉ ጥናቶች የሚያመላክቱ ቢሆንም በኢኮኖሚው ዘርፍ እኩል ተሳታፊና ተጠቃሚ የማድረግ ውስንነት ይታያል::

አካል ጉዳተኞችን በሀገሪቱ ኢኮኖሚ እኩል ተሳታፊና ተጠቃሚ ለማድረግ አካታች የሆነ የኢኮኖሚ መመሪያና አስገዳጅ ህግ መዘጋጀት ይኖርበታል ብለዋል::

ትልቅ አቅም ኖሯቸው የተቀመጡ አካል ጉዳተኞችን የስራ እድል በመፍጠር ወደ አምራችነት ማሰማራትና የመከታተል ስራ ሊሰራ ይገባልም ሲሉ አክለዋል::

በኢትዮጵያ 17 ሚሊዮን የሚሆነው ስራ የሌለው አካል ጉዳተኛ መሆኑን የጠቀሱት ዶክተር ጳውሎስ፤ ይህም በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ የሚደርሰው ጉዳት ከፍተኛ ነው ብለዋል:: የአካል ጉዳተኞች በኢኮኖሚው ያላቸውን የተጠቃሚነት ውስንነት ለመፍታት በትኩረት ሊሰራበት ይገባል ሲሉ አሳስበዋል::

መንግስት አካል ጉዳተኞችን በኢኮኖሚው ዘርፍ ለማሳተፍና ተጠቃሚ ለማድረግ መመሪያ የማዘጋጀትና የማስፋፋት ስራ በመስራት አምራች ዜጋ መሆናቸውን በቀዳሚነት ማሳየት አለበት ሲሉም አብራርተዋል::

የሀገሪቱ ኢኮኖሚ አቅም ሊገነባ የሚችለው የአካል ጉዳተኞችን እኩል ተጠቃሚና ተሳታፊ ማድረግ ሲቻል ነው ያሉት ዶክተር ጳውሎስ፤ ያለውን የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ውስንነት ሁሉም የሚመለከተው ባለድርሻ አካል ተረባርቦ ሊፈታው እንደሚገባ አመላክተዋል::

የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የአካል ጉዳተኞች መሪ ስራ አስፈፃሚ አቶ አሳልፈው አመዲን ችግሩ እንዳለ አምነዋል:: ሆኖም አካል ጉዳተኞችን በኢኮኖሚ ተጠቃሚ ለማድረግ አዲስ ረቂቅ አዋጅ እየተዘጋጀ ነው ብለዋል::

እየተዘጋጀ ያለው የአካል ጉዳተኞች አዲሱ ረቂቅ አዋጅ በርካታ መብቶችን የያዘ ነው ያሉት አቶ አሳልፈው፤ አካል ጉዳተኞችን በኢኮኖሚ ተጠቃሚ የሚያደርግ እና የስራ እድል መፍጠር የሚያስችል ነው ብለዋል::

ለአካል ጉዳተኞች የተለየ አሰራር በመዘርጋት በመንግስትና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ተሳታፊነታቸውና ተጠቃሚነታቸው እንዲሰፋ ረቂቅ አዋጁ ትልቅ ሚና አለው ሲሉ አብራርተዋል::

በተጨማሪም ረቂቅ አዋጁ በመንግስት ጸድቆ ወደ ተግባር ሲቀየር ያለውን የአካል ጉዳተኞችን በኢኮኖሚ የተጠቃሚነት ውስንነት ይፈታል ተብሎ ይታሰባል ብለዋል::

አካል ጉዳተኞችን በኢኮኖሚውና በተለያዩ ዘርፎች ተጠቃሚ ለማድረግ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ብቻ የሚችል አይደለም፤ ሁሉም ባለድርሻ አካል የበኩሉን መወጣት አለበት ሲሉም አመላክተዋል::

# ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የስኳር አቅርቦትን ማሳደግ ላይ በትኩረት እንዲሠራ ምክር ቤቱ አሳሰበ

**ውብሸት ሰንደቁ**



አዲስ አበባ፡- የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የስኳር ፋብሪካዎች ምርታማነት፣ የፕሮጀክት አፈፃፀም እና የግብዓት አቅርቦት ላይ በትኩረት በመሥራት የስኳር አቅርቦትን ማሳደግ እንደሚገባው የኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አሳሰበ:: ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ችግሩ ውስብስብ ቢሆንም ለመፍታት እየሠራሁ ነው ብሏል::

የኢፌዴሪ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል የተከበሩ አቶ አብዱ ደባል እንደገለጹት፤ የስኳር ፋብሪካዎች ምርታማነት፣ የፕሮጀክት አፈፃፀም እና የግብዓት አቅርቦት ላይ ክፍተት አለ:: ይህን ክፍተት ለመሙላት በትኩረት መሥራት እና የስኳር አቅርቦትን ማሳደግ ይገባል::

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በሠራው ሥራ በየአካባቢው ሥራ አቁመው የነበሩ ኢንዱስትሪዎች ወደ ሥራ ገብተው ተጨባጭ ውጤት እንዲያስመዘግቡ ማስቻሉንና ይህም የሚያበረታታ መሆኑን የገለጹት የተከበሩ አቶ አብዱ፤ ሆኖም ባለፉት ዓመታት የሀገሪቱን የስኳር ፍላጎት ለማሟላት የተሄደበት ርቀት እምብዛም ነው ብለዋል::

ባለፉት ዓመታት ከአሥር በላይ ፋብሪካዎች መገንባታቸውን አንስተውም፤ የስኳር አቅርቦት ሊሟላ ግን አልቻለም ብለዋል:: ተመርቶ የሚቀርበው የስኳር ምርት በቂ ስላልሆነ በአቅርቦት እና ፍላጎት መካከል ያለው ልዩነት እየሰፋ መጥቷል ሲሉም አስረድተዋል:: በዚህ የተነሳ ስኳርን ከውጪ በማስገባት የሀገሪቱን ፍላጎት ለማሟላት ጥረት እየተደረገ ይገኛልም ሲሉ አክለዋል::

በሀገሪቱ ያሉ የስኳር ፋብሪካዎች በሙሉ አቅማቸው ወደ ማምረት ቢገቡ በሀገሪቱ ያለውን የስኳር ፍላጎት ለማሟላት እንደሚችል ግምታቸውን ያስቀመጡት አቶ አብዱ፤ “እንዲያውም ኤክስፖርት ማድረግ እና የውጭ ምንዛሬ ማግኘት ይገባን ነበር” ሲሉ አንስተዋል::

እንደ አቶ አብዱ ገለፃ፤ የስኳር ፋብሪካዎች በሙሉ አቅማቸው ወደ ስራ እንዲገቡ መደረግ አለበት:: የስኳር ኢንዱስትሪውን መሰረታዊ ማነቆዎች በፍጥነት መፈታት አለባቸው:: ኦሞ አንድ እና ኦሞ አምስትን የመሳሰሉ አሁን በጅምር ያሉ ያልተጠናቀቁ የስኳር ፋብሪካዎች በመኖራቸው ምክንያት ከፍተኛ የመንግሥት እና የሕዝብ ሀብት እየባከነ ነው:: በመሆኑም ፋብሪካዎችን በማጠናቀቅ ወደ ሥራ አስገብቶ ኢንዱስትሪው ላይ ተጨማሪ አቅም እንዲሁም የሥራ ዕድል ለመፍጠር መሠራት ይኖርበታል::

የኢንዱስትሪ ሚኒስትሩ አቶ መላኩ አለበል በሰጡት ምላሽ፤ “በስኳር ፋብሪካዎች ላይ ባወጣነው ወጪ ልክ ተጠቃሚ እየሆንን አይደለም::” ብለዋል:: ፋብሪካዎቹ በተለያየ ምክንያት ውጤታማ ሊሆኑ እንዳልቻሉም አብራርተዋል::

የዕዳ ጫና ውስጥ እንድንገባ ያደረገን የፕሮጀክት አመራራችን የነበረበት ችግር እና የአዋጭነት ጥናት ሳይጠና ወደ ውሳኔ የተገባባቸው በመሆናቸው ነው ያሉት አቶ መላኩ፤ አሁን ለነዚህ አይነት ፕሮጀክቶች “ዕዳ ከፋይ” ሆነናል ብለዋል:: በአሁኑ ጊዜ ደግሞ ፕሮጀክቶቹ ከዚያም አልፎ የመልካም አስተዳደር ጥያቄ ሆነው እየተነሱ መምጣታቸውም አሳሳቢ መሆኑን ጠቁመዋል::

በኢትዮጵያ ውስጥ የተገነቡ ስኳር ፋብሪካዎች ብዙ ዓይነት ውስብስብ ታሪክ ያላቸው ናቸው ያሉት ሚኒስትሩ፤ አንዳንዶቹ የስኳር ፋብሪካዎች ግዙፍ ሆነው ቢገነቡም ግብዓት የሚቀርብበት መንገድ ግን ትክክለኛ ያልሆነ ነው:: ለአብነትም የሸንኮራ ማምረቻቸው አናሳ ይሆንና ፋብሪካው ከአቅሙ በታች እንዲያመርት ይገደዳል ብለዋል::

አንዳንድ የስኳር ፋብሪካዎች ደግሞ ሰፊ ምርት የሸንኮራ አገዳ ምርት ማምረት የሚችሉ ሆነው ፋብሪካዎቻቸው ግን የማምረታቸው አቅም ትንሽ ይሆናል:: የሸንኮራ ምርቱ ከ25 ኪሎ ሜትር በላይ ተጓጉዞ ሊመረት ስለማይችል በዚህም ምክንያት ሸንኮራ አገዳው እንዲወገድ ይደረጋል:: ይህም የስኳር ፋብሪካዎች ውጤታማ እንዳይሆኑ አድርጓል ሲሉ ገልጸዋል::

በግብዓት እጥረት ረገድ የሚፈጠሩ ችግሮችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተባብረን ለመፍታት ጥረት እያደረግን ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ ተጀምረው ያልተጠናቀቁ ፋብሪካዎች ግን ምን ያህል አዋጭ ናቸው የሚለው ላይ አሁንም ተጨማሪ ጥናት ስለሚያስፈልግ ጥናት እየተደረገ ነው ብለዋል::

# ፍርድ ቤቱ መስከረም አበራን ጨምሮ ስድስት ግለሰቦች በተጠረጠሩበት የሽብር ወንጀል መዝገብ የ14 ቀን የምርመራ ጊዜ ፈቀደ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



አዲስ አበባ፡- የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 1ኛ ጊዜ ቀጠሮ ችሎት ፖሊስ ያቀረበውን የሽብር ወንጀል የጥርጣሬ መነሻን እና የተጠርጣሪዎችን የመከራከሪያ ነጥብ ተመልክቶ ነው ለተጨማሪ ምርመራ ለፖሊስ 14 ቀን የፈቀደው።

በሽብር ወንጀል ተጠርጥረው ከትናንት በስቲያ ከሰዓት በኋላ ፍርድ ቤት የቀረቡት ተጠርጣሪዎቹ መስከረም አበራ፣ ሳሮን ቀባው፣ ዮርዳኖስ አለሜ፣ ቢሰጥ ተረፈ፣ ዶ/ር አሰፋ አዳነ እና ታደሰ መንግስቱ ይባላሉ።

ተጠርጣሪዎቹ ህገ መንግስቱንና ህገመንግስታዊ ስርዓቱን በኃይል ለማፍረስ በማሰብ ኢ - መደበኛ አደረጃጀት በመፍጠር ፣ወጣቶችን በመመልመል፣ ለሽብር ወንጀል የሚውል ገቢ በማሰባሰብ ተግባር ተሳትፈዋል ሲል መርማሪ ፖሊስ የጥርጣሬ መነሻውን በዝርዝር ጠቅሶ ለጊዜ ቀጠሮ ችሎቱ አቅርቧል።

በዚህ የሽብር ወንጀል የመነሻ ጥርጣሬ ተጨማሪ ማስረጃ ሰብስቦ ለመቅረብ 14 ቀን እንዲሰጠው ጠይቋል።

የተጠርጣሪ ጠበቆች በበኩላቸው " ሁሉም ተጠርጣሪዎች ከዚህ በፊት በሌላ ፍርድ ቤት በሁከትና ብጥብጥ ማስነሳት ወንጀል ተጠርጥረው በጊዜ ቀጠሮ መዝገብ እየቀረቡ ባለበት ሂደት ላይ ዛሬ የሽብር ወንጀል ተብሎ መቅረባቸው ተገቢነት የለውም "ሲሉ ተከራክረዋል። የተጠርጣሪዎቹ ዋስትና መብት እንዲከበር ጠይቀዋል።

መርማሪ ፖሊስ በበኩሉ ከዚህ በፊት በተጠረጠሩበት ሁከትና ብጥብጥ አመጽ ማስነሳት ወንጀል ላይ በተደረገባቸው የማጣሪያ ምርመራ የሽብር ወንጀል መፈፀሙን የሚያመላክቱ ተጨማሪ ማስረጃዎች በመገኘታቸው ምክንያት በሽብር ወንጀል መዝገብ እንዲቀርቡ ማድረጉን ጠቅሶ መልስ ሰጥቷል።

የጊዜ ቀጠሮ መዝገቡን የተመለከተው ችሎቱ ተጨማሪ ምርመራ መደረጉ አስፈላጊ ነው በማለት ለፖሊስ የ14 ቀን ጊዜ ፈቅዷል።

ዜና

# “የግብርናውን ዘርፍ ውጤታማነት ለማስቀጠል በሳይንስና ቴክኖሎጂ መደገፍ ይገባል”

- አቶ ሽመልስ አብዲሳ
የኦሮሚያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- በግብርናው ዘርፍ የተገኘውን ውጤታማነት ለማስቀጠል በሳይንስና ቴክክኖሎጂ መደገፍ እንደሚገባ ፕሬዚዳንት ሽመልስ አብዲሳ ገለጹ። 2ኛው የኦሮሚያ ክልል ግብርና ትራንስፎርሜሽን ምክር ቤት ጉባኤ በትናንትናው ዕለት በአዲስ አበባ ተካሂዷል።

የኦሮሚያ ክልል ፕሬዚዳንት አቶ ሽመልስ አብዲሳ በጉባኤው ላይ እንደገለጹት፤እንደ አገር በተሰሩ ሥራዎች የግብርናው ዘርፍ ከነበረበት ቦታ ለማሻሻል ተችሏል። የዘርፍ ውጤታማነት ለማስቀጠል በሳይንስና ቴክኖሎጂ መደገፍ ይገባል።

እንደ አቶ ሽመልስ ገለጻ የግብርናው ዘርፍ ከፍተኛ የሆነ የቴክኖሎጂ ድጋፍ ያስፈልገዋል። በዚህም በጥናትና ምርምር፣በሳይንስና ቴክኖሎጂ በመደገፍ ባለፉት ጊዜያት ያጋጠሙ ችግሮችን መቅረፍ ይቻላል።

የአርሶ አደሩን እውቀት በማሻሻል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የበኩላቸውን መወጣት አለባቸው ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ ግብርና በእውቀት መደገፍ አለበት ብለዋል።

በተያዘውም ዓመት በዘርፉ ለተገኘው ውጤት አምስት መሠረታዊ ሥራዎች ተሰርተዋል። በዚህም የዘርፉን



ባለሙያዎች ከአርሶ አደሮች ማስተሳሰር፣ተግባራዊ ሥራዎችን ለመመዘን የተሰሩ ሥራዎችን ጨምሮ ችግሮችን ለመቅረፍ የምርምር ተቋማት ትልቅ መሆንና የተቋማት ትግበራ መሆናቸውን አስረድተዋል።

የግብርናውን ዘርፍ ከተበታተነ የአሰራር ሂደት ወደ አንድ ጠንካራ የአተገባበር አሰራር ማምጣት ይገባል ሲሉም አቶ ሽመልስ አመላክተዋል።

በምክትል ርዕሰ መስተዳድር ማዕረግ የገጠር ልማት ክላስተር ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ አብዱራህማን አብደላ በበኩላቸው፤ ምክር ቤቱ የግብርናውን ዘርፍ ወደ ተሻለ ደረጃ ለማሸጋገር የሚረዳ ነው።

እንደ አቶ አብዱራህማን ገለጻ የግብርና ዘርፍ በተለይም ባለፉት ሶስት ዓመታት መነቃቃትን አሳይቷል። ነገር ግን ከክልሉ አቅም ጋር ሲነጻጸር አሁንም የበለጠ መስራትን የሚጠይቅ ነው።

በተለይም በክልሉ የሚገኘውን ሰፊ ሀብት ወደ አንድ በማምጣት መጠቀም ይገባል። በዚህም በዘርፉ የተቀመጡትን ዘጠኝ የትኩረት አቅጣጫዎችን ለማሳካት የሚረዳ ነው ብለዋል።

በ2015/16 የምርት ዘመን ምርትና ምርታማነትን በእጥፍ መጨመር ይገባል። ለዚህም ከባለፈው ዓመት ልምድ መውሰድ ይገባል ብለዋል።

ክልሉ በሰባት የግብርና ሴክተሮች ተከፋፍሎ ዘጠኙን የትኩረት አቅጣጫዎችን ተግባራዊ ለማድረግ መሆኑን ጠቅሰው፤ በተለይም ቴክኖሎጂን በመጠቀም የግብርና ግብዓትን፣ የአረንጓዴ ልማትን ጨምሮ መካናይዜሽንና ሞዴል አርሶ አደሮችን በማሳደግ በትኩረት እየተሰራ መሆኑን አስረድተዋል።

በመድረኩ የግብርና ሚኒስትር ዶክተር ግርማ አመንቴ፣ የፌዴራልና የክልል ከፍተኛ አመራሮች እና ባለድርሻ አካላት ጨምሮ የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት አመራሮች ተሳትፈዋል።



# ከኤሌክትሪክ ኃይል ሽያጭ ከ71ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ተገኝቷል

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- ባለፉት ዘጠኝ ወራት ከኤሌክትሪክ ኃይል ሽያጭ ከ71 ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ መገኘቱን የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡ የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር የ2015 በጀት ዓመት የዘጠኝ ወራት እቅድ አፈጻጸምን ለምክር ቤቱ አቅርቧል፡፡

የውሃና ኢነርጂ ሚኒስትር ዶክተር ኢንጂነር ሀብታሙ ኢተፋ የ2015 በጀት ዓመት የዘጠኝ ወራት እቅድን አፈጻጸምን ትናንት ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ባቀረቡበት ጊዜ እንዳሉት፤ ከኤሌክትሪክ ሀይል ሽያጭ የተገኘን ገቢ በማሳደግ በአገሪቱ ያለውን የውጭ ምንዛሬ እጥረት ለመቅረፍና በዘርፉ ያለውን አገልግሎት አሰጣጥ የተሻለ ለማድረግ እየተሰራ ነው፡፡

ከኤሌክትሪክ ሽያጭ የተገኝ የውጭ ምንዛሬ ገቢን ለማሳደግ በዘጠኝ ወራት 91 ነጥብ ሦስት ሚሊዮን ዶላር ገቢ ለማግኘት ተቅዶ 71 ነጥብ አንድ ሚሊዮን ዶላር ገቢ ማግኘት ተችሏል ነው ያሉት ሚኒስትሩ፡፡ በዘጠኝ ወራት 13ሺህ 037 ጊጋ ዋት ሰዓት ለጎረቤት አገራት የኤሌክትሪክ ሀይል መጠን ለመሸጥ ታስቦ 10ሺህ 725 ጊጋ ዋት ሰዓት መሸጥ እንደተቻለም ገልጸዋል፡፡

ከዚህ ባሻገር ፍትሐዊ የኤሌክትሪክ ተደራሽነትን በማረጋገጥ በአገሪቱ ያለውን የኢነርጂ ፍላጎት የተሟላ እንዲሆን እየተሰራ እንዳለ በመግለጽ፤ ከብሄራዊ ግሪድ የኤሌክትሪክ ተጠቃሚዎች ደንበኞች ቁጥር ከነበረበት አራት ነጥብ ሶስት ሚሊዮን ወደ አምስት ነጥብ አንድ ሚሊዮን ለማድረስ በዘጠኝ ወራት 199ሺህ 420 ደንበኞችን ተጠቃሚ ማድረግ እንደተቻለ ጠቅሰዋል፡፡

በዘጠኝ ወራት 825 ደንበኞችን ብቻ “የኦፍ ግሪድ” የኤሌክትሪክ ተጠቃሚ ማድረግ እንደተቻለም ገልጸዋል፡፡

ሚኒስትሩ በገለጻቸው፤ ለዓባይ ግድብ ባለፉት ዘጠኝ ወራት በፌዴራል፣ በክልሎች፣ በከተማ አስተዳደሮች፣ እንዲሁም በውጭ አገር ያሉ ሚሲዮኖችን በመከታተልና በመደገፍ አጠቃላይ አንድ ቢሊዮን 120 ሚሊዮን ብር ለማሰባሰብ ታቅዶ አንድ ቢሊዮን 50 ሚሊዮን 821ሺህ 492 ብር መሰብሰብ ተችሏል ነው ያሉት፡፡

ግድቡን በቋሚነት አገራዊ አጀንዳ ለማድረግ መልዕክቶች በየዕለቱ ለ8100A ሰብስክራይበሮች እንዲሰራጩ ክትትል መደረጉንም አንስተዋል፡፡ በተጨማሪም በየሳምንቱ ከ46 ሚሊዮን በላይ ለሚሆኑ የሞባይል ደንበኞች በ8100A ላይ ተሳትፎ እንዲያሳድጉ የጥቅል መልዕክት እንዲተላለፍ ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር ክትትል መደረጉን ተናግረዋል፡፡

ምክር ቤቱ የሚኒስቴሩን የ2015 በጀት ዓመት የዘጠኝ ወራት እቅድን አፈጻጸም ያደመጠ ሲሆን፤ በሪፖርቱ መነሻነት በተለይ የንጹህ መጠጥ ውሃን በአገሪቷ ፍትሐዊ በሆነ መልኩ ተደራሽ ለማድረግ ጠንካራ ስራ መሠራት እንዳለበት የምክር ቤቱ እንደራሴዎች አሳስበዋል፡፡

# የሕጎች መሻሻል የውጭ ባለሀብቶች ተሳትፎ እንዲጨምር አድርጓል

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በንግድና ኢንቨስትመንት ዙሪያ ከ80 በላይ ሕጎች መሻሻላቸው የውጭ ባለሃብቶች በኢትዮጵያ ኢንቨስት የሚያደርጉባቸውን መስኮች እንዳሰፋ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን አስታወቀ።

በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን የህግ አማካሪ ዶክተር ሃብታሙ ስማቸው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ከዚህ በፊት በንግድና ኢንቨስትመንት ዘርፉ የነበሩ ሕጎች የውጪ ኢንቨስተሮች መሳተፍ የሚችሉባቸውን መስኮችን በቁጥር ለይተው ያስቀመጡ ነበሩ። ይህም በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እንዲኖር አድርጓል።

የንግድና ኢንቨስትመንት ሕጎች እንደየጊዜው ተለዋዋጭ፣ የዘመኑን ኢንቨስትመንት የሚመጥኑ ሊሆኑ ይገባል ያሉት ዶክተር ሃብታሙ፤ ለዚህም ኢትዮጵያ ካለፉት አራት ዓመታት ጀምሮ ዘርፉን ለማሳደግ የሚረዱ ከ80 በላይ ሕጎች ላይ ማሻሻያ አድርጋለች። ይህም የውጭ ባለሃብቶች በኢትዮጵያ ኢንቨስት የሚያደርጉባቸውን መስኮች አስፍቷል ብለዋል።



ፎቶ ገባቦ ገብሬ

ዶክተር ሃብታሙ ስማቸው

ህጎቹ ለረጅም ጊዜያት ጥቅም ላይ የዋሉ በመሆናቸውና ከዘመኑ ጋር የሚጣጣሙ ባለመሆናቸው እንዲሻሻሉ ተደርጓል ያሉት ዶክተር ሃብታሙ፤ ህጎቹ ለረጅም ጊዜያት ባለመሻሻላቸው የንግድና ኢንቨስትመንት ዘርፉ በሚጠበቀው ልክ እንዳያድግ አስተዋጽዖ አድርገዋል ብለዋል።

በተሻሻለው ህግ የውጭ ባለሀብቶች ሊሰማሩ የማይችሉባቸው የኢንቨስትመንት መስኮች በቁጥር ተለይተው የሚታወቁና አናሳ ናቸው። ይህም ማለት የውጭ ኢንቨስተሮች በኢንቨስትመንት ዘርፉ በስፋት መሳተፍ እንዲችሉ ያደርጋል ሲሉ ተናግረዋል።

እንደ አማካሪው ገለፃ፤ በተሻሻሉት የኢንቨስትመንት ሕጎች የውጭ ኢንቨስተሮች የማይሳተፉባቸውን የኢንቨስትመንት መስኮች በግልጽ ለይቷል። መስኮቹም ከ43 የሚበልጡ አይደሉም። ስለዚህ የውጭ ባለሃብቶቹ ከ43ቱ መስኮች ውጭ በሚገኙ ዘርፎች ላይ በፍላጎታቸው መሰማራት ይችላሉ። የውጭ ኢንቨስተሮች በ43ቱ የኢንቨስትመንት መስኮች ላይ እንዳይሳተፉ የተደረገው የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ያለውድድር በነፃነት እንዲሰሩ ለማድረግ ነው።

ከዚህም ባለፈ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ራሳቸውን ከውጭ ኢንቨስተሮች አንፃር እንዲመለከቱ ያደርጋል። ይህም የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ዘንድ ውድድር እንዲኖር በማድረግ የሀገር ኢኮኖሚ በሚፈለገው ልክ እድገት እንዲኖረው ያደርጋል ብለዋል።

ከዚህ ቀደም መንግስት ብቻ ይሰራቸዋል ተብለው የተለዩ የኢንቨስትመንት ዘርፎች እንደነበሩ በማንሳትም፤ አሁን ባለው ህግ በጥምረት የሚሰራ ኢንቨስትመንት ይኖራል እንጂ በመንግስት ብቻ ይሰራሉ የተባሉ የኢንቨስትመንት መስኮች የሉም ሲሉም ተናግረዋል።

ሌላው በተለያዩ ሴክተር መስሪያ ቤቶች ይሰጥ የነበረው ኢንቨስትመንትና የንግድ እንቅስቃሴ አገልግሎት በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን በአንድ ማዕከል አገልግሎት እንዲሰጡ ተደርጓል። ይህም አገልግሎቱ ፈጣን እንዲሆን አስችሏል ብለዋል።

እንደ አጠቃላይ የህግ ማሻሻያዎቹ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ወደ ኢትዮጵያ በስፋት እንዲመጣ፤በሀገር ውስጥ ከፍተኛ የሥራ እድል እንዲፈጠር፤ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ግኝትን እንዲኖር እና ከውጭ የሚገቡ ምርቶች በሀገር ውስጥ እንዲተኩ ያደርጋል። ከዚህም ባለፈ የቴክኖሎጂና የእውቀት ሽግግር እንዲኖር ያደርጋል ብለዋል።

ዜና



አቶ ዘመን ጁነዲን

# ኢንዱስትሪ ፓርኮች የግብርና ምርቶችን በማቀናበር ዘርፉ፡-

- ለ100 ሺ አርሶ አደሮች ዘላቂ የገበያ ትስስር ፈጥረዋል
- 3 ነጥብ 5 ቢሊዮን ብር የሚያወጡ ምርቶችን ከአርሶ አደሮች ገዝተዋል
- በዘጠኝ ወራት 4 ነጥብ 9 ቢሊዮን ብር የሚያወጣ ተኪ ምርት አምርተዋል

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- በሦስት ኢንዱስትሪ ፓርኮች የግብርና ምርቶችን በማቀናበር (በአግሮ ፕሮሰሲንግ) ዘርፍ በተሰማሩ ኩባንያዎች አማካኝነት ከ100 ሺ በላይ ለሆኑ አርሶ አደሮች ዘላቂ የገበያ ትስስር መፈጠሩን የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን አስታወቀ፡፡ በዘርፉ ብቻ ባለፉት ዘጠኝ ወራት 4 ነጥብ 9 ቢሊዮን ብር የሚያወጣ ተኪ ምርት መመረቱም ተጠቁሟል፡፡

የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን የማርኬቲንግና ኮሙዩኒኬሽን መምሪያ ኃላፊ አቶ ዘመን ጁነዲን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ኮርፖሬሽኑ ባለፉት 9 ወራት ተኪ ምርትን በማምረት ረገድ በቦሌ ለሚ፣ በደብረብርሀን እና ጅማ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ብቻ ከ100 ሺ በላይ ለሚሆኑ አርሶ አደሮች ዘላቂ የገበያ ትስስር መፍጠር ተችሏል፡፡

ኢንዱስትሪ ፓርኮቹ ከሚገኙባቸው ዩኒቨርሲቲዎችና የግብርና ምርምር ማዕከላት ጋር በመቀናጀት በተሠራው ሥራ ለአካባቢው አርሶ አደሮች ዘላቂ የገበያ ትስስር ከመፍጠር ባለፈ የምርጥ ዘር አቅርቦት፣ የክህሎት ስልጠና እና የምክር ድጋፍ አገልግሎት እንዲያገኙ በማድረግ ውጤቶች መመዝገባቸውን የጠቀሱት አቶ ዘመን፤ በቦሌ ለሚ ኢንዱስትሪ ፓርክና በደብረ ብርሃን ኢዱስትሪ ፓርክ የቢራ ብቅል በሚያመርቱ ሁለት ፋብሪካዎች የብቅል ገብስ ለሚያመርቱ 85 ሺ አርሶ አደሮች ዘላቂ የገበያ ትስስር ተፈጥሯል ብለዋል፡፡

በጅማ ኢንዱስትሪ ፓርክ የሚገኝ አቦካዶ ዘይት የሚያመርት ኩባንያም ከጅማ ዩኒቨርሲቲና በአካባቢው ከሚገኙ ግብርና ምርምር ተቋማት ጋር በመተባበር የተሻሻሉ የአቦካዶ ዝርያዎችን ለ15 ሺ አርሶ አደሮች ማቅረቡንና የገበያ ትስስር መፍጠሩንም አመልክተዋል፡፡

ባለፉት ዘጠኝ ወራት የግብርና ምርቶችን በማቀናበር የተሰማሩ ኩባንያዎች 3 ነጥብ 5 ቢሊዮን ብር የሚያወጡ ምርቶች ከአርሶ አደሮች ግብይት መፈጸማቸውንም ገልጸው፤ በአጠቃላይ ኢንዱስትሪ ፓርኮች የግብርና ምሮችን በማቀናበር ዘርፍ ብቻ 4 ነጥብ 9 ቢሊዮን ብር የሚያወጣ ተኪ ምርት በማቅረብ አገሪቱ የምታወጣውን የውጭ ምንዛሪ ማዳን መቻሉንም አስረድተዋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በባህር ዳር ኢንዱስትሪ ፓርክ በወር 60 ሺ ኩንታል የሚደርስ በቆሎ በባህርዳርና አካባቢው ከሚገኙ አርሶ አደሮች ተቀብሎ ስታርች የሚያመርት ኩባንያ ግንባታ መጀመሩን የጠቆሙት መምሪያ ኃላፊው፤ ይህም ለአካባቢው አርሶ አደሮች ትልቅ የገበያ መዳረሻ የሚፈጥር መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ኢትዮጵያ ለአግሮ ኢንዱስትሪ ምቹ ሆነ አየር ንብረትና የተፈጥሮ ሀብት የታደለች አገር መሆኗን ያስታወሱት አቶ ዘመን፤ ባለሀብቶች ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ገብተው በዘርፉ መዋዕለ ንዋያቸውን ቢያፈሱ በአጭር ጊዜ ተጠቃሚ ሆነው አገራቸውን በዘላቂነት የሚጠቅሙ መሆኑን ጨምረው ገልጸዋል፡፡

# “የኢትዮጵያ አየር መንገድ በአህጉር አቀፍ...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ የኢትዮጵያ አየር መንገድ አዲስ ያስገነባውን ምዕራፍ ሁለት ስካይ ላይት ሆቴል መርቀው ከፍተዋል፡፡

መርሃ-ግብሩ ላይ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድን ጨምሮ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ ታገሰ ጫፎ፣ ሚኒስትሮች፣ ሌሎች ከፍተኛ የመንግስት የስራ ኃላፊዎች እንዲሁም ጥሪ የተደረገላቸው ዲፕሎማቶች ታድመዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በዚሁ ወቅት እንደገለጹት፤ አየር መንገዱ ደንበኞችን ከማጓጓዝ ባሻገር ምቹ ማረፊያ ጭምር እየሆነ መምጣቱን ገልጸዋል።

አየር መንገዱ በትውልድ ቅብብሎሽ አሁን በደረሰበት እድገት ከሀገር አልፎ ለአፍሪካ ኩራት ሆኗል ነው ያሉት፡፡

ሌሎች ተቋማትም ከአየር መንገዱ ስኬት ልምድ በመውሰድ ከአገር ባሻገር በአፍሪካም ተወዳዳሪ ለመሆን መስራት እንዳለባቸው ተናግረዋል፡፡

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ ዋና ስራ አስፈጻሚ መስፍን ጣሰው በበኩላቸው፤ የምዕራፍ ሁለት ስካይ ላይት ሆቴል በአፍሪካ ከሚገኙ ሆቴሎች መካከል የሚጠቀስ ነው ብለዋል።

አየር መንገዱ በአቪዬሽን መስክ አሁን የደረሰበትን እድገት ከማስቀጠል ባሻገር አዲስ አበባን የቱሪዝም መዳረሻ ለማድረግ ጭምር ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እየሰራ ነው ብለዋል።

አየር መንገዱ ከምዕራፍ አንድ የስካይ ላይት ሆቴል በተጨማሪ ዛሬ ያስመረቀው ምዕራፍ ሁለት የስካይ ላይት ሆቴል አዲስ አበባን የቱሪዝም ማዕከል ለማድረግ የሚከናወኑ ተግባራት አካል መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

አዲስ የተገነባው ምዕራፍ ሁለት ስካይ ላይት ሆቴል በ11 ሺህ 500 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ ያረፈ ሲሆን 651 የመኝታ ክፍሎች እንዳሉትም አብራርተዋል።

በተጨማሪም ዘመናዊ የስብሰባ አዳራሾች፣ የጤና ማዕከል፣ ምግብ ቤቶችና የመዝናኛ ስፍራዎችን አካቷል፡፡

የሆቴሉ ግንባታ የተከናወነው "አቪክ" በተሰኘ የቻይና ህንጻ ተቋራጭ መሆኑም የኢዜአ ዘገባ አመላክቷል፡፡

# “ፕሮጀክቶቹ ዘመን ተሻጋሪና...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

በሚል መሪ ሐሳብ በአብርሆት ቤተመጻሕፍት እየተካሄደ የሚገኘው የመጽሐፍ ዐውደ ርዕይ ቀጥሏል፡፡

በዚሁ አውደ ርዕይ የትናንትና ውሎ ከ2010 ዓ.ም እስከ 2013 ዓ.ም ከመጋቢት እስከ መጋቢትና የተለያዩ ፕሮጀክቶች አፈፃፀምን የሚመለከቱ መፃህፍት ላይ ውይይት ተካሂዷል።

በውይይቱም የማዕድን ሚኒስትሩ ኢንጅነር ሀብታሙ ተገኝ፣ የዓባይ ግድብ ዋና ሥራ አስኪያጅ ኢንጅነር ክፍሌ ሆሮ እና የምስራቅ ሸዋ ዞን ሉሜ ወረዳ አርሶ አደር አሸናፊ አያሌው በውይይቱ ላይ በመገኘት ሀሳብ አንስተዋል።

የማዕድን ሚኒስትር ኢንጅነር ሀብታሙ ተገኝ እንደተናገሩት፤ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ኢትዮጵያ ያላትን ሀብት መጠቀም እንድትችል የቆየ እሳቤ እንዳላቸው አስታውሰው፤ በእሳቸው ተቀርጾ የተሰሩትም ሆነ እየተሰሩ ያሉት ፕሮጀክቶች ሁሉን አካታች በመሆናቸው ለትውልድ ተሰንዶ መቀመጣቸው ተገቢ ነው ብለዋል።

ኢትዮጵያ ፕሮጀክቶችን በመፈጸም ረገድ ያገኘቻቸው ስኬቶችና የገጠሟት ፈተናዎች በመጻህፍቱ መነሻነት በአግባቡ የተዳሰሱ መሆናቸውን ያነሱት ኢንጅነር ሀብታሙ፤ የተገነቡ ፕሮጀክቶች አስቀድሞ ግብን ከመተለም አንስቶ ለስኬት እውን መሆን በቁርጠኝነት መሥራትን ያስተማሩ መሆናቸውን ተናግረዋል።

ኢንጅነር ሀብታሙ ጊዜን፣ ገንዘብንና ጥራትን ታሳቢ ያደረጉ ስራዎች በተጠቀሱት ጊዜያት መጠናቀቃቸው ትክክለኛ ባለሙያዎች ለይተው በትክክለኛ ቦታ በመቀመጣቸው እንደሆነ ገልጸው፤ ችግራችን ድህነት በመሆኑ ያለንን ሀብት ተጠቅመን ድህነት ላይ በመዝመት ከእኛ ተርፈን ለዓለም መብቃት አለብን ብለዋል፡፡



አርሶ አደር አሸናፊ አያሌው



ኢንጂነር ሃብታሙ ተገኝ



ኢንጂነር ክፍሌ ሆሮ (2)

የዓባይ ግድብ ዋና ሥራ አስኪያጅ ኢንጂነር ክፍሌ ሆሮ እንደገለፁት፤ ግድቡ የተለያዩ ፈተናዎች ገጥመውት መዘግየቱን አስታውሰው፣ ከለውጡ ወዲህ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በወሰዱት ፈጣን እርምጃና ዜጎች ባደረጉት ድጋፍ ሶስት ጊዜ ውሃ ይዘን ለአራተኛ ዙር ሙሌት ተዘጋጅተናል። እንዲሁም ሁለቱ ተርባይኖች ሀይል እያመነጩ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

የውጭ ሀይሎች ፈተና ውስጥ የከተቱት የህዳሴ ግድብ ዛሬ ለደረሰበት ስኬት የደረሰው መንግስት ልዩ ትኩረት በመስጠቱ ነው ያሉት የግድቡ ዋና ስራ አስኪያጅ፤ ከለውጡ ወዲህ ፕሮጀክቱ ለአንድም ወቅት በገንዘብ እጥረት ተቋርጦ እንደማያውቅ አብራርተዋል፡፡

እንደ ኢንጅነሩ ገለፃ ግድቡ የእኛን አንድነት በማጠናከር ለሌሎች አፍሪካውያን ወንድሞቻችን ጥንካሬ እንድንሆን አድርጎናል ብለዋል።

አርሶ አደር አሸናፊ አያሌው በበኩላቸው፤ ከለውጡ ወዲህ በግብርናው ዘርፍ ለማመን የሚያስቸግሩ ተግባራት ተከናውነዋል። በኢትዮጵያ 85 በመቶ ገበሬ ቢሆንም ቀደም ባለ ጊዜ መሬቱም ሆነ ውሃ በእጃችን እያለ እንራብ ነበረ፤ ያ ታሪክ ተቀይሮ ለሌሎች መትረፍ ችለናል ብለዋል።

ይሳካል ተብሎ ያልታለመው የመስኖ ስንዴ ልማት አሁን ላይ አርሶ አደሩ ራሱን እንዲችል አስችሎታል ያሉት አርሶ አደር አሸናፊ፤ በቀደመው ወቅት በድህነት ይኖሩ እንደነበረ አስታውሰው፤ ከ400 በላይ ሰራተኞችን ቀጥረው እያሰሩ እንደሆነ ተናግረዋል።

በግላቸውም ምርቶችን ወደ ውጭ በመላክ በአቮካዶ ሽያጭ ብቻ በዓመት ከ250 ሺህ ዶላር በላይ የውጭ ምንዛሬ ለሀገራቸው እያስገኙ እንደሆነ አብራርተዋል፡፡

ሀገር በበርካታ ፈተናዎች ውስጥ ሆና ያሳካቻቸውና የከወነቻቸው ፕሮጀክቶች በአግባቡ ሊሰነዱና በቀጣይ ፕሮጀክቶች መማሪያ ሊሆኑ እንደሚገባም በውይይቱ ተመላክቷል።

የመጻሕፍት አውደ ርዕዩ ከሚያዝያ 24 እስከ ሚያዚያ 29 ቀን 2015 ዓ.ም ለስድስት ተከታታይ ቀናት የሚቆይ እንደሆነ መገለፁ ይታወሳል።

# ያስፉ የድል...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

ሀገራዊ አንድነትና የሀገር ፍቅር ስሜት ወራሪው ኃይል ዳግም የውርደት ካባ ለብሶ እንዲመለስ አድርገውታል፡፡

የድል በዓሉ አርበኞቻችን ኢትዮጵያ በቅኝ አገዛዝ እንዳትያዝ ሀገርንና ህዝብ ሳይከፋፈሉ ለአንድ ዓላማ መንቀሳቀስ መጨረሻው ድል እንደሚያጎናፅፍ ያረጋገጡበት ነው ብለዋል፡፡

የድል ታሪኩን ስናስብ ኢትዮጵያ የጦርነት ታሪክ የሚነገርባት ሀገር ሳትሆን ሊወር የመጣን ጠላት በድል የምናሸንፍበትና እድገታችንን የምናፋጥንበት ሊሆን ይገባል ሲሉም ተናግረዋል፡፡

የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማህበር ፕሬዝዳንት ልጅ ዳንኤል ጆቴ መስፍን በበኩላቸው፤ በዓሉ አባቶቻችንና እናቶቻችንን አርበኞች ባሳዩት ወደር የለሽ ተጋድሎ« እኛ ዛሬ አንገታችን ቀና አድርገን በኩራት እንድንራመድ እንዳደረጉን» ሁሉ የድል በዓሉን ስናስብ የአባቶች ተጋድሎ የሀገርን አንድነትና ሉዓላዊነት በማስጠበቅ እንዲሁም ገድላቸውን በስራና በተግባር በመድገም መሆን አለበት ብለዋል፡፡

ዛሬ ያገኘናት ሰላምና ክብር በአርበኞቻችን ደምና አጥንት የተገኘ ነው ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ አዲሱ ትውልድ ለሀገሩ ዘብ ቆሞ ሉዓላዊነቷን ከማስከበር ባሻገር የኢትዮጵያን ሁለንተናዊ እድገት በሚያፋጥኑ ጉዳዮች ላይ መሰለፍ እንዳለበት አመላክተዋል፡፡

ፕሬዚዳንቱ አክለውም፣ቀደምት አርበኞች ከሰሩት ታላቅ ጀብድና ተጋድሎ ባሻገር በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ታላቅ የዲፕሎማሲ ስራን በመስራት ጉልህ ውጤት አስመዝግበዋል፡፡

የድል በዓሉን ስናከብር የአባቶቻችን ክብር በሚመጥን ክብር መሆን አለበት ያሉት ልጅ ዳንዔል፤ በቀጣይም እስከ ወረዳ ድረስ ወርዶ በአደባባይ እንዲከበር ጥረት እያደረግን ነው ብለዋል፡፡

የሀገር መከላከያ ሰራዊት ተወካይ ሜጀር ጀነራል እንዳልካቸው ወልደኪዳን በበኩላቸው በዕለቱ ባደረጉት ንግግር እንደገለጹት፤ በነበረው የአምስት ዓመት ጦርነት አርበኞቻችን ባሳዩት ወደር የለሽ ተጋድሎ የጣልያን ጦር ድል ማድረግ ይቅርና ተረጋግቶ ፍላጎቱን ለማሳካት የኢትዮጵያ ምድር እንደእሳት የሚፋጅ ነበልባል ሆኖበታል፡፡

ትናንት ጀግኖች አባቶቻችንን ያሳዩት የአብሮነትና የጽናት አብነት ዛሬም ትውልዱ ሊደግመው እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡

«እኛ ኢትዮጵያዊያን ትልቁ እሴታችን በሀገራችን አንድነትና ሉዓላዊነት ላይ የማንደራደር ጀግና ህዝቦች ነን» ያሉት ሜጀር ጀነራል እንዳልካቸው፤የሀገር መከላከያ ሰራዊቱም ይህንኑ እሴት ተላብሶ የሀገር ሉዓላዊነትን ለማስከበር በትጋት እየሰራ ይገኛል ብለዋል፡፡

በክብረ በዓሉ ላይ የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ክብርት ወይዘሮ ሳሃለወርቅ ዘውዴን ጨምሮ ጥሪ የተደረገላቸው የክብር እንግዶች የተገኙ ሲሆን ከንጋቱ 12 ሰዓትም ለበዓሉ ክብር 21 ጊዜ መድፍ ተተኩሷል፡፡

በዓሉ በፖሊስና በመከላከያ ማርሽ ባንድ ጥዑመ ዜማዎች፣ የአባቶችን ተጋድሎና ጀብድ በሚያስታውሱ ቀረርቶ፣ ፉከራና ሽለላዎች እንዲሁም በተለያዩ ባህላዊ ጭፈራዎች ተከብሯል፡፡

የዘንድሮው የአርበኞች የድል በዓል “ለአብሮነት ለጽናትና ለድል” በሚል መሪ ሃሳብ ለ82ኛ ጊዜ የተከበረ ነው፡፡

# አገልግል

## የቅዳሜ መጽሔት

ለኮንስትራክሽን ዘርፍ እድገት ከፍተኛ ሚና እንደሚኖረው የታመነበት ‹‹ቢግ ፋይፍ›› ኤግዚቢሽን

ገጽ 14



‹‹በየክልሉ ያሉ ልዩ ኃይሎችን ወደ ተለያዩ የጸጥታ መዋቅር መልሶ የማደራጀቱ እንቅስቃሴ ተገቢ ነው››

**ሌፍተናንት ዮሴፍ ሽጋው**
**በቀድሞ የኢትዮጵያ ባህር ኃይል ረዳት ትምህርት መኮንን**

ገጽ 6



ፍቅርና ተስፋን በሙዳይ

ገጽ 16

ባህል፣ ኪነ ጥበብ እና ቱሪዝም ቢሮ
አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህል፣ኪነጥበብ እና ቱሪዝም ቢሮ ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

**አፍሪካዊቷ መልህቅ**

# በሆቴሎች አዋኪና መጤ ባህሎችን ለመዋጋት

**ኃይለማርያም ወንድሙ**

የአዲስ አበባ ባህል ኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ባለፈው ሳምንት በአዲስ አበባ መጤ ባህሎችና አዋኪ ድርጊቶች አስመልክቶ ከምግብና መጠጥ ቤት ኃላፊዎችና ተወካዮች ጋር ፍላሚንጎ በሚገኘው ቢሮ ውይይት መድረክ አካሂዶ ነበር ። የቢሮው ኃላፊ ዶክተር ሒሩት ካሳው እንደተናገሩት፤ ለሁሉም የአዲስ አበባ ነዋሪ የሆቴልና ቱሪዝም ድርጅቶች በአጠቃላይ የቱሪዝም ዘርፍ የሙያ ብቃት ማሻሻያ እንደሚሰጥ ጠቁመዋል። ይህም በሆቴል ዘርፍ የተሰጣቸውን ብቃት ይዘው የአገሪቱን ባህልና ዕሴት ጠብቀው እንዲሠሩ ያደርጋል።

ዶክተር ሒሩት አክለውም፤ የመድረኩ ዋና ዓላማ በሆቴል ዘርፍ ተመርቀው ተገቢውን ብቃት፤ የአገሪቱን ባህልና ዕሴት ጠብቀው እንዲሠሩ ማስቻል። ከአገሪቱ ባህልና ዕሴት ያፈነገጡ ሰዎችን ደግሞ በደንብ አስከባሪዎች በኩል ይቀጣል። አገልግሎት መስጠት ሲባል ‹‹እንኳን ደህና መጣችሁ በሚል መልካም ገፅታቸውን ለቱሪስት ማሳየት። መልካም ቀረቤታቸውን መልካም አቀባበል ለእንግዶች ማሳየት፤ መልካም ፈገግታ መልካም ገፅታ ለቱሪስቶች ማሳየት። ሲሄዱም በደህና መሸኘት ይጠበቅባቸዋል። ›› ብለዋል።

ሆቴሎች አንድ፤ ሁለት፣ እስከ አምስት እና ከዛ በላይ ኮከብ የሚሰጠው በዓለም አቀፍ ስታንዳርድ መሠረት ነው። ለኢትዮጵያ ተብሎ ለብቻው የሆቴል ደረጃ የለም። የውጭ አገር ዜጋ ከሆነ ደግሞ ዓለም አቀፍ ደህንነት አዲስ አበባ ደግሞ በእኛ ስታንዳርድ ባህልዋን ዕሴቱዋን መጠበቅ እንዳለባቸው ጠቅሰዋል።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሶሺዮሎጂ ክፍል አስተማሪና ተመራማሪ ኢዛና ዓምደ ወርቅ ‹‹በኢትዮጵያ ውስጥ ዋና ዋና የሴቶች የቅጥር ሥራ›› የመስተንግዶ ዘርፍ ከአፕን ሶሻይቲ ፋውንዴሽን ጋር በመተባበር ያጠኑትን ጥናት አቅርበዋል። ጥናቱ በጥናቱ ዳራው ሰፋ ይላል የሚሉት ጥናታዊ ጽሑፍ አቅራቢው፤ ቀጥታ ከመስተንግዶ ጋር የተገናኙትን አንድ ሦስት ርዕሰ ጉዳዮች በጥናቱ አይተናል ይላሉ። ከሠራተኛ አሠሪ የሥራ ሁኔታ ጋር መሠረታዊ ግንኙነት ይኑራቸው እንጂ ለአገልግሎቱ ተፅዕኖ እንዳላቸው ጠቅሰዋል። ስራው አገልግሎት ፈልጎ የሚመጣ ማንኛውም ሰው ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል። በጥናቱ ግኝት መሰረት ስራው በሚፈለገው ደረጃ አለመሆኑን ጠቁመዋል። በተለይ ሆቴሎች የአገር ውስጥም የውጭም ሰዎች የሚስተናገዱባቸው በመሆኑ ስራው ትኩረት እንደሚፈልግ ተናግረዋል።

በፋብሪካዎች የሚቀጠሩት ሰዎች እንዳሉ ሆነው አገልግሎት ዘርፉ ቀላል የማይባል ሰው እየቀጠረ ነው። ስለዚህ በአገሪቷ ምጣኔ ሀብት ከሚያበረክተው ድርሻ አንፃር፤ በተለይ የሴቶች ድርሻ ስንመለከት እጅግ በጣም ብዙ ቁጥር ያላቸው ሴቶች አገልግሎት ዘርፍ ውስጥ አሉ። አዲስ አበባ ከተማችንን ስንመለከት ደግሞ የከተማው የኢኮኖሚ አገልግሎት ከፍተኛ ድርሻውን ይይዛል። ስለዚህ በጣም ማዕከላዊ ወሳኝ የሆነ ዘርፍ ላይ ያለው።

አገልግሎት ዘርፉ በኢትዮጵያውያን አጠቃላይ የሥራ ዕድገት ስምንት ነጥብ ሶስት በመቶ የሚሆነው የማኅበረሰብ ክፍል ያካትታል። ይሁን እንጂ በሆቴል ደረጃ የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት መኖሩ በሥራ ላይ ያሉትም ቢሆኑ የሚያገኙት ክፍያና ጥቅማ ጥቅም አነስተኛ መሆኑን አቶ ኢዛና በጥናታዊ ጽሑፋቸው ጠቁመዋል።

እንደ አቶ ኢዛና ማብራሪያ፤ ጥናቱ በአዲስ አበባ በአራዳ፣ በየካና በቂርቆስ ክፍለከተሞች በሚገኙ ካፌዎችና ሬስቶራንቶች ላይ የተሠራ ነው። ከ270 ያህል የመስተንግዶ ሠራተኞች መረጃ የተሰበሰበ ሲሆን በተጨማሪ የካፌና የሬስቶራንት አስተዳዳሪዎችና ተቆጣጣሪዎች በቀጥታ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤት ኃላፊዎች እንዲሁም በሌሎች የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች ተካተውበታል። መስተንግዶ ሠራተኞች አብዛኞቹ ወጣት ሴቶች ናቸው። 80 በመቶ ያህሉ እስከ 30 ዕድሜ ክልል ውስጥ ናቸው። 13 በመቶ ያህሉ ከ30 ዓመት በላይ ያሉ ናቸው። ተቀጣሪዎቹ አብዛኞቹ ወደ ከተማ ቅጥር ፍለጋ የሚመጡ የገጠር ሴቶች ናቸው። 16 በመቶ ያህሉ ብቻ በአዲስ አበባ የሚኖሩ ናቸው። 84 በመቶ ከአዲስ አበባ ውጭ አካባቢ የተቀጠሩ ናቸው።

የሥራ ልምድ በአማካይ አራት ዓመት የሥራ ልምድ ያላቸው 29 በመቶ ያህል ሲሆኑ ከ2 እስከ 3 ዓመት የሥራ ልምድ ያላቸው እና በዘርፉ ከፍተኛ የሆነ የሠራተኛ መቀያየር እንደሚታይም ጠቁመዋል። ጥናቱ በሚሠራበት ወቅት ከግማሽ በላይ የሚሆኑ በዛ አገልግሎት ተቀጥረው በሚሠሩበት ካፌ ወይም ሬስቶራንት ውስጥ አንድ ዓመት ወይም ከዚያ በታች ያገለገሉ ናቸው። በባለቤቶች፣ በአሠሪዎችና በማናጀሮች ያለባቸው ተፅዕኖ ደግሞ፤ አዲስ ሠራተኛ በየጊዜው እየገባ በየጊዜው እየለቀቀ ይሄድበታል።

የከተማው አስተዳደር ባህል ኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ከደንብ ማስከበር ባለሥልጣን ጋር በመተባበር ይሠራል ያሉት የባለሥልጣኑ የቁጥጥርና ርምጃ አወሳሰድ ዳይሬክተር አቶ ኢዮብ ከበደ ናቸው። በያዝነው በጀት ዓመት ዘጠኝ ወራት በተደረጉ የቁጥጥር ሥራዎች አዋኪ ድጊቶችን በፈጸሙ ሁለት ሺህ 662 ንግድ ቤቶች (ሆቴሎች መጠጥ ቤቶች) ላይ ርምጃ ተወስዷል።

በአዋኪ ድርጊቶች ላይ የተሳተፉና ርምጃ የተወሰደባቸው ንግድ ቤቶች በትምህርት ቤቶች 200 ሜትር ዙሪያ ውስጥ ሺሻ በማስጨስ፣ ጫት በማስቃም እና የሌሊት ጭፈራ ቤቶችን በመክፈት አካባቢውን ሲያውኩ እንደነበር አቶ ኢዮብ ጠቁመዋል። በትምህርት ቤቶች አካባቢ ሺሻና ጫት ቤት በመክፈት እንዲሁም ሌሊት ጭፈራ ቤቶችን በመክፈት አዋኪ ድርጊት የፈጸሙ እያንዳንዳቸው 10 ሺ ብር እንደተቀጡ፤ በተጨማሪም ጫት ቤት የከፈቱ ደግሞ 5ሺህ ብር ቅጣት ተላልፎባቸዋል። ባለፈው በጀት ዓመት በአጠቃላይ አዋኪ ድርጊቶችን በፈጸሙ ሶስት ሺህ 476 ቤቶች ላይ ርምጃ ተወስዶ እንደነበርም አቶ ኢዮብ ባቀረቡት ጽሑፍ አስታውሰዋል።

ባለሥልጣኑ ከተለያዩ ባለድርሻ ተቋማት ጋር በመቀናጀት ከግንዛቤ ሥራዎች ጐን ለጐን በአዋጅ ቁጥር 74/2014 እና ደንብ ቁጥር 150/2015 መሠረት ነው ጥብቅ ርምጃ የሚጥሱ የቁጥጥር እና የመከልከል ሥራዎች የሚያከናውን ነው።

# የዘመን እንግዳ

# ‹‹በየክልሉ ያሉ ልዩ ኃይሎችን ወደ ተለያዩ የጸጥታ መዋቅር መልሶ የማደራጀቱ እንቅስቃሴ ተገቢ ነው››

**- ሌፍተናንት ዮሴፍ ሸጋው**

**በቀድሞ የኢትዮጵያ ባህር ኃይል ረዳት ትምህርት መኮንን**




አስመረት ብስራት

የቀድሞው የኢትዮጵያ ባህር ኃይል በንጉሱ ዘመን በ1948 ዓ.ም ሲመሰረት ከሶስቱ የኢትዮጵያ ጦር ሰራዊት አንዱ ሆኖ ሙሉ በሙሉ ራሱን የቻለ አገልግሎት ለመስጠት የተቋቋመ ነው፤ ዋነኛ ተልዕኮውም የቀይ ባህርን የባህር ዳርቻ ለመጠበቅ ነበር፡፡ በንጉሡ ነገስሥቱ ዘመን የተቋቋመው የኢትዮጵያ ባህር ኃይል ውስጥ በመግባት በወቅቱ ከነበሩ ምርጥ የዓለማችን የባህር ኃይል አባላት ጋር ተወዳዳሪና ብቁ ለመሆን የሚያስችላቸውን ስልጠናም ወስደዋል - የዛሬው የዘመን እንግዳችን።

ለዓመታት የተመሰረተበትን ዓላማ በብቃት ሲወጣ የነበረው ስመጥር የኢትዮጵያ ባህር ኃይል 1983 ዓ.ም በነበረው ለውጥና ኤርትራ ራሷን ችላ ሉዓላዊ አገር ስትሆን የባህር ኃይሉ በዛው ከሰመ፡፡ በወቅቱ ሌፍተናንት ዮሴፍ ሸጋው በቀድሞ የኢትዮጵያ ባህር ኃይል ረዳት ትምህርት መኮንን የነበሩ። እኚህ ሰውም ከባህር ኃይሉ ጋር የነበራቸው ውል የተቋረጠው እዚህ ላይ ነው።

ሌፍተናንት ዮሴፍ ተወልደው ያደጉት በአዲስ አበባ ልደታ አካባቢ ነበር። ሌፍተናንት በወቅቱ በነበረው የልጆች አስተዳደግ ደንብ ልጆች ጎረቤቱም የቤቱም ማህበረሰብ በጋራ ሆኖ በምግባር ስላሳደጋቸው ደስተኛ መሆናቸውን ይናገራሉ። ሌፍተናንት አንደኛ ደረጃ በተስፋ ኮከብ ትምህርት ቤት፤ ሁለተኛ ደረጃን በአዲስ ከተማ ትምህርት ቤት እየተማሩ ሳለ ነበር የባህር ኃይል የሚያሰለጥናቸው ወጣት የባህር ኃይል ወታደሮች እንደሚፈልግ የሰሙት።

ቀድሞ የባህር ኃይል አባል የነበረ ጓደኛ የነበራቸው ሌፍተናንቱ፣ በወቅቱ የመገናኛ ዘዴ በነበረው በፖስታ ቤት በኩል የተለያዩ ፎቶግራፎች ይልክላቸው ስለነበር ቀድሞ ልባቸው ውስጥ ተጠንስሶ የነበረው የባህር ኃይል አባል የመሆን ፍላጎት ለማስቀጠል ሄደው ይመዘገባሉ። በ1967 ዓ.ም አብዮት በተቀጣጠለበት ወቅት ወደ ባህር ኃይል የገቡት እኚህ ሰው ወደውና ፈቅደው በገቡበት የባህር ኃይል ለዓመታት ሲያገለግሉ ቆዩ።

በ1948 ዓ.ም በንጉሱ ጊዜ አንድ ብሎ የጀመረው ባህር ኃይል በ1983 ዓ.ም ሲፈርስ ሌፍተናንት ዮሴፍ አብረው እንደነበሩ ይናገራሉ። ሌፍተናንቱ ለአስራ ሰባት ዓመታት ያገለገሉበት የባህር ኃይል አባላትም በውጭ አገራት የተለያዩ መርከቦች ላይ ተበትነው ይሰሩ ጀመር። እኚህ ሰው ከረጅሙ የህይወት ልምዳቸው ያካፈሉንን በዚህ መልኩ አቅርበነዋል፤ መልካም ንባብ።

**አዲስ ዘመን፡- የቀድሞ የባህር ኃይል አባላት ማህበር ፕሬዚዳንት እንደመሆንዎ የቀደመውን የሰራዊት ሁኔታ እንዴት እንደነበር ቢያብራሩልኝ?**

**ሌፍተናንት ዮሴፍ፡-** በወቅቱ የጦር ኃይል ተብሎ የሚጠራው የአንዲት አገር ሉአላዊነት የሚያስጠበቅ፣ አገር በነፃነት እንድትሄድ ዳር ድንበሯን አስጠብቆ የሚያቆይ አካል ጦር ኃይል ይባላል። የባህር ኃይል ደግሞ በጦር ኃይል ውስጥ ካሉ የተለያዩ ክፍሎች አንዱ ነው። አንድ አገር የአየር ክልል እንዳላት ሁሉ፤ የባህር ክልል ይኖራታል፤ የየብስ ክልል ይኖራታል። ይህንን ቦታ ደግሞ የሚያስጠብቅ ኃይል አሰልጥና ትገነባለች።

በሰዓቱ በቀይ ባህር ላይ ኢትዮጵያ የነበራትን ከአንድ ሺ ኪሎ ሜትር በላይ ቦታ የሚያስጠብቅላትን ኃይል ባህር ኃይል ብላ አደራጅታ ነበር። በምስራቅ አፍሪካ ያለውን በርካታ ትርምስ የሚቆጣጠር አገሪቱ በባህር በኩል ከሚመጣባት ችግር የሚከላከል እንዲሁም ሙሉ የባህሩን ክልል ሰላም የሚያስጠብቅ የጦር ሰራዊት አካል የባህር ኃይል ይባላል።

**አዲስ ዘመን፡- በአሁን ወቅት ኢትዮጵያ ባህር ኃይል ለምን ያስፈልጋታል?**

**ሌፍተናንት ዮሴፍ፡-** ኢትዮጵያ አሁን የባህር በር ባይኖራትም የባህር ኃይል ለአንዲት አገር ወሳኝ ጉዳይ ነው። የባህር በር ሳይኖራቸው የባህር ኃይላቸውን ያደራጁ አገሮችን ለመጥቀስ ያህል ፓራጓይ፣ አዘርባጃን እና ቦሊቪያ እንደ ኢትዮጵያ የባህር በር የሌላቸው አገራት ናቸው:: ነገር ግን በቂ የባህር ኃይል አላቸው:: አሁን ባለው ሁኔታ ዘጠና ከመቶ በላይ የሚሆነው የኢትዮጵያ ገቢና ወጪ ንግድ የሚሳለጠው በውሃ ላይ በሚደረግ ጉዞ ነው:: በተለይም እ.ኤ.አ ከ2008 እስከ 2010 በምስራቅ አፍሪካ የነበረውን የባህር ላይ ውንብድና አስቸጋሪነት የባህር ኃይል መኖሩ አስፈላጊ ነው ማለት ነው:: እንደዚህ ዓይነት የአገራትን ጥቅም የሚጎዱ ውንብድናዎችን ለመከላከል የባህር ኃይል ወሳኝ ነው:: ምክንያቱም አሁን ባለው ዓለማቀፍ ሁኔታ በአንድ ቀጣና የሚፈጠር ችግር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ አለማቀፋዊ ችግር ይሆናል::

በሌላ ረገድ ኢትዮጵያ ያሏትን የንግድ መርከቦችና ለአገር ያላቸውን ፋይዳ ማየት ነው:: የአስራ አንድ የንግድ መርከቦች ባለቤት የሆነችው ኢትዮጵያ ባንዲራዋን እያውለበለቡ ከአህጉር አህጉር የሚዘዋወሩት መርከቦቿ ደህንነት ተጠብቆ በሰላማዊ ሁኔታ ስራቸውን ለማከናወን አስተማማኝ ጥበቃ ሊደረግላቸው ይገባል፤ ለዚህም በዘርፉ የሰለጠነ የባህር ኃይል መኖር ያስፈልጋል::

**‹‹መከላከያ ሰራዊት ሲቋቋም ለመመልመያነት የራሱ የሆነ መስፈርቶች ቢኖሩትም ቀለም፣ ዘርና ብሄርን ሳይቆጥር የተዋቀረ፣ አገሪቱ ውስጥ ያለውን ኅብረ ብሄራዊነት በሚያስጠብቅ መልኩ የተውጣጣ እንዲሁም ከምንም ነገር በፊት ኢትዮጵያን ሊያስቀድም የሚችል ሰራዊት መሆን ይገባዋል››**

**አዲስ ዘመን፡- ቀደም ሲል ኢትዮጵያ የነበራት ሰራዊት እንዴት ይገለጻል?**

**ሌፍተናንት ዮሴፍ፡-** በየጊዜው የተለያዩ ስያሜዎች የሚሰጡት የጦር ኃይል፣ የጦር ሰራዊት፣ መከላከያ ሰራዊት ሲባል የሚቋቋምበት ዓላማ አለው። አንድ አገር ህልውናዋን አስጠብቃ እንድትቀጥል መከላከያ ኃይልን መገንባት ግዴታዋ ነው። ይህ መከላከል የሚለው ቃል ለአንድ አገር በተፈጥሮ የተሰጣትን ሀብት ለመጠበቅ እንጂ ሌሎችን ሄዶ መጉዳትን ዓላማው አድርጎ የሚንቀሳቀስ አይደለም። ለመከላከል ደግሞ ጥንካሬ ያስፈልጋል፤ ያንን ጥንካሬ ለማምጣት በስልጠና የታገዘ ሙሉ ሎጀስቲክ ወሳኝ ነው:: እንዲሁም የተሟላለት እና ለአገር ደህንነት ዘብ ለመቆም የሚችል ብሎም ለራሱ ደህንነቱ የተጠበቀ ሰራዊት እንዲኖር ያስፈልጋል።

እንኳን በአንድ አገር በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ከጉዳት የሚከላከል አካል ያስፈልጋል። በአንድ ቤተሰብ ውስጥ አባት ካለ አባት ቤተሰቡን ይጠብቃል። ኢትዮጵያም በዓለም ውስጥ ያለች አንድ አገር እንደመሆኗ የተሰጣትን ክልል ዳር ድንበሯን የማስጠበቅ ግዴታ አለባት። ያንን ለማስጠበቅ ደግሞ መከላካያ ሰራዊት ያስፈልጋል።

ይህ መከላከያ ሰራዊት ሲቋቋም የራሱ የሆነ መስፈርቶች ቢኖሩትም ቀለምና ዘር ሳይቆጥር የተዋቀረ፣ አገሪቱ ውስጥ ያለውን ህብረ ብሄራዊነት በሚያስጠብቅ መልኩ የተውጣጣ እንዲሁም ከምንም ነገር በፊት ኢትዮጵያን ሊያስቀድም የሚችል ሰራዊት መሆን ይገባዋል። ሰራዊት ሲቋቋም ዓላማው አንድና አንድ ነው፤ የኢትዮጵያን ነፃነት ማስቀጠል፣ ዳር ድንበራን ማስጠበቅ እና ያቺን አገር በዓለም አቀፍ መድረክ ላይ በምትታወቅበት ነፃነት እንድትቀጥል ማድረግ ነው።

መከላከያ ሰራዊት ማለት እንግዲህ ከላይ እንዳስቀመጥነው ሲሆን፣ ይህ ሰራዊት ሴት ወንድ ሳይባል፣ ኃይማኖት ሳይለይ ብሎም ዘር ቀለም ሳይጠይቅ አንድ አገርን ብቻ የያዘ አገር ወዳድ ሰራዊት ነበር። ይህ ሰራዊት ከንጉሱ ጊዜ ጀምሮ ሲገነባ መስፈርቱ ኢትዮጵያዊነት ነው የነበረው። ይህ ሰራዊት ዓላማውም አገር መጠበቅ ነው ካልን በየመንግስታቱ ለውጥ የሚፈርስ ወይም ፈርሶ የሚገነባ ወይም እንደተፈለገ አውጥቶ ሜዳ ላይ የሚጣል ሰራዊት አይደለም ማለት ነው። አገር ሁልጊዜ ትቀጥላለች። ነገስታት ይመጣሉ፤ ይሄዳሉ፤ ስርአት ይለዋወጣል፤ አገር ግን ስለምትቀጥል መሪዎች በተቀያየሩ ቁጥር እያፈረሱ የሚገነቡት ሰራዊት ሊኖር አይገባም።

ለምሳሌ የባህር ኃይልን ስንመለከት ለ35 ዓመታት የተገነባ ኃይል፣ ስንትና ስንት ሀብት የፈሰሰበት ኃይል የደርግ ሰራዊት ተብሎ በአንድ ሌሊት ማፍረስ ምን አይነት እብደት ነው? ያሰኛል። ስለዚህ ሰራዊት ስርአትን እየተከተለ እንዲፈርስ ወይም እንዲገነባ መፈቀድ የለበትም።

**አዲስ ዘመን፡- ቀደም ሲል ሰራዊት ሲገነባ የነበረውን መስፈርቶች ቢያብራሩልን?**

**ሌፍተናንት ዮሴፍ፡-** ማን ያርዳ የቀበረ፤ ማን ይናገር የነበረ ነውና ነገሩ በቀደመ ጊዜ የነበረውን ለመናገር ከሰራዊቱ አባላት የበለጠ እማኝ አይገኝም። እኔ አሁን የስልሳ አምስት ዓመት እድሜ ባለፀጋ ነኝ፤ በእኔ እድሜ ባህር ኃይል ስገባ የነበረው መስፈርት በትምህርት ከአስረኛ ክፍል በላይ፤ ሙሉ ጤንነት ያለው፤ ኢትዮጵያዊ የሆነ፤ እድሜና አቋም ኪሎን የያዘ ብቻ ነው። ቋንቋና ብሄር ለውትድርና መስፈርት ሆኖ አያውቅም ነበር።

**አዲስ ዘመን፡- የአንድ አገር መለያ የሆነ ሰራዊት እንዲኖር ከቀደመው ልምድ ተነስተው ምን መሰራት አለበት ይላሉ?**

**ሌፍተናንት ዮሴፍ፡-** ከላይ እንዳልነው አንዲት አገር በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚታወቅ ግዛት ያላት፣ በውስጡ በርካታ ሀብቶችን ብሎም የተፈጥሮ ሀብቶችን የያዘች፣ የበርካታ ሰዎች መኖሪያ እንደመሆኗ ይህንን ያላትን ነገር በሙሉ ማስጠበቅ ሉአላዊነት እንለዋለን:: ይህን ሉአላዊነት ለማስጠበቅ ደግሞ የሆነ ኃላፊነት ሊሰጠው የሚገባ ኃይል አለ፤ ይህ ኃይል የመካላከያ ኃይል ይባላል።

ሁሉም አገር የራሱ የመከላከያ ኃይል አለው። በተለያዩ ጊዜያት አገር ውስጥ የሚከሰቱ፣ አገር እንደ አገር እንዳትቀጥል የሚያደርጋት እንደ ስርአት አልበኝነት

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

## የዘመን እንግዳ

# ‹‹በየክልሉ ያሉ ልዩ ኃይሎችን...

ከገጽ 6 የዞረ

ያሉ ነገሮችን ለመከላከል የሚያስችል ሰራዊት አንድ አገር አሰልጥና ማስቀመጥ ይኖርባታል። አንዲት አገር አገር ስትባል የራሷ ስርአትና መመሪያ ያላት ናት። ለአገር የሚያስፈልጋት ለዛ ስርዓት ተገዥ የሆነ በመመሪያ የሚመራ ኃይል ነው። ከአገሪቱ ጦር ኃይል በተጨማሪ የውስጥ ስርአትን የሚያስከብር የፖሊስ ሰራዊት ደግሞ ለብቻው ሰልጥኖ ይቀመጣል።

ለመከላከያ ሰራዊት ዋንኛው መስፈርት ኢትዮጵያዊነት ነው። ኢትዮጵያዊ ማንነት ከፊት ሲቀድም ነው። አንዲት አገር ለሁሉም ዜጎቿ እኩል አገልግሎት የሚሰጥ እንጂ በጎጥ ተከፋፍሎ የሚጠብቃት የጦር ኃይል ሊኖራት አይገባም። መከፋፈሉን ወደ ጎን በመተው የአገርን ሉአላዊነት የሚያስከብር ሰራዊት መመስረት ይገባል።

**አዲስ ዘመን፡- አሁን በየክልሉ ያሉ ልዩ ኃይሎችን ወደ መከላከያ ሰራዊት በማስገባት መልሶ የማደራጀት እንቅስቃሴ እየተደረገ ነው፤ እዚህ ላይ ያልዎን ሀሳብ ቢገልፁልን?**

**ሌፍተናንት ዮሴፍ፡-** ሁልጊዜ አንድ ነገር ሲታሰብ መጀመሪያ መነሻን መመልከት ያስፈልጋል። መነሻውን የማያውቅ የት እንደሚደርስ አያወቅምና። አዲስ ነገር ሲታሰብ አባቶቻችን በምን መልኩ ይህችን አገር ይመሯት እንደነበር፤ እኛንስ ሲያስረክቡን በምን መልኩ እንደነበር ማጤን ያስፈልጋል። የትውልድ ቅብብሎሽን በተስተካከለ ቅኝት ሄዶ የነበረ መሆኑን ማየት ተገቢ ነው።

አንድም ጊዜ በቅኝ ግዛት ያልተገዛች አገር መሆኗንና ለነፃነት ዋጋ የከፈሉ አባቶች የሰሩትን ገድል መመልከት ተገቢ ነው። የአገርን ዳር ድንበር ለማስከበር የብሔር ስም አልተጠቀሰም ነበር። አገር እስከዚህ ጊዜ ድረስ ሉአላዊነቷን ጠብቃ እንድትኖር ያቆዩን አባቶቻችን አፅምም ይወጋናል።

አሁን በየክልሉ ያሉ ልዩ ኃይሎችን ወደ ተለያዩ የጸጥታ መዋቅር መልሶ የማደራጀቱ እንቅስቃሴ ተገቢ ነው። ቢዘገይም መቅረት የማይኖርበት ጉዳይ ነው። አሁንም ማደራጀት ብቻ ሳይሆን የሚደራጅበት መንገድ በደንብ የተጠና ሊሆን ይገባዋል።

አንድ ሰራዊት ስርዓት በመጣ ቁጥር የሚገለባበጥ ሳይሆን የአገርን ሉአላዊነት የሚያስከብር፤ በሰላሙ ጊዜ ፊቱን ወደ ልማት አዙሮ ለአገር ግንባታ ክንዱን የሚዘረጋ ብሎም ለአገር ሰላምም ሆነ ኢኮኖሚ ዋልታ የሆነ መከለከያ ሰራዊት እንዲመጣ ቁልጭ ያለ ግልፅ ፖሊሲ ያስፈልጋል።

ይህ ፖሊሲ በቋንቋ ያልተበረዘ፤ በብሄር ያልተቃኘ፤ ኃይማኖትን የማይከፋፍል፤ ዓላማው ለአንዲት አገር ሉአላዊነት ዘብ የቆመ ሰራዊት እንዲሆን የኢትዮጵያዊ ስነ ልቦና ያለው ሰራዊትን ለማስቀጠል የሚያስችል ጥናት ያስፈልጋል። በዚህ ጥናት ተመስርቶ የተቃኘ ሰራዊት ያስፈልጋል። የአባቶቹን የጀግንነት ታሪክ በየፈርጁ እያስጠበቀ የሚኖር እና የአገር ታሪካዊ ጠላቶች የሆኑ ዳግም እንዳያንሰራሩ የሚያደርግም መሆን ይጠበቅበታል። ምንም አይነት አገር አፍራሽ ሸፍጥ ሳይሰራ ጂኦ ፖለቲካውን አውቆ የሚመራ የኢትዮጵያ ጦር ኃይልን መቅረፅ ያስፈልጋል።

**አዲስ ዘመን፡- አሁን እየተከናወነ ያለው መልሶ የማደራጀት እንቅስቃሴ መከላከያ ሰራዊቱን ምን ያህል ያጠናክረዋል ብለው ያስባሉ?**

**ሌፍተናንት ዮሴፍ፡-** አሁን እየተከናወነ ያለው ሰራዊቱን መልሶ የማደራጀት እንቅስቃሴ መከላከያ ሰራዊቱን ምን ያህል ያጠናክረዋል ለተባለው ከዚህ በላይ ምን አጠናካሪ ነገር ይኖራል? ምንም አይኖርም። አገር አንድነቷን እንድታስጠብቅና በአፍሪካ ቀንድ ያለች ኃያል አገር ለመፍጠር ትልቅ አቅም ነው።

ኢትዮጵያ ደካማ ሰራዊት እንዳይኖራትም ያደርጋል። የጸጥታ ኃይል ጎጥ ውስጥ እንዳይገባና የዚህ ብሔር አገልጋይ ነህ በሚል መከፋፈል እንዳይኖርም ያግዛል። በዚህም አካሄድ አንድ የመሆን ጅማሬው ይበል የሚያሰኝ ነውና መልካም ነው።

ይህን ግን በዚህ የማደራጀት ሒደት ብቻ ማብቃት የለበትም። ህፃናት ከትምህርት ቤት ጀምሮ ኢትዮጵያዊ ማንነት እንዲኖራቸው አበክሮ መስራት ይገባል።

**አዲስ ዘመን፡- ልዩ ኃይል ለአንድ አገር ምን ጥቅም ምን ጉዳትስ አለው?**

**ሌፍተናንት ዮሴፍ፡-** መጀመሪያ ስለ ልዩ ኃይሉ ጥቅምና ጉዳት ከመነጋገራችን በፊት ምንድነው ልዩ ያሰኘው የሚለውን ጉዳይ ማንሳት እወዳለሁ። በኛ ጊዜ የተለየ ስራ የሚሰሩና የተለየ ተልእኮ የሚሰጣቸው ኃይሎች ‹‹እስፔሻል ፎርስ›› በሚል ይጠሩ ነበር። ከዛም የኢትዮጵያ አወቃቀር ሲቀየርና በክልል ሲከፋፈል ተከትሎ የመጣው ይህ ልክ የራስ ግዛት ያለው ይመስል የእገሌ ልዩ ኃይል በሚል መቋቋም ጀመረ።

መከላከያ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መዋቅር ውስጥ በየትኛውም ክልል ገብቶ የፀጥታ ጉዳይ መስራት ሲችል ለምን ሲባል ነው ልዩ ኃይል ሊቋቋም ያስፈለገው? በየትኛውስ አዋጅ ነው ሊቋቋም የቻለው? የሚል ጥያቄ መጠየቅ እፈልጋለሁ። በክልሉ ለሚከሰቱ የተለያዩ ጉዳዮች ለማርገብ ከሆነ ፖሊስ ምን ያደርጋል? ስራው የክልሉን ፀጥታ ማስከበር ነው። ለምን ይህ ሁሉ ወጪ ወጥቶ መከላከያ ሰራዊት ማቋቋም አስፈለገ? የሚለው ጥያቄ ብጠየቅም አመሰራረቱ ግን ትክክል አለመሆኑን ሳልናገር አላልፍም።

ልዩ ኃይል የክልል ፀጥታን ያስጠብቃል ከተባለ አንዳንድ ቦታ መከላከያን የሚገዳደር አቅም ያለው ሁሉ አለ፤ ይህ መሆኑ ደግሞ የአገር ስጋት ነው። ስለዚህ ይህ ኃይል መኖሩ የአገር መፍረስ ስጋት ነው።

ይህ ልዩ ኃይል ግን በስርአት ተጠንቶ በኢትዮጵያዊ ማንነት ላይ የተመሰረተ ሰራዊት ውስጥ ገብቶ በወጣበት አቅም ልክ ለአገር የሚበቃና የሚያገለግል ሊሆን ይገባዋል።

**አዲስ ዘመን፡- አንድ ክልል ሲኖረው የሚገባው የፖሊስ ሰራዊት ብቻ ነው ይባላል፤ እዚህ ላይ ያልዎት አስተያየት ምንድን ነው?**

**ሌፍተናንት ዮሴፍ፡-** በእኛ ጊዜ የባህር ኃይል ነበር ከዛም የአየር ኃይል፤ እግረኛ ሰራዊት በሚባሉ የተለያዩ ክፍሎች የተከፋፈለ ከመሆኑ በስተቀር በየብሔር የተከፋፈለ አልነበረም። ከእነዚህ ውጪ የፖሊስ ሰራዊት የሚባል ራሱን የቻለ ሰራዊት ደግሞ የውስጥ ደህነንት በሚያስጠብቅ መልኩ ተደራጅቶ ይሰራ ነበር።

ይህ ትልቅ ተቋም በወቅቱ አጠራር በየክፍለ አገሩ የውስጥ ሰላምን የሚያስጠብቀው የፖሊስ ሰራዊት ነበር። ይህ የራሱ አደረጃጀት ነበረው። የውስጥ ችግሮች ቢከሰቱም የፖሊስ ሰራዊት በየቦታው ተገኝቶ ነገሮችን ያስተካክል ነበር። ከአቅም በላይ የሆነ ነገር ሲከሰት ለምሳሌ የተፈጥሮ አደጋ ሲከሰት፣ ከፖሊስ ቁጥጥር ውጪ የሆነ ነገር ሲመጣ መከላከያ ይጠራል። ከመከላከያ አቅም በላይ ከሆነ ደግሞ ህዝባዊ ሰራዊት የሚባል ሰራዊት አለ፤ ይህ ያለውን ችግር ያስተካክላል።

ቀድሞ በነበሩትም ስርአቶች አንድ ክፍለ አገር የከተማ ፖሊስ እንጂ ልዩ ሰራዊት የሚባል አልነበረውም፤ ይህ አለመኖሩ ደግሞ ኢትዮጵያዊነት ገንኖና እና በልጦ እንዲኖር አድርጎታል።

**አዲስ ዘመን፡- እንደ አንድ የሰራዊት አባል አገር ሰላሟ ተጠብቆ ትኖር ዘንድ፤ ከውስጥም ሆነ ከውጭ ለሚነሱ ግጭቶች ሊኖራት የሚገባው የመከላከል አቅም እስከምን ድረስ ነው ይላሉ?**

**ሌፍተናንት ዮሴፍ፡-** ስለሰራዊቱ ሲነሳ በእኛ ጊዜ አሁን እያልኩ ማነፃፀር አልፈልግም። ኢትዮጵያ እስካለች ድረስ አብሯት የሚኖር ዳር ድንበሯን አስከብሮ ሉአላዊነቷን አስጠብቆ የሚሄድ ሰራዊት ያስፈልጋታል። ለዚህም የመከለካያ ሰራዊትን ከሰው እስከ ትጥቅ በበቂ ሁኔታ ማደራጀት ያስፈልጋል።

አሁን ባለው ሁኔታ አገራችን በርካታ ጠላቶች ያላት አገር ናት፤ ይህንን በተገቢው መልኩ ተረድቶ ከአገር የሚቀድም የለም በማለት ደረቱን ለጥይት የሚሰጥ ኃይል ያስፈልጋታል። በአሁኑ ወቅት በግልፅ የሚታዩ ዳር ድንበርን የመድፈር ሁኔታ አለ። ይህንን የሚከላከል ከታሪክ ተጠያቂነት የሚያድን፣ ጠላትን ተቋቁሞ ለማለፍ የሚያስችል፣ ከውስጥ ግጭት የፀዳ ኢትዮጵያዊ መከላከያ ሰራዊት ሲኖር ነው።

እኔ በዘመኔ አራት መንግስታትን ተመልክቻለሁ። ሁሌም መሪዎች ይሄዳሉ፤ ህዝብ ቀሪ ነው። የዚህ ህዝብ አካል የሆነ ሰራዊት ሊኖረ ያስፈልጋል። ሰው በብሔር መከፋፈሉን ትቶ አንድ አይነት አመለካከት ያለው ማህበረሰብ፤ ማህበረሰቡ የወለደው ጠንካራ አንድነት የሚጠብቅ መከላከያ ሰራዊት ያስፈልጋል።

ወጣቶች ትምህርታቸውን ሲጨርሱ ለአገር አገልግሎት የሚሰጡ ወታደሮችን በመፍጠር እንደነ እስራኤል ፍፁም አገር ወዳድ የሆነን ህዝብ ማደራጀት ተገቢ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ውድ ጊዜዎን ሰውተው ተቋማችን ድረስ መጥተው ሀሳብዎን ስላካፈሉን በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ስም ሳቅ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።**

**ሌፍተናንት ዮሴፍ፡-** እኔም ሀሳብህ ይጠቅማል ብላችሁ እንደካፍል ስለጋበዛችሁኝ ከልቤ አመሰግናለሁ።



**ለአንድ ወታደር መለያው ሊሆን የሚገባው መጀመሪያም ወደ ስልጠና ተቋም ሲገባ የሚማረው ነገር ወታደራዊ ስነ ምግባርን ነው። ይህ ወታደራዊ ዲሲፕሊን ከአነጋገር እስከ አለባበስ፤ ከአካሄድ ጀምሮ እስከ ሰውነት እንቅስቃሴ በስርዓት የተቃኘ መሆን አለበት።**

# ማህደረ ጤና

## ጤናማ ያልሆነ አመጋገብ፡- ዝምተኛው ገዳይ

**አስናቀ ፀጋዬ**

የከተሞች መስፋፋትን ተከትሎ የሰዎች የአኗኗር ዘይቤ በእጅጉ እየተቀየረ መጥቷል:: ይህም የአመጋገብ ስርዓትን ቀይሯል:: በፋብሪካ የተቀነባበሩ ምግቦች በከፍተኛ ደረጃ በአቅርቦት እየጨመሩና በተመጣጣኝ ዋጋ ለገበያ እንደልብ መቅረብ ደግሞ የአመጋገብ ስርዓቱ እንዲቀየር ትልቅ አስተዋፅኦ አድርገዋል:: ሰዎችም እነዚህን ምግቦች በተለይ ደግሞ የረጋ ስብ/transfat and Saturated fat/፣ ስኳርና የጨው ይዘት ያላቸውን ምግቦችንና መጠጦችን አዘውትረው በመመገብ ተላላፊ ላልሆኑ በሽታዎች እየተጋለጡ መጥተዋል::

መረጃዎች እንደሚያሳዩት በዓለም አቀፍ ደረጃ በየዓመቱ 8 ሚሊዮን የሚሆኑ ሰዎች ጤናማ ባልሆነ አመጋገብ ምክንያት ህይወታቸው ይቀጠፋል:: እንደ ዓለም ጤና ድርጅት ሪፖርት ደግሞ 5 ቢሊዮን ሰዎች በትራንስ ፋት አደጋ ስጋት የተጋለጡ በመሆናቸው ከዚሁ ጋር ተያይዞ ለልብ ህመም ይጋለጣሉ ተብሎ ይገመታል:: በየዓመቱም ከግማሽ ሚሊዮን በላይ ሰዎች በትራንስ ፋት ለሞት ይዳረጋሉ:: ከመጠን ያለፈ ክብደት፣ የደም ግፊትና የስኳር በሽታዎች ጤናማ ባልሆነ አመጋገብ ምክንያት የሚከሰቱ ዋነኞቹ በሽታዎች ናቸው::

በኢትዮጵያም እ.ኤ.አ በ2010 በተደረገ ጥናት ከ20 እስከ 69 ዓመት እድሜ ክልል በልብና በደም ቧንቧ በሽታዎች ከሞቱት ውስጥ የ33 በመቶዎች የሞት ምክንያት ከፍተኛ የጨው አጠቃቀም ነው:: ጨውን በከፍተኛ ደረጃ መጠቀም ለደም ግፊት በማጋለጥ የልብና የደም ቧንቧ እንዲሁም ስትሮክ አደጋን እንደሚጨምርም በዚሁ ጥናት ተረጋግጧል::

የዓለም ጤና ድርጅት በቅርቡ ባወጣው ሪፖርት ደግሞ ከ 1 ነጥብ 8 ሚሊዮን በላይ ሰዎች በከፍተኛ ጨው አጠቃቀም ምክንያት በየዓመቱ እንደሚሞቱ አስታውቋል:: በየዓመቱ ከ180 ሺ በላይ ሰዎች ስኳራማና ጣፋጭ መጠጦችን አብዝቶ በመውሰድ ምክንያት ህይወታቸውን እንደሚያጡም ገልጿል::

አቶ ክፍሌ ሀብቴ በኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት የምግብ ሳይንስና የስርአተ ምግብ ተመራማሪ ናቸው:: እርሳቸው እንደሚሉት ጤናማ ያልሆኑ ምግቦች የስኳር፣ የጨውና በመደበኛ የቤት ውስጥ ሙቀት የሚረጋ ዘይትና የአትክልት ቅቤ፣ / transfat and Saturated fat/ መጠናቸው የበዛባቸው ፈጣንና በፋብሪካ የተቀነባበሩ ምግቦችንና መጠጦችን ያጠቃልላል:: እነዚህን ምግቦች አብዝቶና በተደጋጋሚ መመገብ ደግሞ ለከፍተኛ የሰውነት ውፍረት፣ ስኳር፣ ካንሰርና የልብ ህመም ለመሰሉ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችና ለሌሎች የጤና እክሎች ያጋልጣል::

የአካል ብቃት እንቅስቃሴዎችን በማድረግ መቆጣጠር ይቻል ካልሆነ በስተቀር ህመሞቹ እድሜ ዘለቅና የማያቋርጥ ክትትል የሚፈልጉ ናቸው:: በኢትዮጵያም ጤናማ ያልሆነ አመጋገብ የደም ግፊት፣ የስኳር ህመም /በተለይ አይነት ሁለት የስኳር ህመም/፣ በደም ውስጥ የኮሌስትሮል መጠን መጨመር፣ ካንሰርና ሌሎች ተዛማጅ የጤና ችግሮችን እያስከተለ ይገኛል::

ለአብነትም ተፈጥሯዊ ከሆኑት ውስጥ ስብ ያለው ስጋ አዘውትሮና በብዛት መመገብ ትራንስ ፋት ያለውና ከፍተኛ የስብ መጠን የያዘ በመሆኑ ተላላፊ ላልሆነ በሽታ ያጋልጣል:: በፋብሪካ ተቀነባብሮ የወጣ ቅቤም በተመሳሳይ ትራንስ ፋት ያለውና በውስጡ ሳቹሬትድ ፋት የያዘ በመሆኑ ይህን አዘውትሮ መመገብ በተመሳሳይ ለነዚሁ ተላላፊ ላልሆኑ በሽታዎች የመጋለጥን እድል ይጨምራል::

በሌላ በኩል ደግሞ ጣፋጭ ምግቦችን ለአብነትም ብስኩቶችን፣ ኬኮችን፣ ከረሜላዎችን፣ ቸኮሌቶችንና ሌሎች መሰል ጣፋጭ ምግቦችን አዘውትሮና በተደጋጋሚ መመገብ ከጥርስ መቦርቦር ጀምሮ ለሌሎች እድሜ ዘለቅ በሽታዎች ያጋልጣሉ:: ሆኖም እነዚህን ምግቦች በሌሎች ተፈጥሯዊ ምግቦች ማመጣጠን ከተቻለ ጉዳታቸውን መቀነስ ይቻላል:: በተለይ ደግሞ እነዚህ ጣፋጭ ምግቦች በልደትና መሰል ፕሮግራሞች ላይ የሚቀርቡ በመሆናቸውና ህፃናት የሚመገቧቸው በመሆኑ የህፃናት ጤና እንዳይጎዳ በቤተሰብና በህፃናት ላይ የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራዎችን መስራት ያስፈልጋል::



ጤናማ ያልሆነ አመጋገብ ለውፍረትና ተላላፊ ላልሆኑ በሽታዎች ያጋልጣል፤

**የጨው** አጠቃቀምን በሚመለከት በተደጋጋሚና ከልክ በላይ እስከተወሰደ ድረስ ጤናማ ካልሆኑ ምግቦች ተርታ የሚመደብ ነው:: የዓለም ጤና ድርጅት አንድ ሰው በቀን አምስት ግራም ጨው እንዲወስድ ይመክራል

በተመሳሳይ ክሬም፣ ማርጋሪንና በፋብሪካ የተቀነባበሩ ቅቤዎችም ለግዜው ሊጣፍጡ ቢችሉም በውስጣቸው ትራንስ ፋትና የረጋ ዘይት/Saturated fat acid/ በውስጣቸው ያላቸው በመሆኑ ብሎም የቅባት መጠናቸውም ከፍተኛ ስለሆነ ተላላፊ ላልሆኑ በሽታዎች የማጋለጥ እድላቸው ከፍተኛ ነው:: ቺፕስ፣ በርገር፣ ማስቲካ፣ ከረሜላ፣ ቸኮሌቶችም በውስጣቸው ከፍተኛ ስኳር የሚይዙ እንደመሆናቸው በከፊል የረጋ ዘይት በውስጣቸው ስለሚኖር በቀላሉ ከጥርስ መቦርቦር ጀምሮ ለተለያዩ እድሜ ዘለቅ በሽታዎች ይዳርጋሉ::

እንደ አቶ ክፍሌ ገለፃ ጤናማ ያልሆኑ ምግቦች በጤና ላይ ጉዳት የሚያስከትሉት የኋላ ኋላ ነው:: በጤና ላይ የሚያሳድሩት ተፅእኖም ቀስ በቀስና በዝምታ ነው እንጂ ወዲያው አይደለም:: እነዚህን ምግቦች በተደጋጋሚና በብዛት መውሰድም ነው ተላላፊ ላልሆኑ በሽታዎች የሚያጋልጠው:: ለአብነትም የደም ግፊት ያለበት ሰው ጨው ቢወስድ ከጤናማ ሰው ጋር ሲነፃፀር ህመሙ ወዲያው ይሰማዋል:: ጤነኛ የሆነ ሰው ግን ጨውን ቢጠቀም ወዲያውኑ የህመም ስሜት አይሰማውም:: ህመሙ የሚሰማውና ለደም ግፊት በሽታ ሊጋለጥ የሚችለው ጨውን በተደጋጋሚና አዘውትሮ ሲመገብ ነው::

ብዙ የማይገመቱና ከስኳር ነፃ ቢሆኑም የማቆያ ንጥረ ነገሮችን የሚይዙ የለስላሳ መጠጦችና የታሸጉ ጭማቂች በድግግሞሽ የሚወሰዱ ከሆነ እነዚህም ተላላፊ ላልሆኑ በሽታዎች በተለይ ደግሞ ለስኳር በሽታ፣ ለካንሰርና ውፍረት በከፍተኛ ደረጃ ያጋልጣሉ::

የረጋ ስብ /trans fat acid/ በሚመለከት ደግሞ የዓለም ጤና ድርጅት የሰው ልጅ በቀን ማግኘት ካለበት አጠቃላይ የ1 ከመቶ ኃይል መብለጥ እንደሌለበት ያስቀምጣል:: ቢቻል ግን በምግቦች ውስጥ የትራንስ ፋት አሲድ መጠን ባዶ ቢሆን ይመረጣል::

ሌሎች የአፍሪካ፣ የአውሮፓና የሌሎች አህጉራት አገራት ከኢትዮጵያ በበለጠ የተቀነባበሩ ምግቦችን ሊመገቡ ይችላሉ:: ቅጥ ያጣ ውፍረት የሚታየውም እነዚሁ ምግቦችን በሚመገቡ አገራት ውስጥ ነው:: ይህም ብዙ ካሎሪ ያላቸውን ምግቦች በብዛትና በድግግሞሽ እንደሚወስዱ ያሳያል:: ምግቦቹን በቀላል ዋጋ መሸመትና ማግኘት እንደሚችሉም ይጠቁማል:: በዚህም ምክንያት በተለይ የአውሮፓና አሜሪካ አገራት ሰዎች ከ30 እስከ 60 በመቶ ካሎሪ ይመገባሉ::

በኢትዮጵያ ግን በቂ የዳታ ጥንቅር ባለመኖሩ ምን ያህል ካሎሪ ሰዎች እንደሚመገቡ ለማወቅ ያስቸግራል:: ከእያንዳንዱ ምግቦችን ምን ያህል ካሎሪ ሰዎች እንደሚያገኙ የሚያሳይ ጥርት ያለ መረጃም የለም:: ሆኖም የ2011 ዓ.ም የምግብ ፍጆታ ዳሰሳ ጥናት ሲታይ የኢትዮጵያውያን የተቀነባበሩ ምግቦችን የመጠቀም ሁኔታ አነስተኛ እንደነበር ያሳያል:: አሁንም የተሰበሰበ ዳታ እንዳለ ሆኖ ቁጥሩ ሊጨምር ግን ይችላል::

የተቀነባበሩ ምግቦችን የመጠቀም ሁኔታ እንደሌሎቹ አገራት የከፋ ደረጃ ላይ የደረሰ ባይሆንም ገበያውና መደብሩ በበዛ ቁጥርና የግብርና ምርቶች እየቀነሱ በሄዱ ቁጥር ወደተቀነባበሩ ምግቦች የመሄድ እድሉ በጣም ሰፊ ነው:: አንዴ ከመጣ በኋላ ተጋላጭነቱን ለመመለስም በጣም አስቸጋሪ ይሆናል:: በዚሁ ምክንያት ለሚከሰተው እድሜ ዘለቅ በሽታ ምክንያት የሚወጣው የህክምና ወጪም ከባድና የማይቻል ነው::

አቶ ክፍሌ እንደሚያብራሩት የገበታ ስኳር ፍጆታን በሚመለከት የዓለም ጤና ድርጅት ከ20 እስከ 50 ግራም በቀን መጠቀም እንደሚገባ ያስቀምጣል:: የዓለም ምግብ ድርጅት ባወጣው መረጃ መሰረት ደግሞ የኢትዮጵያውያን ዓመታዊ የስኳር ፍጆታ 6 ነጥብ 32 ኪሎ ግራም ነው:: ይህም የአንድ ሰው የቀን የስኳር ፍጆታ የዓለም ጤና ድርጅት ካስቀመጠው መጠን ያነሰ መሆኑን ያሳያል:: ከዚህ አንፃር የኢትዮጵያውያን የስኳር አጠቃቀም ጤናማ ነው ማለት ይቻላል:: ሆኖም ደግሞ ኢትዮጵያውያን ከስኳር በቂ ኃይል እያገኙ ነው ወይ? የሚለው ሌላ ጥያቄ ነው::

በ2011 ዓ.ም በኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት በተሰራ የዳሰሳ ጥናት አንድ ሰው በቀን በአማካይ 1 ሺ 700 ኪሎ ካሎሪ ይጠቀማል:: የዓለም ጤና ድርጅት ደግሞ በቀን ከ2 ሺ እስከ 2 ሺ 200 ካሎሪ አንድ ሰው መውሰድ እንዳለበት ይመክራል:: ይህም ኢትዮጵያ ካሎሪን እየተጠቀመች እንዳልሆነና መቀንጨርም የዚሁ ውጤት መሆኑን ያሳያል:: የካሎሪው መጠንና ከየትኛው ምግብ ነው የሚገኘው የሚለው ወሳኝ ጉዳይ ነው::

የጨው አጠቃቀምን በሚመለከት በተደጋጋሚና ከልክ በላይ እስከተወሰደ ድረስ ጤናማ ካልሆኑ ምግቦች ተርታ የሚመደብ ነው:: የዓለም ጤና ድርጅት አንድ ሰው በቀን አምስት ግራም ጨው እንዲወስድ ይመክራል:: ይህም ከየትኛውም መመዘኛ አንፃር ጤናማ ነው:: በ2011 ዓ.ም በተሰራ ጥናት በኢትዮጵያ የአንድ ሰው የቀን የጨው ፍጆታ 8 ነጥብ 3 አካባቢ ነው:: ይህም በኢትዮጵያ የሰዎች የቀን ጨው ፍጆታ ከፍተኛ መሆኑን ይጠቁማል::

አቶ ክፍሌ እንደሚሉት ጤናማ ያልሆነ አመጋገብ ተላላፊ ላልሆኑ በሽታዎች ይበልጥ እያጋለጡ በመምጣታቸው አሳሳቢነታቸውም እየጨመረ እንደመሆኑ የስርአተ ምግብ መመሪያ 2022ትን አንብቦ በዛ መሰረት የአመጋገብ ስርአትን ማስተካከል ያስፈልጋል:: ለምሳሌ በዚሁ መመሪያ መሰረት አንድ ለስላሳ በቀን መጠጣት በቀን ከተቀመጠው የስኳር ፍጆታ አንፃር ከፍተኛ በመሆኑ ጤናማ አይደለም:: በቀንም ሆነ በሳምንት የምግብ አጠቃቀምን መቀያየር ያስፈልጋል:: ከአንድ አይነት ይልቅ የተለያዩ ምግቦችን መመገብም ይገባል::

በፋብሪካ የተቀነባበሩ ምግቦችን ከሌሎች ተፈጥሯዊ ምግቦች ጋር በመቀላቀል መመገብም ራስን ተላላፊ ካልሆኑ በሽታዎች ከመያዝ ማራቅ ያስችላል:: ስኳር የበዛባቸውን መጠጦችን፣ ኬኮችን፣ ቸኮሌቶችን፣ ከረሜላዎችን፣ ኩኪሶችንና ሌሎችንም መሰል ጣፋጭ ምግቦችን ከተቻለ መተው፤ ካልተቻለ ደግሞ ቢያንስ በሳምንት አንድ ግዜ ቢወሰድ ይመረጣል:: የሰባ ስጋ ከመመገብ ቀይ ስጋ መመገብ ይመረጣል:: ወተትም ቢሆን ብዙ ቅባት ያለው ከሆነ የራሱ የሆነ የጤና ጉዳት ስለሚያስከትል ብዙም ቅባት የሌለውን መጠቀሙ ይመከራል::

ከዚህ ባለፈ ጤናማ ያልሆነ የአመጋገብ ችግርን ለማስተካከል የተለያዩ የቁጥጥር አካላትም የራሳቸው አስተዋፅኦ ይኖራቸዋል:: ለምሳሌ ጤናማ ያልሆነ አመጋገብ ቁጥጥር አዋጅ እየተዘጋጀ ይገኛል:: ይህ አዋጅ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከፀደቀ ከማስታወቂያ ጀምሮ ምን አይነት ሌብል በምግቦቹ ላይ መኖር አለበት የሚል ህግ ይኖረዋል::

ጤና ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩትና የምግብና መድሃኒት ቁጥጥር ባለስልጣንም ጤናማ ያልሆነ አመጋገብን ከመቆጣጠር አኳያ የራሳቸው ድርሻ ይኖራቸዋል:: የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲም ደረጃዎችን በማውጣት በቁጥጥር ስርአቱ ውስጥ የራሱን ሚና ይጫወታል:: ግብርና ሚኒስቴርም ጤናማና ተፈጥሯዊ ምግቦችን በማምረት ረገድ የራሱን ድርሻ ይወስዳል::

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ


# ነፃ ሃሳብ





(በጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

## "የአርበኞች መታሰቢያ? የነፃነት ቀን?" ወይንስ የድል በዓል!















### የመንደርደሪያችን መደላድል፤

የሀገራዊ አስተሳሰባችን ውቅርና የጋራ ታሪካዊ እሴቶቻችንን አረዳድ፣ አቀባበልና ፍረጃ በተመለከተ የጋራ መግባባት ላይ ለመድረስ መቸገራችን ዋነኛው "የብሔራዊ ሕመማችን" ምልክት ስለመሆኑ ይህ ጸሐፊ በሚገባ ያምንበታል። ከአሁን ቀደም በዚሁ ዐምድ ላይ ደጋግሞ ለመግለጽ እንደተሞከረው፤ ከሀገራዊ ታሪኮቻችን መሰዊያ ላይ ፍሙን ብቻ እየጫርን በትናንት መልካም ውርሶችና እሴቶቻችን ስሜታችንንና መንፈሳችንን በማሞቅ ጨለማችንን ከመግፈፍ ይልቅ አመዱን እየዛቅን በመበተን መናቆሩ እስከ ዛሬ ድረስ የትም ሊያደርሰን አልቻለም፤ ለወደፊቱም ቢሆን "የጋት ያህል" ፈቅ ሊያደርገን እንደማይችል አያያዛችን ምስክር ነው።

በታሪኮቻችን ይዘትና ምንነት ላይ ብቻ ሳይሆን በስያሜዎቻቸውም ላይ ሳይቀር ብዙ መጣረሶች እንደሚስተዋሉ "ዕድሜ ደጉ" ቆመን እንድናስተውል የተፈረደብን ይመስላል። ለአብነት ያህልም በትናንትናው እለት አክብረን የዋልነውን ታሪካዊ የድል በዓል ስያሜ በተመለከተ እንዴት ሲውገረገር እንደኖረ ሳንረዳ የቀረን አይመስለንም። ለዚህ ሁሉ ጥፋት በዋነኛነት ተጠያቂዎቹ ደግሞ ጥቂት የማይባሉ የብዙኃን መገናኛ ባለሙያዎችና የተለያዩ የኅትመት ዐውደ እለታት (Calendars) አሳታሚና አታሚ ተቋማት በቀዳሚነት ጣት ይጠቆምባቸዋል።

በርካቶች በሚያሳትሟቸው ዐውደ ዕለታት ገጾች ላይ የሚያዝያ 27 በዓልን "የአርበኞች መታሰቢያ" በማለት መግለጻቸው የተለመደ ነው። በዓሉ በጀግኖች አርበኞቻችን የደምና የመስዋዕት ውጤት መገኘቱ እርግጥ ቢሆንም፤ በጦርነቱ የተሳተፉትን በተመለከተ ግን በዚያ ዘመን የኖሩትን ሁሉንም የማኅበረሰብ ክፍሎች የሚወክሉ የኢትዮጵያ ልጆች በምልዓት አሻራቸውን ያተሙበት የመስዋዕትነት ድል ነበር።

ብዙዎች በአፍላው ጦርነት ጥሎ በመውደቅ፣ አንዳንዶች በውስጥ አርበኝነት፣ አንዳንዶች የልባቸውን በልባቸው አድርገው ከፋሽስቶች ጋር አብሮ በመሥራትና በመዋል ለአርበኞች መረጃ በማቀበል፣ አንዳንዶችም አርበኞችን በቤታቸው ውስጥ ሸሽገውና ደብቀው በማሳረፍና ግድ ሲልም በሕክምና በማገልገል፣ ብዙኃን ዜጎችም እንዲሁ ስንቅ በማቀበልና በስለላ ወዘተ. የተሳትፎው ወሰን ይህ ልኩ ተብሎ በማይወሰን መስዋዕትነት ድርሻቸውን ተወጥተዋል። እርግጥ ነው "ከስንዴ መካከል እንክርዳድ..." እንዲሉ ከጠላት ጋር በማበር ክህደት ፈጽመው ሀገራቸውንና ሕዝባቸውን የወጉ ባንዳዎችም እንደነበሩ በሚገባ ይታወቃል።

"የአርበኞች መታሰቢያ" የሚለው ስያሜ የተሸከመው ሌላው ስህተት በዓሉ በብሔራዊ ደረጃ ከፍ ያለ ክብርና እውቅና ተሰጥቶት ዕለቱ በመንግሥታዊ አዋጅ ተደንግጎና መደበኛ የሥራ እንቅስቃሴ ተዘግቶ በብሔራዊ ደረጃ የሚከበር በዓል እንጂ "ታስቦ ብቻ" የሚውል አይደለም። ስለዚህም "መታሰቢያ" የሚለው ገለጻ ይህንን ብሔራዊ የድል በዓል አይመጥንም።

ሌላውና መታረም የሚገባው ስህተት "ሚያዝያ 27 የነፃነት በዓል" የሚለው አገላለጽ ነው። በመሠረቱ ኢትዮጵያ በየትኛውም ዘመን በቅኝ ገዢዎች የወረራ ሙከራ ሲደረግባት ቢኖርም ወራሪዎቹ በሙሉ በእፍረት ተዋርደው ተባረሩ እንጂ የትኛውም ሀገርና መንግሥት በቅኝ ግዛት ባርነት ሥር ስላላንበረከካት "የነፃነት" ቀን የላትም። በትናንትናው ዕለት ያከበርነው ብሔራዊ በዓላችንም "የድል በዓል" እንጂ ሌላ ስያሜ አይመጥነውም።

በየዓመቱ የሚከበረውን የሚያዝያ 27 ብሔራዊ የድል በዓል ስንዘክር ሊታወሱ የሚገባቸውን አንዳንድ ዋና ዋና ጉዳዮችን ጠቁመን እንለፍ። የፋሽስት ኢጣሊያ ወረራን ተጋድለንና ተፋልመን በአርበኞቻችንና በሕዝባችን ብርቱ መስዋዕትነት አኩሪ ድል መቀዳጀታችንን አጉልተን የምንመሰክረው እኛ ብቻ ሳንሆን ዓለም በሙሉ ያረጋገጠው ገድላችን ነው። ይህ የሕዝባችን የተጋድሎ ታሪክ እንደተከበረ ሆኖ ከበስተጀርባ እና ፊት ለፊት በመውጣት ወራሪውን የፋሽስት ኢጣሊያ መንግሥት በዓለም ፊት በመኮነን አጋርነታቸውን የገለጹልንና ድጋፍ ያደረጉልን ወዳጅ መንግሥታትና ሕዝቦችም መኖራቸው ሊዘነጋ አይገባም።

እርግጥ ነው ወራሪው የፋሽስት ኃይል አከርካሪው ተሰብሮ ጦርነቱ በድል ከተጠናቀቀ ሰማንያ ሁለት ዓመታት ቢቆጠርም ከላይ የጠቀስናቸውንና ከጎናችን ተሰልፈው ወይንም በርቀት ሆነውም ቢሆን ድጋፍ ላደረጉልን የክፉ ቀን ወዳጅ መንግሥታት በየዓመቱ ድላችንን ስንዘክር በፕሮቶኮል ንግግሮችና ከፍ ሲልም መንግሥት የጉዳዩን ክብደት ተረድተው ድጋፍ ላደረጉልን መንግሥታት በቋሚ መታሰቢያ እውቅና ቢሰጣቸው ወዳጅነቱንና የዲፕሎማሲ ግንኙነቱን በእጅጉ እንደሚያጠናክረው አሌ አይባልም። ይህ ማለት ግን ለአንዳንድ ሀገራት ዜጎችና መንግሥታት ከአሁን ቀደም በስማቸው መንገድ፣ አደባባይ፣ ት/ቤትና በጥቂቱም ቢሆን አንዳንድ ተቋማት በስማቸው መሰየሙ የሚካድ አይደለም። ጥያቄው በቂ ነው አይደለም? የሚለውና ሁሉንም አለማካተቱ ነው።

የ2008 ዓ.ም የሚያዝያ 27 የድል በዓል በተከበረበት ዓመት የተፈጸመን አንድ በአርአያነቱ ከፍ ያለ ተግባር ለአብነት እናስታውስ። በተጠቀሰው ዓመት የተከበረውን የ75ኛውን ዓመት የአልማዝ ኢዮቤልዩ የድል በዓል ሙሉ ዝግጅቶች ለማስተባበር የጥንታዊ ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማኅበር እድሉን የሰጠው ይህ ጸሐፊ ለሚሠራበት ተቋም ሲሆን የማስተባበሩም ሙሉ ኃላፊነት የዚህ ዓምደኛ ነበር።

ከዋናው በዓል አስቀድሞ እጅግ በርካታ መርሐ ግብሮች የተከናወኑ ቢሆንም ሁለቱን ኩነቶች ብቻ በምሳሌነት ጠቅሰን ለማስታወስ እንሞክር። የወርቅ ኢዮቤልዩ በዓሉን ካደመቁት መካከል አንዱ ተጠቃሽ ተግባር ከኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት ጋር በመተባበር ለ26 ያህል ጀግኖች አርበኞቻችን የመታሰቢያ ቴምብር መዘጋጀቱ ነበር። ይህ የመታሰቢያ ቴምብር ሁሉንም አርበኞች ሊወክሉ ይችላሉ ተብሎ የታመነባቸው ጀግኖች አርበኞች የተካተቱበት ነው። ከኢትዮጵያ ጎን ቆመው ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያደረጉ እንደ እንግሊዛዊቷ ክብርት ሪታ ፓንክረስትን የመሳሰሉት ወዳጅ የውጭ ሀገራት ዜጎችም በቴምብሩ ላይ ምስላቸው እንዲገባ ተደርጓል።

ሁለተኛው ክንውን በዓይነቱ እጅግ የተደነቀው የሽልማት መርሐ ግብር ሲሆን ተሸላሚ መንግሥታቱ በጦርነቱ ወቅት ከጎናችን የተሰለፉባቸው ምክንያቶች የተለያዩ ነበሩ። ለምሳሌ፡- እንግሊዝና ሰሜን አየርላንድ፣ ቻይና፣ሩሲያ፣ ሜክሲኮ፣ ኒውዚላንድ፣ ስዊድን፣ ደቡብ አፍሪካ፣ አርጀንቲና በቀጥታ ከሀገራችን ጎን ቆመው የድጋፍ ድምፃቸውን በማሰማት የፋሽስቶችን ወረራ በአንድም ሆነ በሌላ ተቃውመዋል፤ እንዳስፈላጊነቱም ልዩ ልዩ ድጋፎች አድርገውልናል። ኬኒያ፣ ሱዳን፣ ታንዛኒያ፣ ናይጄሪያ፣ ጋናና ዩጋንዳ ደግሞ ከእንግሊዝ የቃል ኪዳን ጦር ጋር የተሰለፉ ወታደሮችን ያዋጡ ሀገራት ናቸው።

ምክንያቱ በእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ሥር ስለነበሩ ብቻ ሳይሆን በዋነኛነት ሊቆጠርላቸው የሚገባው ከኢትዮጵያ ሠራዊት ጎን ተሰልፈው የከፈሉት መስዋዕትነት ነው። ከእነዚህ ሀገራት ዜጎች መካከል በጦርነቱ መሐል የወደቁት ወታደሮች መካነ መቃብር በድሬዳዋ ውስጥ እንደሚገኝ ይታወቃል። የዘላቂ ማረፊያው ስም "No. 1" የሚባል ሲሆን ዛሬም ድረስ በጥንቃቄ እንደተጠበቀ ይገኛል።

ከላይ ከተዘረዘሩት መንግሥታት በተጨማሪ ከጦርነቱ በፊት ወታደራዊ ኤክስፐርቶችን ልኮ የረዳን የቤልጂዬም መንግሥትና በድሉ ማግሥት የየካቲት 12 የሰማዕታት ሐውልትን አሰርቶ በስጦታ የሰጠን የወቅቱ የሰርቢያ ሪፑብሊክ መንግሥትም ከተመስጋኞቹ መካከል ነበሩ። የቀድሞው የሀገራችን ፕሬዚዳንት ክቡር ግርማ ወልደ ጊዮርጊስ በክብር እንግድነት ተገኝተው ሽልማቱን ባበረከቱበት ወቅት ተሸላሚ ሀገራቱ በሀገራችን ውስጥ በሚገኙት አምባሳደሮቻቸው ውክልና የተሰማቸውን ስሜት የገለጹት ከቁጥጥር በላይ በሆነ ተመስጦ ውስጥ በመሆን ነበር። "ኢትዮጵያ እንዴት ከ75 ዓመት በኋላ አሰበችን" በማለት። ለማንኛውም ይህ በጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማኅበር ተነሳሽነት የተፈጸመው አስመስጋኝ ተግባር በመንግሥት ደረጃ ተጠናክሮ ቢፈጸም ውጤቱ ያማረ እንደሚሆን ይታመናል።

በወቅቱ ታትመው ከነበሩት ሰነዶች መካከል አንዳንድ ተጠቃሽ ታሪኮችን እየመዘዝን ለማስታወስ እንሞክር። አርበኝነት የኢትዮጵያ ታሪክ አካል ነው። የሀገራችን ሥርዓተ መንግሥታትም በነፃነት ቆመው የኖሩት፣ ሀገርና ሕዝብም ከቅኝ ተገዥነት ነፃ ለመሆን የበቃው በሕዝባችን የአርበኝነት ተጋድሎ ነው። ከአክሱማዊው አፄ ካሌብ ጀምሮ በመካከለኛው፣ በጎንደር፣ እና በዘመናዊው ታሪካችን ውስጥ የአርበኝነት ታሪክ አብሮ አድጓል።

የእርስ በእርሱን መናቆርና ሥርዓተ መንግሥታቱን ለማማከልና ለማጠናከር የተደረጉትን መስፋፋቶች ትተን፣ ሀገርንና ወገንን በጋራ በመከላከል ረገድ ከቱርኮች፣ ከዐረቦች፣ ከድርቡሾች-ማሃዲስቶች፣ ከግብፃውያን፣ ከእንግሊዞች እና ከኢጣሊያኖች ጋር ተዋግተናል። የነፃነት ታሪካችን የተቀረጸው በዚህን መሰሉ ውጣ ውረድ ውስጥ በመሆኑ የአርበኝነት ዋጋውና ታሪካዊ ቦታው ትልቅ ሥፍራ ይኖረዋል።

### የፋሽስት ኢጣሊያ የዝግጅትና የወረራ ዜና መዋዕል፤

መስከረም 22 ቀን 1928 ዓ.ም ሐሙስ ማታ በ12 ሰዓት ቤኒቶ ሙሶሊኒ በጽሕፈት ቤቱ ሰገነት ላይ ብቅ ብሎ ንግግሩን ለመስማት ይጠባበቅ ለነበረው ለመላው የጣሊያን ሕዝብ «ኢትዮጵያን ለ40 ዓመታት ታግሰናታል! እንግዲህስ በቃ!» ብሎ ረጅም የድንፋታ ንግግር ሲያደርግ የሕዝቡ ደስታ እጅግ በጋለ መልኩ ይስተጋባ ነበር። ይህም በተንቀሳቃሽ የፊልም ምስል በዓለም ዙሪያ ታይቷል። ጥቂት የማይባሉ ኢትዮጵያውያንም በቁጭትና በንዴት እንደተመለከቱት ይታመናል።

የሙሶሎኒ ንግግር ከመሰማቱ ሰባት ሰዓት ቀደም ብሎ መስከረም 21 ቀን 1928 ዓ.ም እኩለ ቀን ሲሆን ፋሺስቱ ጄ.ደ ቦኖ ከመረብ ወንዝ 50 ኪሎ ሜትር ራቅ ብሎ ለወረራ ሲዘጋጅ ነበር። ከንጋቱ 11፡00 ሰዓት ሲሆን 268,000 የጦር ወታደር፣ 7,000 መኮንኖች፣ 150 ታንኮች፣ 150 አዳኝና ቦምብ ጣይ አውሮፕላኖች፣ 700 ልዩ ልዩ መድፎች፣ 6,000 ከባድና ቀላል መትረየሶች፣ 6,000 የጭነት የጋማ ከብቶች፣ 2,300 ተሽከርካሪዎች ይዞ በመንቀሳቀስ ከጧቱ 3፡00 ሰዓት ተኩል ሲሆን መረብን ተሻግሮ ወደ ኢትዮጵያ ዘለቀ። መረብን ሲሻገር የኢትዮጵያ ጦር በሚወስደው የመከላከልና የማጥቃት እርምጃ ችግር ይፈጥርብኛል ብሎ የነበረው የጠላት ጦር ስጋቱ እውን ሳይሆን ያለአንዳች ተቃውሞ ሰተት ብሎ ገባ።

የጣሊያኖችን ወረራ አስመልክቶ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መስከረም 22 ቀን 1928 ዓ.ም የክተት አዋጅ አስነግረው የጉዞ ነጋሪት መጎሰም ጀመረ። ጣሊያኖች በኢትዮጵያ ላይ የዘመቱበት ሰበብ በብዙ መላምቶች ሊታጀብ ቢችልም ዋናውና ትልቁ ምክንያት ግን በዘመናዊ የዓለም ታሪክ ጥቁር ሕዝብ አንድን የአውሮፓ ኃይል አዋርዶ ያባረረውን ታሪክ በበቀል ለማደስ የተጠነሰሰ እንደነበር መገመትና ብሎም ማመን አያዳግትም።

ጣሊያኖች ለጦርነት 40 ዓመት ሲዘጋጁ ኢትዮጵያ ለጦርነት ዝግጅት ያደረገችው 3 ዓመት ብቻ ነበር። በወቅቱ ሀገራችን የነበራት በአብዛኛው ዘመን ያለፈባቸው አንድ ሚሊዮን የሚገመቱ ጠብመንጃዎችና ወደ 150 ሚሊዮን የሚጠጉ ጥይቶች ብቻ እንደነበሩ በታሪክ ተመዝግቧል። የጦርነቱ ጊዜ እየተቃረበ በሄደበት ወቅት የኢትዮጵያ መንግሥት ዘመናዊ መሣሪያዎችን ለመግዛት በነፍስ ወከፍ አንድ ብር ሕዝቡ እንዲያዋጣ የመንግሥት ሠራተኛም ከደመወዛቸው ሃያ በመቶ እንዲያዋጡ በማድረግ የተገኘውን ያህል ተሰብስቦና የሀገሪቱ ሀብት ተሟጦ ጥቂት የጦር መሣሪያ ግዢ መፈጸሙ ጣሊያኖችን ሳያስጋቸው አልቀረም። በተለይም አንዳንድ ዘመናዊ የሚሰኙ መሣሪያዎች ከቼኮስሎቫኪያ፣ ከቤልጅግና ከጀርመን በጂቡቲ በኩል አዲስ አበባ ሲደርሱ ንጉሠ ነገሥቱ እራሳቸው ባቡር ጣቢያ በመሄድ የመጣውን መሣሪያ በጉጉት መመልከታቸው ጣሊያኖችን ሳያሸብር አልቀረም።

ዘመናዊ መሣሪያ ታጥቀው በዘመናዊ የጦር ስልት ይከላከላሉ ተብሎ ተስፋ የተጣለባቸው በሆለታ ገነት ጦር ትምህርት ቤት ገብተው የሰለጠኑ ጥቂት መኮንኖች ነበሩ። ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በተገኙበት መጋቢት 7 ቀን 1927 ዓ.ም በጃንሜዳ ሰልፍ ያሳዩት 3,000 የሚሆኑት እነዚያ መኮንኖችና ወታደሮች ነበሩ። ቢሆንም 40 ዓመታት ያህል ኢትዮጵያን ለመበቀል ተዘጋጅቶ የመጣውን የጣሊያን ሠራዊት የሚከላከል ሙሉ አቅም ነበረን ለማለት ያዳግታል። ለምሳሌ፣ መስከረም 23 ቀን 1928 ዓ.ም ጣሊያኖች የሰሜን ኢትዮጵያን ወሰን ጥሰው ሲገቡ አገራችን አንድም የመከላከያ ኃይል በአካባቢው ዘርግታ የመከላከል ተግባር ለመፈጸም አልቻለችም ነበር።

በኦጋዴንና በደቡብ ኢትዮጵያ በኩል ጣሊያኖች ኢትዮጵያን ለመውረር የቀየሱት እቅድ የሚላን ፕላን በመባል ይታወቃል። እቅዱ በሦስት የተከፈለና ምዕራብ መሐልና ምሥራቅን ያካለለ የጦር እቅድ ነበር። የመጀመሪያው የምዕራብ ጦር ግምባር የሚባለው የጠረፍ ከተማ የሆኑትን ዶሎንና አካባቢዋን ለመያዝ የተንቀሳቀው ነበር። የዚህ ጦር አዛዥ ኮሎኔል ሚሼሊ ይባላል። የሚሼሊ ጦር ጥቅምት 11 ቀን 1928 ዓ.ም በቀኑ 11፡00 ሰዓት ላይ ጦርነት ከፍቶ ወዲያውኑ ጣሊያኖች አካባቢውን በቁጥጥራቸው ሥር አዋሉት።

ይህ ጦርነት ሲከፈት ግራዝማች መኩሪያ ተሰማ የተባሉት የጠረፍ ጥበቃው አዛዥ በጀግንነት ተዋግተው ብዙ ቦታ ቆስለው እጄን ለጠላት አልሰጥም ብለው በጨካኙ የጠላት ጦር ተሰውተዋል። አካባቢውም በጣሊያኖች ቁጥር ሥር እንደዋለ የግራዝማች መኩሪያን ጀግንነት ጠላትም ስለተገነዘበ በክብር እንዲቀበሩ አድርጓል።

ሁለተኛው ዕቅድ በመሐል ግንባር ተሰልፎ የሚጠባበቅን ጦር በማሰማራት የዋቢ ሸበሌን ሜዳማ መሬት ለመያዝ ነበር። ይህም በጄኔራል ፍሩሽ የሚመራው ጦር ነበር። የጣሊያኑ ጦር በጦር አውሮፕላኖች እየተረዳ ጥቅምት 15 ቀን 1928 ዓ.ም ቀላፎን ሺላቦን ለመያዝ ቻለ። በኢትዮጵያ በኩል የጠረፍ ጦር አዛዥ የነበሩት ግራዝማች በላቸው የተባሉ ጀግና እጃቸውን ሳይሰጡ በጀግንነት ተዋግተው በጨካኙ የጠላት ጦር ተሰውተዋል። ሦስተኛው የጦር እቅድ በምሥራቅ በኩል የተሰማራው የጣሊያን ጦር የሚመራው በኮሎኔል ማሊቲ ነበር። በኢትዮጵያ በኩል ቆራሄንና አካባቢውን በአስተዳዳሪነትና በጠረፍ ጠባቂነት የተመደቡት ግራዝማች አፈወርቅ ወልደ ሰማያት ነበሩ። ምሽጋቸው ዘመናዊ ነው ባይባልም ከአውሮፕላን ለሚዘንበው ቦምብ ግን በቂ መከላከያ ነበር ተብሎ በታሪክ ተጠቅሷል።

የመሐሉንና የሌላውን ክፍል የጠላት ወረራ በዝርዝር ለመዘከር ገጹ ስለሚወስነን ለማሳየት የተሞከረው ጥቂቱን ታሪክ ብቻ ለማስታወስ ነው። ጀግኖቹ አርበኞቻችንና ሕዝቡ በምድር በዘመናዊ መሣሪያዎች እየወደቀ፣ በሰማይ በሚዘንብበት የመርዝ ጋዝ እየተንገበገበ በከፈለው መስዋዕትነት ነው ኢትዮጵያ በፋሽስት ወራሪዎች ላይ ድል ተቀዳጅታ አኩሪ ታሪክ ያስመዘገበችው። እናም ሚያዝያ 27ን የድል ቀን ብላ የምታከብረው። ሰላም!

# ተናጋሪው ዶሴ

## በመርከብ የተጫነ እቃ መጥፋትና መጉደል ያስከተለው ውዝግብ

ክፍለዮሐንስ አንበርብር

የሰነድ መለያ ቁጥር 98358 የሰጠው ፋይል ጥር 05 ቀን 2007 ዓ.ም አምስት ዳኞች ከመንበሩ ተሰይመው የመጨረሻውን ውሳኔ ይሰጣሉ:: የአመልካቹ አንበሳ ኢንሹራንስ ኩባንያ ነገረ ፈጅ በአካል የቀረቡ ሲሆን፤ ተጠሪው የኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ አገልግሎት ድርጅት ጠበቃም እንዲሁ ከችሎት ግራ ቀኝ ቆመው የመጨረሻ የፍርድ ውሳኔ ሊሰሙ ነው:: የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ውሣኔዎች በሚለውና ጥቅምት 13 ቀን 2008 ዓ.ም በቅፅ 17 የጠቅላይ ፍርድ ቤት የጥናትና ህግ ድጋፍ ዳይሬክቶሬትም ይህን ጉዳይ እንዲህ ሲል ለማስተማሪያነት ከትቦታል::

### የክሱ ይዘት

የመድን ውልን መሠረት አድርጎ የቀረበውን የገንዘብ ይተካልኝ ጥያቄ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ ነው:: አመልካች ለደንበኛው ለነፃ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ከቱርክ አገር ለሚያስመጣቸው 246 ጥቅል ብረቶች ከተጫኑበት አገር ተጓጉዞ እስኪመጣ ድረስ ለሚያጋጥም ጉዳት በፖሊሲ ውል ቁጥር 01/ኤም አር ኦኤ/00001/07 የባህር ላይ የጉዞ መድን ሽፋን መስጠቱን፤ ተጠሪ የመድን ሽፋን የተሰጣቸውን 246 ጥቅል ብረቶችን ተረክቦ ሆውማ ቤሊ ቪ.ኢኤስቲአር53 በሚባለው መርከብ ከሊአጋ ኢዝሚር ቱርክ አጓጉዞ ጅቡቲ ለማድረስ በባህር እቃ መጫኛ ሰነድ ቁጥር 305/ኤስሲ ግዴታ መግባቱን፤ ተጠሪ ጅቡቲ ለማድረስ ግዴታ ከገባባቸው 246 ጥቅል ብረቶች ውስጥ እቃው ጅቡቲ ወደብ ደርሶ ሲራገፍ 11(አስራ አንድ) ጥቅል ብረቶች መጥፋታቸውን፤ ከተጓጓዘው 246 ጥቅል ብረቶች ውስጥ የአመልካች ደንበኛ በ11/04/2004 ዓ/ም 226 ጥቅል አዲስ አበባ ላይ በእቃ መረከቢያ ሰነድ ቁጥር 10431 መረከቡን፣ ቀሪው 20 ጥቅል ብረት ውስጥ ዘጠኝ ጥቅል ደግሞ ዘግይቶ በ05/06/2004 ዓ/ም በእቃ መረከቢያ ሰነድ ቁጥር 10999 መረከቡን ነው::

ይህ የተጫነ እቃ መጥፋትና መጉደሉ በጅቡቲ የሰርቬየር ስራ በሚሰራው ገልፍ ኤጀንሲ አገልግሎት የሚባል ሰኔ 24 ቀን 2004 ዓ.ም ማረጋገጡን ገልጾ አመልካች ለደንበኛው የከፈለውን ካሳ ብር 289 ሚሊዮን 527ሺ ተጠሪ እንዲተካለት ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው::

### የተጠሪው ምላሽ

የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን ያስቀደመ ሲሆን በዚህም መሰረት የአመልካች ክስ እቃው በጅቡቲ ወደብ ላይ መራገፉ ከተረጋገጠበት ከጳጉሜ 03 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ በሚታሰብ በአንድ ዓመት ይርጋ ጊዜ ውስጥ የሚታገድ መሆኑን የባህር ሕግ ቁጥር 203(1) ድንጋጌ እንደሚያሳይ እንዲሁም አመልካች ክስ ለማቅረብ መብት ወይም ጥቅም የሌለው መሆኑን ገልፆ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል::

### ሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ እና የአመልካች አቤቱታ

የስር ፍርድ ቤትም በዚህ መልክ የቀረበውን የይርጋ ክርክር በጭብጥነት ይዞ ጉዳዩን በመመርመር እቃው በጅቡቲ ወደብ የተራገፈው ጳጉሜ 03 ቀን 2003 ዓ.ም መሆኑን መነሻ አድርጎ ይርጋውን በመቁጠር የካቲት 05 ቀን 2005 ዓ.ም የቀረበው የአመልካች ክስ በባህር ሕግ ቁጥር 203(1) መሰረት በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ያልቀረበ በመሆኑ በይርጋ የታገደ ነው በማለት መዝገቡን ይዘጋዋል::

ታዲያ በዚህ ብይን የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም:: የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ብይን በመቃወም ለማስቀየር ነው::

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ይዘት ደግሞ የመጨረሻ ርክክብ የተደረገው የካቲት 05 ቀን 2004 ዓ.ም ሁኖ እያለና የደንበኛው እቃ መጉደሉም የተገለጸው ሰኔ 24 ቀን 2004 ዓ.ም ሁኖ እያለ የእቃው ርክክብ ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ይርጋው ሊቆጠር ይገባል ተብሎ የአመልካች ክስ ውድቅ መደረጉ ያላግባብ ነው የሚል ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት ሊታይ ይገባዋል ተብሎ ተጠሪ ቀርቦ ግራ ቀኙ በፅሁፍ እንዲከራከሩ ተደረገ::

> ግራ ቀኙን እያከራከረ ያለው ጉዳይ በባህር ህጉ ቁጥር 203(1) የተመለከተው የአንድ ዓመት የይርጋው ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው ከመቼ ጀምሮ ነው የሚለው ነው:: አመልካች የበታች ፍርድ ቤቶች የይርጋ ጊዜ አቆጣጠር ስህተት ነው በማለት የሚከራከረው የእቃዎቹ ርክክብ ጊዜ በማስጫኛ ውሉ ላይ አልተገለፀም

### የችሎት የምርምራ ውጤት

ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል:: እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው ነጥብ የአመልካች ክስ በይርጋ የታገደ ነው ተብሎ ውድቅ መደረጉ ባግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነው::

አመልካች በተጠሪ ላይ ክስ ሊመስርት የቻለው ለደንበኛው ለነፃ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ከቱርክ አገር ለሚያስመጣቸው 246 ጥቅል ብረቶች ከተጫኑበት አገር ተጓጉዞ እስኪመጣ ድረስ ለሚያጋጥም ጉዳት በፖሊሲ ውል ቁጥር 01/ኤም አር ኦኤ/00001/07 የባህር ላይ የጉዞ መድን ሽፋን መስጠቱን መሰረት አድርጎ ነው::

በዚህ ጉዞ ሂደት ጠፉ ለተባሉት 11 ጥቅል ብረቶች ለደንበኛው ከፈልኩ የሚለውን ገንዘብ እቃዎቹን የማጓጓዝ ግዴታ አለበት የሚለው ተጠሪ እንዲተካለት ነው:: ስለሆነም ለጉዳዩ ቀጥተኛ አግባብነት ያለው ሕግ የባህር ህግ ሲሆን፤ ለተያዘው ጉዳይ ተፈፃሚነት ያለውን የይርጋ ጊዜ የሚያስቀምጠው የህጉ ድንጋጌ ቁጥር 203 ነው:: ድንጋጌው ሁለት ንዑስ ቁጥሮችን የያዘ ሆኖ የመጀመሪያው ንዑስ ቁጥር ከማመላለሻው ውል ውስጥ የተገኙ መብቶች በይርጋ የሚታገዱት የንግድ እቃውን ከተረከበበት ቀን ጀምሮ ወይም የማስረከቡ ጉዳይ ሳይፈፀም ቀርቶ እንደሆነ እቃውን ማስረከብ ከሚገባበት ቀን አንስቶ የአንድ ዓመት ጊዜ ካለፈ በኋላ ነው በማለት አስገዳጅነት ባለው ሁኔታ አስቀምጧል:: ቁጥር 203 ንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ ደግሞ ከሂሳብ አከፋፋል ጋር ተያይዞ የሚነሳው ክርክር የሚታገድበትን አግባብ የሚያስቀምጥ ነው::

የባህር ህግ ቁጥር 203 ድንጋጌ የሚገኘው በጭነት ማስታወቂያ የተረጋገጠ ደረሰኝ የማመላለሻ ውልን የሚመለከቱ ልዩ ድንጋጌዎች በሚገዛው ክፍል ነው:: የድንጋጌዎችን ወሰን በተመለከተ በቁጥር 180 ስር ሕግ አውጪ አስቀምጧል:: ይህ ድንጋጌ በንዑስ ቁጥር አንድ ስር በክፍሉ ላይ የተመለከቱት ድንጋጌዎች የሚፀኑት በተለይ በመርከብ ላይ በተጫኑት የንግድ እቃዎች የጭነት ማስታወቂያ ደረሰኝ ወይም ይህን በመሰለ ሌላ አይነት ሰነድ በተረጋገጡ የጭነት ማመላለሻ ውሎች ላይ ብቻ መሆኑን ሲያስቀምጥ የድንጋጌው ንዑስ ቁጥር ሁለት እና ሶስት ደንጋጌዎች ደግሞ እንደቅደም ተከተላቸው የመርከብ መከራየት ውል ሰነድ ባለው ጉዳይ ላይ ተፈፃሚ ሊሆኑ አይችሉም:: በዚህ ጊዜም ድንጋጌዎቹ ተፈፃሚ ሊሆኑ የሚችሉበትን ልዩ ሁኔታዎችን የሚያስቀምጡ ናቸው::

ይህ የህግ ክፍል የተመለከተው ችሎቱ፤ ተጠሪ ጅቡቲ ለማድረስ ግዴታ ከገባባቸው 246 ጥቅል ብረቶች ውስጥ እቃው ጅቡቲ ወደብ ደርሶ የተራገፈው ጳጉሜ 03 ቀን 2003 ዓ.ም ሁኖ በዚህ ጊዜ ከተጓጓዘው 246 ጥቅል ብረቶች ውስጥ የአመልካች ደንበኛ በ11/04/2004 ዓ/ም 226 ጥቅል አዲስ አበባ ላይ በእቃ መረከቢያ ሰነድ ቁጥር 10431 መረከቡን፣ ቀሪው 20 ጥቅል ብረት ውስጥ ዘጠኝ ጥቅል ደግሞ ዘግይቶ በ05/06/2004 ዓ.ም በእቃ መረከቢያ ሰነድ ቁጥር 10999 መረከቡን፣ ይህ የተጫነ እቃ መጥፋትና መጉደሉ በጅቡቲ የሰርቬየር ስራ በሚሰራው ገልፍ ኤጀንሲ አገልግሎት የሚባል ሰኔ 24 ቀን 2004 ዓ.ም ማረጋገጡንና አመልካች ክስ የመሰረተው የካቲት 05 ቀን 2005 መሆኑን የክርክሩ ሂደት ያሳያል::

ግራ ቀኙን እያከራከረ ያለው ጉዳይ በባህር ህጉ ቁጥር 203(1) የተመለከተው የአንድ ዓመት የይርጋው ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው ከመቼ ጀምሮ ነው የሚለው ነው:: አመልካች የበታች ፍርድ ቤቶች የይርጋ ጊዜ አቆጣጠር ስህተት ነው በማለት የሚከራከረው የእቃዎቹ ርክክብ ጊዜ በማስጫኛ ውሉ ላይ አልተገለፀም:: በመጀመሪያው ዙር 226፣ ቀጥሎ ደግሞ ዘጠኝ ጥቅል ብረቶች የተላኩ መሆኑንና ለክሱ መነሻ የሆኑት ቀሪዎቹ 11 ጥቅል ብረቶች መጥፋታቸው የተረጋገጠው ሰኔ 24 ቀን 2004 ዓ.ም ነው በሚል ነው::

ከክርክሩ መረዳት የሚቻለው እቃው በባህር ላይ ተጉዞ ጅቡቲ የተራገፈበት አግባብ በአንድ የማስጫኛ ሰነድ ያለመሆኑን ነው:: በአንድ የማስጫኛ ሰነድ እቃዎቹን ተጠሪ ባልተረከበበት ሁኔታ የመጀመሪያው የማራገፊያ ቀን ማለትም ጳጉሜ 03 ቀን 2003 ዓ.ም ከይርጋው መቆጠር መነሻ ቀን የሚሆንበት አግባብ የለም:: እንዲሁም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የመጀመሪያ የርክክብ ቀን የሆነው ታህሳስ 11 ቀን 2004 ዓ.ም ለይርጋው መነሻ ተደርጎ ሊወሰድ ይገባል ማለቱ እቃው በሙሉ አንድ አይነት፣ በአንድ የጭነት ሰነድ በአንድ የማጓጓዣ ውል የተጓጓዘ መሆኑን ከክሱ መረዳት ይቻላል በሚል ነው:: ይሁን እንጂ ከዚሁ ከመጀመሪያው ርክክብ በኋላ ዘጠኝ ጥቅል ብረትን የአመልካች ደንበኛ የካቲት 05 ቀን 2004 ዓ.ም መረከቡ አይካድም፡

ስለሆነም ርክክቡ የቆመው ከዚህ ከየካቲት 05 ቀን 2004 ዓ.ም በኋላ በመሆኑ የአመልካች ደንበኛ እቃዎቹ መጥፋታቸውን እርግጠኛ ሊሆኑ ይችላሉ ተብሎ የሚታሰበው ከዚህ ቀን በኋላ እንጂ የመጀመሪያው ርክክብ ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ አይደለም::

ተጠሪው የባህር ህግ ቁጥር 180(2) ድንጋጌን መሰረት አድርጎ የሚያቀርበው ክርክርም እቃዎቹ ከመርከቡ ላይ ከተጫኑበት አንስቶ አስከሚራገፉበት ጊዜ ብቻ የባህር ህግ ቁጥር 203 ድንጋጌ ተፈፃሚ መሆኑን የሚያስቀምጥ ሲሆን ይህም እቃዎቹ ሙሉ በሙሉ ተጭነው ባልተቆራረጠ ሁኔታ ርክክቡ የሚፈፀምበትን አግባብ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የተቀመጠ ድንጋጌ ነው ከሚባል በስተቀር በመርከብ ላይ የተጫኑት እቃዎች በተግባር በተለያዩ ጊዜያት እየተራገፉ ርክክቡም በተለያዩ ጊዜያት ሲደረግ የነበረበትን ሁኔታ ለመግዛት ታስቦ የተቀመጠ ነው ለማለት የሚቻል አይደለም:: የአመልካች ደንበኛ እቃዎቹን በተለያዩ ጊዜያት ሲረከቡ የነበሩ መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ከተረጋገጠ እቃዎቹ የተራገፉበትን ቀን ወይም የመጀመሪያ ርክክብ የተደረገበትን ቀን መነሻ አድርጎ ክሳቸው በይርጋ እንዲታገድ ማድረግ ከይርጋ ፅንሰ ሃሳብም ውጪ መሆኑ የሚታመን ነው ይላል::

በባህር ህግ ቁጥር 162 ድንጋጌ፣ የይርጋ አቆጣጠር ጊዜ የሚጀምርበትን አግባብ ያስቀመጠ ሲሆን፤ ለተያዘው ጉዳይ ግን ድንጋጌው ሙሉ በሙሉ አግባብነት አለው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም:: ምክንያቱም ድንጋጌው በንዑስ ቁጥር አንድ ስር ለመጫን ወይም ለማራገፍ የተወሰነው ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው ካፒቴኑ መርከቡን ሊጫን ወይም ሊራገፍ ተዘጋጅቷል ብሎ ካስታወቀበት ጊዜ ጀምሮ መሆኑን ያስቀምጣል:: የድንጋጌው ንዑስ ቁጥር ሁለት ደግሞ ጊዜም የሚታሰበው ካፒቴኑ ማስታወቂያውን ሰጥቶ ስራው ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ መሆኑን ያሳያል:: በሌላ አገላለፅ ይህ ድንጋጌ ተፈጻሚ የሚሆነው የመጫኛና የማራገፊያ ጊዜ የሚጀምርበት ጊዜ በግልጽ በታወቀበት ሁኔታ ነው እንጂ እቃዎቹ በተለያዩ ጊዜያት በተጫኑበትና በተራገፉበት ግንኙነት ውስጥ አይደለም ሲል ያትታል:: የአመልካች ደንበኛ እቃዎች ሙሉ በሙሉ የተጫኑበት ቀንም ሆነ የሚራገፉበት ቀን ያለመታወቁን የክርክሩ ሂደት ያሳያል::

አመልካች መብቱን ማስከበር የሚችልበት ጊዜ የካቲት 05 ቀን 2004 ዓ.ም ከተባለ ይኼው ጊዜ በፍትቤሄር ቁጥር 1848(1) ድንጋጌ መሰረት ግንዛቤ ውስጥ ገብቶ በባህር ህጉ አንቀጽ 203(1) የተቀመጠው የአንድ ዓመት ጊዜ የሚያበቃው ከየካቲት 06 ቀን 2005 ዓ.ም ጀምሮ ሲሆን፤ አመልካች ግን ይኼው ጊዜ ከማለፉ በፊት የካቲት 05 ቀን 2005 ዓ.ም ክሱን ያቀረበ በመሆኑ ክሱ በይርጋ የሚታገድ አይደለም::

ሲጠቃለልም የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካች ክስ በአንድ ዓመት ይርጋ የሚታገድ ነው በማለት የሰጡት ብይን ተገቢውን የይርጋ መቁጠሪያ ጊዜ መነሻ ያላደረገ ከመሆኑም በላይ የባህር ህግ ቁጥር 162 ድንጋጌን ይዘቱንና መንፈሱን ከተያዘው ጉዳይ ልዩ ባህርይ ጋር ባላገናዘበ መልኩ በመሆኑ ብይኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ሲል ፍርድ ቤቱ የመጨረሻ የምርመራ ውጤቱን ሰጥቷል፤ ተከታዩን ውሳኔም አሳልፏል::

### ውሳኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመለያ ቁጥር 203024 ግንቦት 06 ቀን 2005 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመመለያ ቁጥር 137802 ታህሳስ 08 ቀን 2006 ዓ.ም በትዕዛዝ የፀናው ብይን በፍትሐብሄር ሥነ ስርዓት ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የአመልካች ክስ በይርጋ የታገደ አይደለም፡፡
3. የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክርክሩን በመመለያ ቁጥር 203024 ቀጥሎ በሌሎች የግራ ቀኙ የክርክር ነጥቦች ተገቢውን የክርክር አመራር ስርዓት ተከትሎ ተገቢውን ዳኝነት እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341(1) መሰረት ተመልሶ ተልኳል፡፡

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

## ትምህርት ሸቀጥ ወይስ ማኅበራዊ ኃላፊነት?

ቦጋለ አበበ

የትምህርት ጉዳይ ከአንድ ማኅበረሰብ አልፎ ለአገር ያለውን ጥቅም ማብራራት ለቀባሪው የማርዳት ያህል ነው። የትምህርት ጉዳይ በተለይም በዚህ ዘመን የእያንዳንዱን ቤት የሚያንኳኳ እንደመሆኑ ማንም በቀላሉ የሚመለከተው አይደለም። በዚህ ዘመን ተፈጥሮ ፊደል አለመቁጠር ወይም ከቶ አለመማር የሚቻል አይደለም። ከሌላው ዓለም ጋር እኩል መራመድ ቢከብድ እንኳን ሰፊ ልዩነት እንዳይኖርና የእውቀት ክፍተት እንዳይፈጠር ትውልድ የግድ መማር አለበት። ይህ ደግሞ ከግለሰብ ወይም ከማኅበረሰብ አልፎ በአገር ላይ ያለው ተፅዕኖ እንዲህ በቀላሉ የሚገለፅ እንዳልሆነ ለማንም የተደበቀ አይደለም።

ትምህርትን ለሁሉም የማዳረስ ጉዳይ በተለይም እንደ አዲስ አበባ ባሉ ትልልቅ የሀገራችን ከተሞች በመንግሥት ብቻ የሚሸፈን አለመሆኑ አያከራክርም። ስለዚህም በርካታ የግል ትምህርት ቤቶች ተፈጥረዋል። ቀላል የማይባል የማኅበረሰብ ክፍልም ባለው አቅም ላይ ተመሥርቶ ወዶም ይሁን ተገዶ ልጁን ወደ ግል ትምህርት ቤት ይልካል። የግል ትምህርት ቤቶች ሲነሱ ግን ሁሌም ከክፍያ ጋር በተያያዘ የሚማረረው የማኅበረሰብ ክፍል ጥቂት አይደለም። ባለፉት ጥቂት ዓመታት መንግሥት የግል ትምህርት ቤቶች ክፍያ እንዳይጨምሩ ያወጣውን መመሪያ ተከትሎ እፎይ ብሎ የነበረው ሕዝብ አሁን ወደ ምሬቱ ተመልሷል።

የዘንድሮው የትምህርት ዘመን ተገባዶ መጪውን የትምህርት ዘመን በመጠባበቅ ላይ በምንገኝበት በዚህ ወቅት ከሰሞኑ ከትምህርት ቤት ክፍያ ጭማሪ ጋር በተያያዘ አስደንጋጭ ነገር ያልሰማ የለም።

**አንድ ግለሰብ በግሉም ይሁን ከሌሎች ጋር ተጣምሮ በአክሲዮን ትምህርት ቤት ሲከፍት መጀመሪያ ዓላማው ግልፅ መሆን አለበት**

በርካታ የግል ትምህርት ቤቶች ሰሞኑን በግላቸውም ከወላጅም ጋር ተሰብስበው ነበር። በዚህ ስብሰባም ላይ በመጪው የትምህርት ዘመን ክፍያ ላይ የሚደረገው ጭማሪ አስደንጋጭና ብዙዎችን ያሳሰበ ነው። ሁሉም የግል ትምህርት ቤቶች ማለት ይቻላል በመጪው የትምህርት ዘመን ቢያንስ መቶ በመቶ ጭማሪ ለማድረግ እንዳሰቡ ወይም እንደወሰኑ ተሰምቷል። ሁለት መቶ ፐርሰንት ለመጨመር የተዘጋጀም አለ። ይህን ለማድረግ የተዘጋጁትም ባለፉት ጥቂት ዓመታት ትምህርት ቤቶቹ ክፍያ ላይ ጭማሪ ባለማድረጋቸው በቀጣይ ከወላጅ ጋር ተወያይተው እስከ ሁለት መቶ ፐርሰንት እንዲጨምሩ መንግሥት ይሁንታ እንደሰጣቸው በማስረዳት ነው።

ካለው የኑሮ ውድነት አንፃር ትምህርት ቤቶች የክፍያ ጭማሪ አያድርጉ ማለት ይከብዳል:: ጥያቄው ክፍያ ላይ ጭማሪ ለማድረግ ትክክለኛው ጊዜ አሁን ነው የሚለው ነው:: በኑሮ ውድነት የተነሳ ያልጨመረ ሸቀጥ ያልጋሸበ የአገልግሎት ክፍያ የለም:: ይህም እንኳን ዝቅተኛ የኑሮ ሁኔታ ላይ የሚገኘውን ማኅበረሰብ መካከለኛ ገቢ አለው ተብሎ የሚታሰበውንም እጅ ከወርች አስሮት ይገኛል:: አስቡት በዚህ የኑሮ ውድነት የተማረረ ማህበረሰብ ላይ ሁለት መቶ ፐርሰንት የትምህርት ክፍያ ሲጨመርበት:: እሺ ትምህርት ቤቶች ክፍያ ላይ የግድ መጨመር ካለባቸውስ በዚህ መልኩ የተጋነነ ጭማሪ ማድረግ ተገቢ ነው?::

የትምህርት ቁሳቁሶች መወደድ ጭማሪ ለማድረግ አንድ ምክንያት ነው ብለን እናስብ፣ መምህራንም እዚህ ግባ በማይባል ደመወዝ የኑሮ ውድነቱ ሰለባ በመሆናቸው የደመወዝ ማሻሻያ እንዲደረግላቸው ጭማሪ ማድረጉ የግድ ነው ብለንም በቅንነት ካሰብን ጭማሪው ምክንያታዊ ሊሆን ይችላል:: ያም ሆኖ ቢያንስ ሃምሳ በመቶ ጭማሪ ማድረግ ሲቻል እስከ ሁለት መቶ በመቶ ጭማሪ ማድረግ ትምህርትን እንደ አንድ ማኅበራዊ ኃላፊነት ከመቁጠር ይልቅ ሸቀጥ ማድረግ ይሆናል::

ይህ አይነት የተጋነነ ጭማሪ የሚለውጠው ነገር አለመኖሩ ደግሞ ይበልጥ አሳሳቢ ነው:: ይህ በእጅጉ የጋሸበ ጭማሪ ዳፋው ወላጅን በማማረር ብቻ አይቆምም፣ ጭማሪው የሚደረግበት ወላጅ ምናልባትም ነጋዴ ሊሆን ይችላል:: የትምህርት ቤት ክፍያ ተጨምሮብኛል ብሎ እሱም በሚነግደው ሸቀጥ ወይም በሚሰጠው አገልግሎት ላይ ማካካሻ የመሰለውን ጭማሪ ያደርጋል:: ሌላውም በዚህ መንገድ ይቀጥላል:: በዚህም መምህራን ጭምር ተጎጂ እንጂ ተጠቃሚ ሊሆኑ አይችሉም:: ትምህርትም ትምህርት ቤቶቹም የሚኖሩት መምህራን ሲኖሩ ነው:: መምህራን ከሌሉ ሁሉም የለም:: ይህ ደግሞ እንደ ሀገር ትልቅ አዙሪት ውስጥ የሚከተን አደጋ ሊሆን ይችላል::

አንዳንዶቹ ትምህርት ቤቶች እስከ ሁለት መቶ በመቶ ጭማሪ ለማድረግ ያሰቡት ወላጅን ትምህርት ቤቱን ወደ ኢንተርናሽናል ደረጃ ለማሳደግ በማሰብ መሆኑን ሊያሳምኑ ሲሞክሩ ከማየት በላይ የሚያበሳጭ ነገር የለም:: ይህ ‹‹ዓይንህን ጨፍን ላሞኝህ›› የሚሉት አይነት ነው:: እውነት ለመናገር እንዲያው አንድ ትምህርት ቤት ሲያስተምርበት ከኖረው ሥርዓት ወጥቶ ድንገት ብድግ ብሎ ዛሬ ኢንተርናሽናል ላደርገው ስለሆነ ሁለት እጥፍ ጭማሪ አደርጋለሁ ማለት ቀልድ ነው:: አቅሙ ያለው ወላጅ እሺ ይሁን ብሎ ቢቀበል እንኳን ነገ የትምህርት ቤቱ ስያሜ ላይ ኢንተርናሽናል የሚል ቅፅል ከመጨመር የዘለለ ነገር እንደማይኖር ሁሉም ልቦናው ያውቀዋል::

አንድ ግለሰብ በግሉም ይሁን ከሌሎች ጋር ተጣምሮ በአክሲዮን ትምህርት ቤት ሲከፍት መጀመሪያ ዓላማው ግልፅ መሆን አለበት:: እኛ ጋር ግን ትምህርት ቤቶችን በሚከፍቱ ሰዎች ግልፅ የሆነ የግንዛቤ ወይም የአመለካከት ችግር አለ:: ትምህርት ቤት ንግድ አይደለም፣ እንደ ሸቀጥም የሚታይበት ዓለም የለም:: ትልቅ ትርፍ ለማጋበስ ተብሎም አይከፈትም:: ከዚያ ይልቅ ማኅበራዊ ኃላፊነት መሆኑን ስንቶቹ የትምህርት ቤት ባለቤቶች ያውቁታል?::

አሁን የታሰበው የተጋነነ ጭማሪ መልሱን በግልፅ ይነግረናል:: ሕዝብ በከፍተኛ የኑሮ ውድነት ፍዳውን እያየ በሚገኝበት ወቅት እስከ ሁለት መቶ ፐርሰንት ለመጨመር ማሰብ ማኅበራዊ ኃላፊነትን ወደ ጎን ትቶ እንደ ስግብግብ ነጋዴ ትርፍ ማግበስበስ ካልሆነ በቀር ሌላ ምን ሊባል ይችላል?::

# ዓለም አቀፍ



## አዲስ የተገኘው የአልዚመር በሽታ መድኃኒት ተስፋ ሰጪ ውጤት አሳየ

በጋዜጣው ሪፖርተር

በአብዛኛው ከእርጅና ጋር በተያያዘ የሚከሰተው አልዚመር የተባለው የአዕምሮ ጤና እክልን ለማከም የሚውል ሁለተኛው መድኃኒት ተስፋ ሰጪ ውጤት ማሳየቱ ተዘገበ።

የዚህ መድኃኒት ውጤታማነት እና እውን ለመሆን መቃረቡ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ለበሽታው መድኃኒት ማግኘት አስቸጋሪ ነው የሚለውን ግምት ይለውጠዋል ብለዋል ባለሙያዎች።

የመድኃኒቱ አምራች የሆነው ኤሊ ሊሊ እንዳለው፣ ዶናኔምባስ የተባለው ይህ የአልዚመር መድኃኒት የበሽታውን የመስፋፋት ፍጥነት በአንድ ሦስተኛ ያዘገየዋል።

መድኃኒቱ በሚሞከርበት ጊዜ ሁለት በጎ ፈቃደኞች እና አንድ ሦስተኛው ሕሙማን በአንጎላቸው ውስጥ ባጋጠማቸው አደገኛ እብጠት ምክንያት ለሞት መዳረጋቸው ተነግሯል።

“ለአስርታት የዘለቀው የአልዚመር በሽታን ለመቀየር የሚያስችል ሕክምና ለማግኘት የተደረገው ጥረት ለውጥ እያሳየ ነው” የሚሉት በዩናይትድ ኪንግደም የአንጎል ጤና ከፍተኛ ባለሙያ የሆኑት ዶክተር ኬት መመሪ፣ በዚህም ሳቢያ በሽታው ያለባቸው ሰዎችን እስከሞት ድረስ ከመንከባከብ ባሻገር፣ አሁን ለማከም እና ለመጠበቅ ዕድል ይፈጠራል ብለዋል።

የመድኃኒት አምራቹ ኤሊ ሊሊ ሙሉው የሙከራ ውጤቱ ያልታተመ ቢሆንም፣ ነገር ግን ይፋ የሆኑት ቁልፍ ግኝቶቹ እንዳመለከቱት፣ መድኃኒቱ በሕሙማን ጤና ላይ እና ሕይወት ዙሪያ ከፍተኛ ለውጥን አስገኝቷል።

መድኃኒት አምራቹ ኩባንያ በመጪዎቹ ጥቂት ወራት ውስጥ መድኃኒቱ በሆስፒታሎች ውስጥ ጥቅም ላይ እንዲውል የሚያስችለውን ፈቃድ ለማግኘት አስፈላጊውን ሂደት ይጀምራል።

የብሪስቶል ዩኒቨርስቲዋ ዶክተር ሊዝ ኩልትሃርድ እንዳሉት ምንም እንኳን መድኃኒቱን በተመለከተ የረጅም ጊዜ መረጃ ባይኖርም እንዲሁም “ጉልህ የጎንዮሽ ጉዳት” ቢኖረውም “በሽታው ያለባቸው ሰዎች ለረጅም ጊዜ የተሻለ ሕይወት እንዲኖራቸው ይረዳል።”

ይህ የአሁኑ የአልዚመር መድኃኒት ሁለተኛው ግኝት ሲሆን የበሽታውን ሂደት ለማዘግየት መቻሉ ሳይንቲስቶች ለዘመናት ያደረጉት ጥረት ለበሽታው መፍትሔ ለማግኘት በትክክለኛው መስመር ላይ እንዳደረሳቸው ማሳያ ነው ተብሏል።



## ዩክሬን በማዕከላዊ ኪዬቭ የራሷን ድሮን መትታ ጣለች

በጋዜጣው ሪፖርተር

የዩክሬን አየር ኃይል በማዕከላዊ ኪዬቭ ከቁጥጥር ውጭ ሆኗል ያለውን የራሱን ድሮን መትቶ መጣሉን ቢቢሲ ገለጸ፡፡

የአየር መከላከያ ኃይሉ ሐሙስ ምሽት በፕሬዚዳንቱ ጽሕፈት ቤት አቅራቢያ ድሮኑን መትቶ ለመጣል ሲሞክር ከ15 እስከ 20 ደቂቃ የቆዩ ፍንዳታዎች ተሰምተዋል።

የዩክሬን ፕሬዚዳንታዊ የሥራ ኃላፊ አንደሬይ ኢርማርክ መጀመሪያ ላይ ተመትቶ የተጣለው የጠላት ድሮን ነው ብለው ነበር።

ሆኖም በኋላ ላይ አየር ኃይሉ የዩክሬን ድሮን መሆኑን ያረጋገጠ ሲሆን፣ ተመትቶ የተጣለው “አላስፈላጊ ሁኔታዎችን” ለማስወገድ ነው ብሏል።

አየር ኃይሉ በመግለጫው እንዳለው ባራክታር ቲቢ2 ዩኤቪ (ሰው አልባ የአየር ላይ በራሪ ድሮን) በኪዬቭ ግዛት ውስጥ በታቀደለት በረራ ላይ መቆጣጠር ተስኖት ነበር።

በመሆኑም በዋና መዲናዋ ድሮኑ ከቁጥጥር ውጭ በመገኘቱ ሌላ ያልተጠበቀ ጉዳት ያስከትላል በሚል መትቶ ለመጣል ውሳኔ ላይ መደረሱንም ገልጿል።

በወደቀው ድሮን ምክንያትም የጠፋ የሰው ሕይወትም ሆነ የደረሰ ጉዳት የለም ብሏል መግለጫው።

“የሚያሳዝን ነው፤ ግን ቴክኖሎጂ ነው እንዲህ ዓይነት ክስተቶች ያጋጥማሉ” ያለው መግለጫው ድሮኑን መቆጣጠር ያልተቻለው ምናልባት በቴክኒክ ብልሽት ሊሆን እንደሚችል ጠቁሟል።

ድሮኑን መትቶ ለመጣል ሲደረግ የነበረውን ጥረት የሚያሳዩ ተንቀሳቃሽ ምስሎች በማኅበራዊ ሚዲያዎች ላይ በስፋት ተጋርተዋል።

ድሮኑ በመጨረሻም ሲወድቅ የደስታ ጩኸት ተሰምቷል።

የከተማዋ ጦር አስተዳደር ኃላፊ ስርሂይ ፖፐኮ፣ ድሮኑ በወደቀበት በከተማዋ የምዕራብ አካባቢ ሶሎምያንስኪይ በተባለው ስፍራ በነበረ ሕንጻ ላይ ሲወድቅ የተቀሰቀሰው እሳት በቁጥጥር ሥር መዋሉን ተናግረዋል።


ክስተቱ ያጋጠመው ረቡዕ ዕለት ዩክሬን በክሬሚሊን የድሮን ጥቃት ፈፅማለች ስትል ሩሲያ ከከሰሰች በኋላ ነው።

ሐሙስ ዕለት የክሬሚሊን ቃል አቀባይ ዲሚትሪ ፔስኮቭ፣ ያለ ምንም ጥርጥር አሜሪካ ከጥቃቱ ጀርባ አለችበት ብለዋል። ሆኖም ቃል አቀባዩ ለዚህ ንግግራቸው ያቀረቡት ማስረጃ የለም።

ዩክሬን በበኩሏ በክሬሚሊን በተፈፀመው ጥቃት እጇ እንደሌለበት ገልጻ፣ ሩሲያ ጦርነቱን ለማባባስ ራሷ የፈፀመችው ነው ስትል ከሳለች ።

# እንቅልፍን በቀላሉ ማሸነፍ

**አስናቀ ፀጋዬ**



ሁሉ ነገር ከልክ ሲያልፍ ልክ አይመጣም:: ከልክ በላይ ንግድ ትርፉ ኪሳራ ነው:: ከገደብ በላይ መመገብ ሲተፉ ማደር ነው:: ሁሉን ነገር ለማግኘት መስገብገብም «የቆጡን አውርድ ብላ የብብቷን ጣለች» እንደሚባለው ከሁለት ያጣ መሆን ነው:: ከመጠን በላይ መስራትም በጤና ላይ መፍረድ ነው:: ገደብ የለሽ ሀሳብ፣ ህልምና ጭንቀትም ጤናን ማቃወስ ነው:: ከመጠን በላይ እንቅልፍም በሽታ እንጂ ጤናማነት አይደለም::

በርግጥ እንቅልፍ ተፈጥሯዊ ነው:: የሰው ልጅ ካልተኛ የጤናማነት ስሜት አይሰማውም:: በስራውም ውጤታማ ሊሆን አይችልም:: ተሯሩጦ፣ ሰርቶና በልቶ የሚበቃውን ያህል እንቅልፍ መተኛት አለበት:: ችግሩ የሚመጣው ሀሳቡን ጥሎ አብዝቶ የተኛ እለት ነው:: አብዝቶ የሚተኛ ሰው ደግሞ ስለማይንቀሳቀስ ከሞተ ሰው ብዙም የሚለየው ነገር የለም::

በጠዋት የሚነሱ ሰዎች ያስቀናሉ:: የታደሉ ናቸው:: በህይወታቸው አስገራሚ ለውጦችን ያያሉ:: ሙሉ አእምሯቸውን መጠቀም ይችላሉ:: በራስ የመተማመን መንፈሳቸው ይጨምራል:: ለስራና ለትምህርት ያላቸው ሞራል ያድጋል:: ሙሉ ጉልበታቸውንም ይጠቀማሉ:: የቀዘቀዘ ሻይ የሚጠጡ ሰዎች ግን አርፍደው የሚነሱ እንቅልፋሞች ናቸው:: የህይወትንም ጣዕም አያውቁም:: አርፍደው የሚነሱ ሰዎች አንድ ሰሞን በጧት ሲነሱ «ለካ ያመለጠን ይሄ ነው» እንደሚሉ እርግጥ ነው:: ለመሆኑ ማልዶ መነሳትን እንዴት ቀላል ማድረግ ይቻላል?

ለማንኛውም ግን ሰበብ አታብዛ:: «ጧት ስነሳ ይደክመኛል፣ ማታ አርፍጄ ስለምተኛ እኮ ነው፣ ጧት ተነስቼስ ምን እሰራለሁ» የሚሉ ሰበቦችን አትደርድር:: መጀመሪያ ተነስ:: ከዛ አይምሮህ ምን መስራት እንዳለብህ፣ ምን ህይወትህን እንደሚቀይረው በማለዳ ሊነግርህ ይችላል:: ሰበበኛውን ቆፍረህ ቅበረው:: እሱ ነው ጠላትህ:: በጧት የማትነሳ ከሆነ ተመሳሳይ ነገር እያደረክ የተለየ ውጤት እንደሚጠብቅ አይነት ሰው ነህ:: ለሽሮ ብለህ እያዘጋጀህ ፓስታ ከጠበክ ሞኝ ነህ ማለት ነው:: በጧት መነሳት መጀመር አለብህ:: አዲስ ልማድ ነው:: ከትናንቱ ማንነትህ ጋር መፎካከር አለብህ:: ትናንት የተነሳኸው ከጥዋቱ አንድ ሰዓት ከሆነ ዛሬ አስራ ሁለት ሰዓት ተኩል መነሳት ይጠበቅብሃል:: ቀደም ማለት አለብህ:: ቀደም ስትል አዲስ ነገር እየሞከርክ ነው:: በህይወትህ አዲስ ነገር እየጠራህ ነው:: አዲስ ነገር ደግሞ መፈጠሩ አይቀርም:: ለምን ? በጥዋት እየተነሳህ ነዋ !

ይቅርብህ ለሚልህ ውስጣዊ ድምፅ ቦታ አትስጠው:: ስለዚህ ወዳጄ ምርጫው ያንተ ነው:: ወይ ተኝተህ ህልም ታልማለህ አልያ ደግሞ በጥዋት ተነስተህ ህልምህን ታሮጣለህ:: እጅህን ወደእሳትም ወደውሃም መጨመር ትችላለህ:: መብቱ አንተ ጋር ነው:: ተነስ ከተነሳህ! አለበለዚያ ተኛ! ህልምህም እዛው እንደተኛ ይጠብቅሃል:: በማለዳ ቀድማ የተነሳች ወፍ ትሉን ታገኛለች ይባላል:: አይህ መነሳት ያለብህ ወሳኙን የህይወት ምእራፍ ለማጣጣም ነው::

«ኸረ እኔ አርፋጅ ነኝ» እያልክ ይሆናል:: በእርግጠኝነት ዘመድ ልትሸኝ፣ ወይ ፈተና ሲኖርብህ አልያም ደግሞ ወሳኝ ጉዳይ ሲገጥምህ በጥዋት ተነስተህ ታውቃለህ:: ራስህን ለመለወጥ የሚያስገድድህ ቀን እስኪመጣ ለምን ትጠብቃለህ? አሁን ነቃ ብለህ ራስህን ጠይቀው:: ነገ ምንድን ነው የምሆነው?፣ ምን አይነት ዓለማዊና መንፈሳዊ ህይወት ነው የሚኖረኝ?፣ ከማን ጋር ነው የምኖረው?፣ ደስተኛ የምሆነው ምን ባሳካ ነው? ብለህ ራስህን ጠይቅ:: ፈጣሪህ ባንድም ሆነ በሌላ መልስ ይሰጥሃል:: መልሱ ግልፅ እስኪሆን ግን ነገን አስበህ ራስህን ሁሌ አሳድግ:: ገንዘብ አስቀምጥ:: መፅሃፍ አንብብ:: ተማር:: ራስህን አሳድግ:: የሚጠበቅብህን ነገር ሁሉ አድርግ:: ከሁሉ በላይ በጥዋት ተነሳ::

ስንፍናህን ቆፍረህ ቅበረው:: የዚህ ዓለም ስኬት ለነቁ እንጂ ለተኙ አይደለም:: ለፈዘዙ አይደለም ለባነኑ እንጂ:: ለጧት አላርም ትሞላለህ:: ይጠራል፤ ስልክህ ይጮሃል:: ትባንናለህ:: አስር ደቂቃም ቢሆን ተኝቼ አርፍጄ ልነሳ ትላለህ:: ጊዜ ልትገዛ ትፈልጋለህ:: አስር ደቂቃ ህይወትህን የሚቀይረው ይመስል አስር ደቂቃ ትፈልጋለህ:: አስር ደቂቃ ምን ይጨምርልሃል? የአስር ደቂቃ ስፖርት ግን ትንፋሽህን ያስተካክለዋል:: የአስር ደቂቃ ንባብ መንፈስህን ያድሰዋል::

አየህ ምን ታደርጋለህ መሰለህ አስር ደቂቃ ዘግይተህ ተነስ የሚል ስሜት ሲሰማህ ከአንድ እስከ ሶስት ቁጠር:: ከዛ ብድግ ትላለህ:: ያኔ ማንነትህ ልዩ ይሆናል:: «እኔ እኮ ጀግና ነኝ በጥዋት ተነሳሁ፤ በምፈልገው ሰዓት ተነሳሁ» የሚል ስሜት ይሰማሃል:: አለበለዚያ ግን ብርድ እኮ ነው:: ትንሽ ጋደም ብትልስ፤ ትንሽ ብታርፍስ ለሚለው ስሜትህ ከታዘዝክና ከተኛህ የስሜትህ ባሪያ ትሆናለህ:: ህይወትህን አትቀይርም:: ለምን? ስሜትህን ማፈን አለብህ::

አንዳንዴ ህይወትህን ለመቀየር፤ ራስህን ለማሳደግ ከስሜትህ በላይ መሆን አለብህ:: ተኛ፤ አርፍድ ከሚለው ስሜትህ በላይ መሆን አለብህ:: ስለዚህ በህይወትህ ደስተኛ ለመሆን ሙሉ ኃላፊነት ውሰድ:: ታላቅነትህን ቀስቅሰው:: አስራ አንድ ሰዓት ተነስ:: ብዙ የምትሰራው ስራ አለ:: ስለነገ ማወቅ የሚፈልግ ሰው ዛሬን ይመልከት:: ነገ የት እንደምትደርስ የሚነግርህ የዛሬው ማንነትህ ነው:: አሁን ቀንህን በምድን ነው የምታሳልፈው? ምሽቱንስ በምን እያሳለፍክ ነው? ነገ መሆን የምትፈልገው ድንቅ ሰው እንደዚህ ነው ግዜውን የሚያጠፋው፤ እንደዚህ ነው ግዜውን የሚያሳልፈው ? መልሱን አንተ ታውቃለህ::

ታዲያ ወዳጄ አሁን ካልነቃህ መቼ ልትነቃ ነው? አሁን ካልተለወጥክ መቼ ልትለወጥ ነው? ግዜው እየሮጠ ነው:: ቆሞ አይጠብቅህ:: ላንተ ሲል አይዘገይ:: እሱ ይሮጣል:: አንተ ፈዘሃል:: ንቃ እንጂ! አንተ ግዜን ካከበርከው እርሱም ያከብርሃል:: ስለዚህ በጥዋት ተነሳ:: ግዜህን ተጠቀምበት:: ይህን እድል መቼም አታገኘውም:: ካረጀህ በኋላ ካሳካሃቸው ይልቅ ያጎደልካቸው ናቸው የሚቆጩህ:: ለምን ያኔ አልተነሳሁም ነበር ትላለህ:: አሁኑኑ ተነስ! በጥዋት ተነስ! በቃ ከማንም በፊት አንተ ነቅተሃል:: አንተ እየለፋህ ነው:: ህልምህን እያሮጥክ ነው፤ ነቅተሃል::

ከአልጋህ የምትነሳው ነገ ለልጆችህ የምትነግራቸውን ታሪክ ልትሰራ ነው:: ስንፍና እንዳይሰማህ ከፈለክ የምወዳቸው፤ የማከብራቸው ሰዎች እያዩኝ ቢሆንስ ብለህ አስብ:: ያኔ ትጠነክራለህ:: የምትሰምጠው ውሃ ውስጥ ስትገባ አይደለም:: ውሃ ውስጥ ገብተህ ከቀረህ ብቻ ነው:: ህይወትህ የሚበላሸው ስትሳሳትም አይደለም:: ለማስተካከል ምንም ካላደረክ ነው:: በምንም ሁኔታ ውስጥ ብትሆን ተስፋ ቆርጠህ ዛሬን ካላቆምክ ነገ ያንተ ነው:: እስከዛሬ ያልተነሳህባቸው ጧቶች ዛሬ ያለህበት አድርሰውሃል:: ከዚህ በኋላ የምትነሳቸው ጧቶች ከሰው በላይ፤ ከምኞትህ በላይ ያደርጉሃል::

አየህ ከስሜትህ በላይ መሆን አለብህ:: ጧት እንዳትነሳ የሚከለክልህ ድምፅ ካለ እንዳትሰማው:: ትነሳለህ:: አላርሙ ሳይጮህ አንተ ተነስተህ ፊትህን ታጥበህ ህልምህን እያሳደድክ ነው:: እንቅልፍህን እየተኛህ አይደለም:: ለምን? ለነገ ታሪክ እየሰራህ ነው:: ነገ ለልጆቼ የምነግራቸው ታሪክ አለኝ እያልክ ነው:: ስለዚህ በጥዋት ትነሳለህ:: ያውም አስራ አንድ ሰዓት::

አይምሮህ ምክንያት ነው የሚፈልገው እንጂ የሚነሳ ማንነት ነው ያለህ:: «ጥዋት ተነስቼ ስፖርት መስራት፤ ማንበብ አለብኝ፣ አዲስ ነገር መሞከር አለብኝ» ብለህ ምክንያት አስቀምጥ:: ምክንያት ሲኖርህ ማንም ሳይቀሰቅስህ ትነሳለህ:: በተለይ ትልቅ ህልምና ዓላማ ካለህ አላርሙን ሁሉ ትቀድመዋለህ:: ከዛ ምን አይነት ቀን ዕንደምታሳለፍ አስበው:: በጥዋት ተነስተህ ፈጣሪህን አመስግነህ፣ ሰላም የሚሰጥህን ነገር አንብበህ፣ ቀለል ያለ ስፖርት ሰርተህ፣ ሻወር ወስደህ፣ ቁርስህን ብልተህ ወደስራህ ወይም ወደ ትምህርትህ ስትገባ ምን አይነት ቀን እንደሚሆን አስበው እስኪ:: ማት ሁሉንም ችግር አድርገህ ልትተኛ ስትል የሚሰማህን ልዩ ስሜት አስበው እስኪ:: ምን አይነት ተአምረኛ ቀን አሳለፍኩ፣ ቀኔን አሸንፌያለሁ፣ ጀግና ነኝ ስትል አስበው::

ይሄ ቀን ሁሌ ቢሆን የት እንደምትደርስ፣ ምን አይነት ደስተኛ፣ ምን አይነት ስኬታማ ሰው እንደምትሆን፣ ምን አይነት አመስጋኝና ብርቱ ሰው እንደምትሆን አስበው እስኪ:: የምትተኛው ሲደክምህ አይደለም፤ የጀመርከውን ስትጨርስ እንጂ:: አየህ ሁሌም ቀኑ አልፎ ማታ ልትተኛ ስትልና ጠዋት ከእንቅልፍህ ስትነሳ ያመንክበትን ነገር እየሰራህ የሚያስደስትህን ኑሮ እየኖርክ እንደሆነ አስበህ ደስተኛ ከሆንክ በቃ ስኬታማ ነህ:: የስኬት ጥግ ደስተኛ መሆን ነው::

በየቀኑ የምትወስናቸው ትናንሽ ውሳኔዎች የነገን መድረሻህን ይወስኑታል:: ማንበብ ውሳኔ ነው፣ ስፖርት መስራት ውሳኔ ነው:: በጠዋት መነሳት ውሳኔ ነው:: ለህይወትህ ከሚጠቅሙ ሰዎች ጋር መዋል ውሳኔ ነው:: ተኝቶ መዋልም ውሳኔ ነው:: ብር ማጥፋትም ውሳኔ ነው:: ግዜ ማባከንም ውሳኔ ነው:: አንተ ነህ መወሰን የምትችለው:: አየህ ከወሰንክ በኋላ ግን ህይወትህን ይቆጣጠረዋል:: የነገህ መድረሻ ላይ እሱ ይወስንልሃል:: የቀለድከውና ያባከንከው ግዜ ነገ ብኩን ያደርግሃል:: ዋጋ የምትከፍለው ግን መጀመሪያ ላይ ነው::

በጥዋት መነሳቱ፣ ስፖርት መስራቱ፣ ማንበቡ፣ ማጥናቱ፣ ገንዘብ ማስቀመጡ ሌላውም ነገር የሚያስቸግርህ ስትጀምረው ነው:: አንተ ጀምረው! አዲሱ ማንነትህ ሲለምደው አቁም ብትባል እንኳን አታቆመውም:: ወዳጄ ! ጣእሙን የምታውቀው ስትቀምሰው ብቻ ነው:: ስለዚህ ቶሎ ብለህ ጀምረው:: ከዛ በኋላ የጣፈጠህን ነገር ትደጋግመዋለህ:: ህይወትህ ላይ ቶሎ ለውጥ ይሰጥሃል:: ትቀየራለህ:: ማንም አይደለም ያንተን ህይወት የሚቀይረው:: ልማድህ ነው የሚቀይርህ:: በጧት ተነስ!

ዓለም ያከበረቻቸው የቢዝነስ ሰዎች፣ የመዝናኛው ዓለም ኮኮቦችና የአገር መሪዎች ከሁሉ በላይ መንፈሳዊ ሰዎች ቀናቸውን የሚጀምሩት ከጥዋቱ አስራ አንድ ሰዓት ወይ ከዛ በፊት ነው:: ስለዚህ በህይወትህ የሆነ መቀየር የምትፈልገው ነገር ካለ በጧት የምትነሳበትን ሰዓት አሻሽል:: ሌላው ሲተኛ አንተ ተነስ:: አይምሮህን በትኩስ አቅሙ ሳትጠቀምበት ከቀረህ ከዛ በኋላ ባለው ሰዓት ምንም ብታደርግ ጉልበታም አትሆንም:: አቅም አይኖርህም:: ስለዚህ ተነስ:: ለማን ብለህ ነው የምትተኛው?

ለብዙዎች የማያደርጉትን ከባድ ነገር ካደረክ ህይወት ቀላል ትሆንልሃለች:: ስለዚህ ሌሎች ተኝተው ሲያረፍዱ አንተ ተነስ:: መክፈል ያለብህን ዋጋ ክፈል:: ጥቂቶች ብቻ ከሌላው ተለይተው ለምን ስኬታማ እንደሚሆኑ ታውቃለህ? ለግዜ ዋጋ ስለሚሰጡ ነው:: ግዜ ምን ያህል ልዩነት ፈጣሪ እንደሆነ ጠንቅቀው ያውቃሉ:: በቂ ግዜ እንደሌላቸው ከተሰማቸው በሌላ የሚጠፉትን ግዜ መስዋዕት ቢያደርጉም ግድ የላቸውም:: የጧት እንቅልፋቸውንም ቢሆን::

ባለህበት መራመድ ትፈልጋለህ? በርግጠኝነት አትፈልግም:: ስለዚህ በማለዳ ተነስ:: የሚጠበቅብህን ሁሉ አድርግ:: ተአምር የምትሰራው ራስህን አሳምነህ ከስሜትህ በላይ በመሆን ነው:: ስለዚህ ማንም ሳይቀሰቅስህ ራስህ ተነስ::

አስብ እንግዲህ ወዳጄ! ጠዋት ሁለት ሰዓት የሚነሳ ሰው አስራ አንድ ሰዓት ቢነሳ በቀን ውስጥ ሶስት ሰዓት ያተርፋል:: ዓመት ደግሞ ፤ ሺ ሰዓት ያተርፋል:: ያ ሰው ሃምሳ ዓመት ቢኖር ስድስት ዓመት አተረፈ ማለት ነው:: ስድስት ዓመት ከሚተኛ ይልቅ ስድስት ዓመት ህልሙን ቢያሮጥ ይሻለዋል:: ህይወቱን ይቀይራል:: እና ጎበዝ ምን ትጠብቃለህ ተነስ እንጂ!! ህይወትህን ትቀይራለህ ወዳጄ::

# በዲጂታል የክፍያ ዘዴ እንዴት በቀላሉ ነዳጅ መግዛት ይችላሉ?

CBE Birr

NEDAJ

## በሲቢኢ ብር ነዳጅ ለመቅዳት ምን ያስፈልጋል?

- የሲቢኢ ብር ደንበኛ መሆን
- በሲቢኢ ብር ሒሳብዎ ውስጥ በቂ ገንዘብ እንዲኖር ማድረግ
- የምስጢር ቁጥርዎን ማስታወስ (የምስጢር ቁጥርዎን ከረሱት ወደ ነፃ የስልክ መስመር 951 በመደወል ወይም ወደ ባንካችን ቅርንጫፍ በመምጣት ወይም የሲቢኢ ብር መተግበሪያን በመጠቀም መቀየር ይችላሉ)

## የሲቢኢ ብር አገልግሎት ተጠቃሚ ካልሆኑ

- መተግበሪያውን በማውረድ አልያም *847# በመደወል በራስዎ ይመዝገቡ
- በማንኛውም የባንኩ ቅርንጫፍ ወይም የሲቢኢ ብር ወኪል ዘንድ በመቅረብ የሲቢኢ ብር ሒሳብ ይክፈቱ

## ሲቢኢ ብር ላይ እንዴት ገንዘብ ማስተላለፍ ይችላሉ?

- በሞባይል ባንኪንግ ከመደበኛ የባንክ ሒሳብዎ ወደ ሲቢኢ ብር ማስተላለፍ ይችላሉ
- በማንኛውም የባንኩ ቅርንጫፍ ወይም ወኪል ዘንድ በመሄድ ወደ ሲቢኢ ብር ማስተላለፍ ይችላሉ

## ነዳጅ ማደያ ሲደርሱ ምን ማድረግ ይገባዎታል?

- የሲቢኢ ብር ስልክ ቁጥርዎን፣ የሰሌዳ ቁጥርዎን እና የገንዘብ መጠን ለነዳጅ ማደያ ሠራተኛው ያሳውቁ
- በስልክዎ የሲቢኢ ብር የምስጢር ቁጥርዎን እንዲያስገቡ የሚጠይቅ አጭር የጽሑፍ መልዕክት ይደርስዎታል
- የሚከፍሉትን የገንዘብ መጠኑን ትክክለኛነት ካረጋገጡ በኋላ የሲቢኢ ብር ምስጢር ቁጥርዎን ያስገቡ
- ክፍያውን እንደፈፀሙ፣ ወዲያውኑ የክፍያ ማረጋገጫ መልዕክት በስልክዎ ይደርስዎታል

Nedaj መተግበሪያውን ያውርዱ
አስፈላጊውን መረጃ በማስገባት ይመዝገቡ

መተግበሪያው ላይ "My Cars" የሚለውን ይምረጡ
የሠሌዳ ቁጥሮን በማስገባት መኪናዎን ይመዝግቡ

በመልዕክት የደረሰዎትን የነዳጅ ልዩ መለያ ቁጥር
በሁለት መንገድ ከባንክ ሒሳብዎ ጋር ያስተሳስራሉ

→ የCBE የሞባይል ባንኪንግ መተግበሪያን ወይም *889# በመጠቀም "Utilities" ወይም «ክፍያዎች» በሚለው ገፅ ስር የሚገኘውን የነዳጅ ሒሳብ ማስተሳሰሪያ (Nedaj Account Link) በመጠቀም የነዳጅ ልዩ መለያ ቁጥርዎን በማስገባት ከመረጡት መደበኛ የባንክ ሒሳብዎ ጋር ማስተሳሰር ይችላሉ

→ በማንኛውም የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቅርንጫፍ በመቅረብ የነዳጅ መተግበሪያዎን ከሒሳብዎ ጋር ማስተሳሰር ይችላሉ

**በCBEBirr እና Nedaj ተጠቅመው ነዳጅ ሲቀዱ**
**ምንም አይነት ተጨማሪ የአገልግሎት ክፍያ አይጠየቁም።**

## ይፍጠኑ! በማንኛውም ዓይነት ስልክ ነዳጅዎን በቀላሉ ይቅዱ!

*847#

GET IN ON Google Play

Download on the App Store

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ
Commercial Bank of Ethiopia

ኢኮኖሚ

# መሠረተ ልማት

## ለኮንስትራክሽን ዘርፍ እድገት ከፍተኛ ሚና እንደሚኖረው የታመነበት ‹‹ቢግ ፋይፍ›› ኤግዚቢሽን

**መሳኩ ሔርሴ**

ቢግ ፋይፍ በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና ያለው በግንባታ ዘርፍ ላይ ያተኮረ የንግድ ትርዒት ነው:: ይህ የንግድ ትርኢት በተለያዩ የዓለማችን ሃገራት ላይ መካሄድ ከጀመረ 40 ዓመታትን አስቆጥሯል፤ ከመቶ ሺህ በላይ ዓለም አቀፍ አቅራቢዎችንና ገዢዎችን በማገናኘት ለንግድ ሥራ ትስስር ድልድይ ከመሆኑም በላይ ለዘርፉ ባለሙያዎች ትምህርታዊ መድረኮችን በማዘጋጀት በርካታ ባለሙያዎችን ማሰልጠኑን መረጃዎች ያመለክታሉ:: በዚህም ዓለማችን ካሏት ታላላቅ እና ተፈላጊ የግንባታ ዘርፍ የንግድ ትርዒቶች ውስጥ በመሪነት ደረጃ ለመቀመጥ ችሏል።

ቢግ ፋይፍ ዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒት በዱባይ ከሚያካሂደው የንግድ ትርዒት በተጨማሪ በሳዑዲ ዓረቢያ፣ ካታር፣ ናይጄሪያ፣ ግብፅ፣ ኬንያ እንዲሁም በደቡብ አፍሪካ ውስጥ ቢግ ፋይፍ ብራንድ የንግድ ትርዒቶችን በየዓመቱ ያሰናዳል::

ኢትዮጵያም ይህን ዓለም አቀፍ ኩነት ለማዘጋጀት በአፍሪካ አምስተኛ ሀገር ሆና ተመርጣለች። የዚህ ንግድ ትርዒት አዘጋጅ ዲኤምጂ ኢቨንትስ የተባለ ዓለም አቀፍ ተቋም ሲሆን፣ የቢግ ፋይፍ ብራንድን በኢትዮጵያ ለማዘጋጀት ከሀገር በቀሉ ኢትኤል ኢቨንትስ ጋር በመተባበር ከግንቦት 10 እስከ 12 ቀን 2015 ዓ.ም ‹‹አዲስ ቢዩልድ ባይ ዘ ቢግ ፋይፍ ኮንስትራክት ኢትዮጵያ›› በሚል ስያሜ ይህን የንግድ ትርዒት በሚሊንየም አዳራሽ እንደሚያቀርብ ይጠበቃል::

ኤግዚቢሽኑን አስመልክቶ ጋዜጣዊ መግለጫ በተሰጠበት ወቅት እንደተገለጸው፤ ይህ የንግድ ትርዒት በከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር ይፋዊ ድጋፍ ያለው ሲሆን በመጀመሪያው ፕሮግራም ላይ ከ17 ሀገራት የሚመጡ ከ100 በላይ የዓለም አቀፍ ድርጅቶች ይሳተፉበታል። በተጨማሪም በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና ያለውና በግንባታ ዘርፍ በሀገራችን የንግድ ትርዒት ታሪክ የመጀመሪያ የሆኑ ተከታታይ ሙያዊ ስልጠናዎች ፕሮግራሞች ይኖሩታል።

በዚህ የሲፒዲ /CPD/ ፕሮግራም/ የሙያ ስልጠና/፣ በግንባታ ዘርፍ የተሠማሩ የሀገራችን ባለሙያዎች ዓለም አቀፍ የምስክር ወረቀቶችን እንዲያገኙ እንዲሁም የሲፒዲ ነጥቦቻቸውን እንዲጨምሩ የሚያስችሉ ከ20 በላይ የሚሆኑ መድረኮች ተዘጋጅተዋል:: እነዚህ መድረኮች በፕሮጀክት አስተዳደር፣ በቴክኖሎጂ፣ በኪነሕንጻና ሥነቅርጽ፣ በምሕንድስና እንዲሁም በዘላቂነት ዙሪያ የተዘጋጁ ሲሆኑ፣ ታዋቂ ባለሙያዎች የሙያ ልምዳቸውን ያካፍሉባቸዋል:: ከስድስት ሺህ በላይ የሀገር ውስጥ ገዥዎችም በኤግዚቢሽኑ ላይ ይሳተፋሉ ተብሎ ይጠበቃል::

ኤግዚቢሽኑን አስመልክቶ ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጋር ቆይታ ያደረጉት የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር የኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ኢትዮጵያ በደቻ እንደተናገሩት፤ ቢግ ፋይፍ ኢትዮጵያ የተባለው የኮንስትራክሽን ኤግዚቢሽን የተዘጋጀው በፈጣን እድገት ላይ ያለውን የሀገሪቱን የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ጉዞን ለመቃኘት እና ያለበትን ሁኔታ ለማየት ነው:: በኤግዚቢሽኑ ከበርካታ ሀገራት የተውጣጡ ትላልቅ የኮንስትራክሽን ዘርፍ ኩባንያዎች ይሳተፋሉ ተብሎ የሚጠበቅ ሲሆን፤ ኤግዚቢሽኑ በከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር ድጋፍና ሙሉ እውቅና የሚሰጠው ኤግዚቢሽን ነው::

ይህ ኤግዚቢሽን በሀገሪቱ ዓለም አቀፍ ደረጃውን ጠብቆ ሲካሄድ ለመጀመሪያ ጊዜ እንደሆነ ጠቁመው ከዚህ ቀደም በሌሎች ሀገሮች መሰል ኤግዚቢሽኖች በስፋት ሲካሄዱና ኢትዮጵያም በኤግዚቢሽኖቹ ላይ ስትሳተፍ እንደነበር ጠቁመዋል:: በተለይም ባለፈው ዓመት በዱባይ በተካሄደው ኤግዚቢሽን ላይ ከኢትዮጵያ ከተለያዩ ተቋማት የተውጣጡ አመራሮች ተሳትፈውበታል::

የንግድ ትርዒቱ ላይ የአገሪቱ የኮንስትራክሽን ዘርፍ ማኅበረሰብ መሳተፋቸው ለዘርፉ ተዋናዮች ሙያዊ እድገት የራሱ አስተዋፅዖ ያበረክታል:: በርካታ ሙያተኞች የሚሳተፉበት እንደመሆኑ የሀገራችን የዘርፉ ሙያተኞች ከውጭ ሀገራት ከሚመጡ ሙያተኞች ጋር ተቀራርበው የመነጋገር እና በቀጣይ አብሮ የመሥራት እድል ይፈጥርላቸዋል:: ይህም በቀጣይ ለሀገራችን ሙያተኞች የሙያ እድገት ድርሻው የላቀ ነው ሲሉ አቶ ኢትዮጵያ ተናግረዋል::

**ከኮንስትራክሽን ግብዓት አንጻር የሲሚንቶ እና ብረት እጥረት እና ዋጋ መናር ዘርፉን እየፈተኑ ካሉ ችግሮች መካከል በግንባር ቀደምትነት ይጠቀሳሉ። የግንባታ ማጠናቀቂያ ግብዓቶች እጥረትም እንዲሁ ተጠቃሽ ነው። ኤግዚቢሽኑ የግንባታ ግብዓት አማራጮችንም ከማየት አኳያ መልካም አጋጣሚን ይፈጥራል፤ በተለይም ዘርፉን እያጋጠመ ያለውን የግብዓት እጥረት ችግርን ለመቅረፍ በየአካባቢው ያሉ አማራጮችን ለመጠቀም የሚረዱ አማራጭ መንገዶችን ለማየት በር ይከፍታል**

እንደ አቶ ኢትዮጵያ ማብራሪያ፤ ኤግዚቢሽኑ ለሀገሪቱ ባለሙያዎች የሙያ እድገት ከሚያበረክተው አስተዋፅዖ ባሻገር የአገሪቱ ባለሙያዎች እና ኩባንያዎች ዓለም አቀፋዊ የኮንስትራክሽን ዘርፉን እንዲቀላቀሉ ያደርጋል:: በዓለም የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ውስጥ ተዋናይ እንዲሆኑም በር የሚከፍት ነው::

እሳቸው እንዳሉት፤ የአገሪቱ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ በአሁኑ ወቅት ከፍተኛ ተግዳሮት ያለበት ነው የሚሉት አቶ ኢትዮጵያ፤ ተግዳሮቶቹ የግብዓት፣ የቴክኖሎጂ፣ የክህሎት ክፍተቶች መሆናቸውን አንስተዋል:: ከኮንስትራክሽን ግብዓት አንጻር የሲሚንቶ እና ብረት እጥረት እና ዋጋ መናር ዘርፉን እየፈተኑ ካሉ ችግሮች መካከል ግንባር ቀደም ተጠቃሽ ናቸው:: የግንባታ ማጠናቀቂያ ግብዓቶች እጥረትም እንዲሁ ተጠቃሽ ነው:: የግንባታ ግብዓት አማራጮችንም ከማየት አኳያ መልካም አጋጣሚ የሚፈጥር መሆኑን ነው የጠቆሙት:: ኤግዚቢሽኑ በተለይም ዘርፉን እያጋጠመ ያለውን የግብዓት እጥረት ችግርን ለመቅረፍ በየአካባቢው ያሉ አማራጮችን ለመጠቀም የሚረዱ አማራጭ መንገዶችን ለማየት በር እንደሚከፍት አስታውቀዋል::

እንደ አቶ ኢትዮጵያ ማብራሪያ፤ ለሀገሪቱ የኮንስትራክሽን ዘርፍ ሌላኛው እንቅፋት የዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች አጠቃቀም አነስተኛ መሆን ነው:: ኢትዮጵያን የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ሲታይ በጣም ኋላ ቀር መሆኑ ይታወቃል:: በዓለም ላይ የኮንስትራክሽን ዘርፍ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በፍጥነት ጥቅም ላይ እያዋለ ነው:: ኢትዮጵያ የረጅም ዘመን የኮንስትራክሽን ታሪክ ያላት ብትሆንም አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ተጠቅሞ የኮንስትራክሽን ሥራዎችን በማካሄድ ረገድ እምብዛም ነው:: በዚህም ምክንያት ዘርፉ ማደግ ባለበት ልክ ማደግ ሳይችል ቆይቷል::

በቅርቡ በሚካሄደው ኤግዚቢሽን ላይ አንቱታን ያተረፉት ትላልቅ ዓለም አቀፍ የኮንስትራክሽን ቴክኖሎጂዎች ባለቤት የሆኑ ኩባንያዎች እንደሚሳተፉ የሚጠበቅ ሲሆን፤ የሀገሪቱ የኮንስትራክሽን ድርጅቶች ከእነዚህ ኩባንያዎች ቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲያደርጉ እና ዘርፉን ለማሳደግ የሚያስችል ሥራ እንዲሠሩ እድል የሚፈጥር ነው ተብሏል::

በዘርፉ የዳበረ ክህሎት ያለው የሰው ኃይል እጥረትም መኖሩን የጠቆሙት አቶ ኢትዮጵያ፤ የክህሎት ክፍተቱ የተለያዩ መንስኤዎች መኖራቸውን ተናግረዋል፤ የክህሎት ክፍተቶችን ለመሙላት በተለያዩ አካላት የሚደረጉ ጥረቶች መኖራቸውን ጠቁመዋል:: ኤግዚቢሽኑ የክህሎት ክፍተቱን ለመሙላት ለሚደረገው እንቅስቃሴ የራሱን ሚና እንደሚጫወትም ነው የገለጹት::

እንደ አቶ ኢትዮጵያ ገለጻ ሀገሪቱ ለኮንስትራክሽን ኢንደስትሪ አመቺ የሆኑ የተለያዩ እድሎችም አላት:: ኤግዚቢሽኑ የዘርፉን ተግዳሮቶች ለመቅረፍ ካለው ፋይዳ ባሻገር፤ በአገሪቱ ያለውን የኮንትራክሽን ኢንዱስትሪ እድሎችንም ለማስተዋወቅ እድል በር የሚከፍት ነው:: ሀገሪቱ ያላትን የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪና በዘርፉ ያለውን ሀገር በቀል ሀብት ለማስተዋወቅ ዕድል ከመስጠት ባሻገር ሀገር በቀል ሀብት እንዴት ማስተዋወቅ እንደሚቻል፣ እንዴት ጥቅም ላይ ማዋል ፍንጭ የሚሰጥ ትልቅ ኤግዚቢሽን ነው::

ኤግዚቢሽኑ በርካታ የውጭ ኩባንያዎች በኢትዮጵያ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ውስጥ እንዲሰማሩና መዋዕለ ንዋያቸውን እንዲያፈሱም መነቃቃትን የሚፈጥር ነው ያሉት አቶ ኢትዮጵያ፤ በተለይም የውጭ ኩባንያዎች ከሀገር በቀል ኩባንያዎች ጋር በቅርበት የሚሰሩበትን እድል እንደሚፈጥር ጠቁመዋል::

ኤግዚቢሽንና ባዛር ሲካሄድ በዋናነት የሀገራችን የኮንስትራክሽን ኩባንያዎች ከሌሎች ሀገራት ከሚመጡ ኩባንያዎች ጋር እንዲሁም እርስ በርሳቸው የልምድ ልውውጥ እንዲያደርጉ እድል ይፈጥራል:: በሀገሪቱ ውስጥ ያሉ የኢንዱስትሪው ተዋናዮች ማለትም ተቋራጮች፣ መሐንዲሶች፣ አማካሪዎች፣ የሙያ ማኅበራት ሁሉ በቀላሉ ልምድ ማግኘት የሚችሉበት፣ የዓለማችን የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ የደረሰበትን ደረጃ ማየት የሚችሉበት እና በቀጣይም እንዴት አድርገው ተገናኝተው መሥራት የሚችሉበት ቢዝነስ ቱ ቢዝነስ የሚባለውን ፓርትነርሺፕ የሚፈጥሩበት ትልቅ እድል ነው::

እንደ አቶ ኢትዮጵያ ማብራሪያ፤ ለሀገሪቱ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪዎች የኮንስትራክሽን ማሽነሪዎች እጦት አንዱ ማነቆ ሆኖ ቆይቷል:: በአገሪቱ ያሉ የኮንስትራክሽን ማሽነሪዎች አስመጪዎች ማሽነሪዎችን የሚያስገቡት በብዙ ውጣ ውረድ ነው:: በኤግዚቢሽኑ የሚፈጠረው እድል ደግሞ ወደ ሀገር ውስጥ የሚያስመጡ ትላልቅ ሀገር በቀል ተቋማት የግንባታ ማሽነሪዎችን በቀላሉ ማግኘት የሚችሉበትን እድል ይፈጥራል::

ቢግ ፋይፍ ዓለም አቀፍ የኮንስትራክሽን ኩባንያ ሲሆን፤ ኩባንያው በተለያዩ ዓለም አቀፍ ሀገራት ውስጥ በተለያዩ ጊዜያት ኤግዚቢሽኖችን ሲያካሄድ ቆይቷል:: በእስያ፣ በአውሮፓ በሚገኙ በተለያዩ ከተሞች ኤግዚቢሽኖችን ሲያካሂድ ቆይቷል:: በሚሊኒየም አዳራሽ ከግንቦት 10 ጀምሮ የሚካሄደው ኤግዚቢሽን ለኢትዮጵያ የኮንስትራክሽን ዘርፍ እንደ ልዩ አጋጣሚ የሚታይ ነው ብለዋል::

ኤግዚቢሽኑ ለኮንስትራክሽን ዘርፍ ከሚያበረክተው አስተዋፅዖ ባሻገር ለቱሪዝም ዘርፉም የራሱን አስተዋፅዖ ያበረክታል:: በኤግዚቢሽኑ በርካታ ኩባንያዎች የሚሳተፉበት እንደመሆኑ ኤግዚቢሽኑ በኮንፈረንስ ቱሪዝም በኩል ለሀገሪቱ የሚያስገኘው ከፍተኛ ፋይዳ አለ:: ሀገሪቱ በኤግዚቢሽኑ ለመሳተፍ ከሚመጡት የውጭ ዜጎች ገቢ ታገኛለች ብለዋል::

ኤግዚቢሽኑን አስመልክቶ ጋዜጣዊ መግለጫ በተሰጠበት ወቅት የተገኙት የኢትዮጵያ የኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን ሥራ አስኪያጅ ኢንጂነር ዮናስ አያሌው በበኩላቸው የሀገሪቱ የኮንትራት እና የአማካሪ ኩባንያዎች ልምዶቻቸውንና ምርቶቻቸውን የሚያስተዋውቁበት እና የሚያሳዩበት እድል እንደሚፈጠር ጠቁመዋል:: ኮርፖሬሽኑም ድርጅቶቹ ራሳቸውን የሚያስተዋውቁበት እድል ለመፍጠር በትኩረት እየሠራ መሆኑን ጠቁመዋል::

የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስትሯ ወይዘሮ ጫልቱ ሳኒ በበኩላቸው፤ መንግሥት የኮንስትራክሽን ዘርፍ ውስጥ ያሉ ማነቆዎችን ለመፍታት እየሠራ መሆኑን ተናግረው፤ በተለይም በአሁኑ ወቅት መንግሥት በኮንስትራክሽን ዘርፍ ያሉ ማነቆዎችን ለመፍታት ወሳኝ ሥራዎችን እየሠራ ነው ብለዋል::

በ10 ዓመቱ እቅድም ዘርፉ ማበርከት የሚያስችለውን ሀገራዊ ሚና እንዲወጣ የተለያዩ ስትራቴጂካዊ አቅጣጫዎችን በመጠቀም እየተሠራበት መሆኑን ጠቁመው፤ በተጨማሪም የዘርፉ የ30 ዓመት ፍኖተ ካርታ የተዘጋጀ ሲሆን፤ በቅርቡ የሚካሄደው ኤግዚቢሽንም በኢትዮጵያ መካሄዱ ዘርፈ ብዙ ጠቃሜታዎች እንደሚኖረው ጠቁመዋል:: ኤግዚቢሽኑ በኢትዮጵያ መካሄድ የሀገራችንን የኮንስትራክሽን ዘርፍ ሁለንተናዊ እድገት የሚያበረክተውን የላቀ ሚና በመገንዘብ ሰፋፊ ሥራዎች እየተሰሩ ነው::

ዘርፉን ለማዘመን በሀገሪቱ ሰፋፊ ሥራዎች እየተሠሩ ባሉበት በዚህ ወቅት መካሄዱ እንደ ሀገር ልንቀስማቸውና ልንማርባቸው የሚገቡ ዓለም አቀፍ ልምዶችን አሠራሮችን፣ ዘርፉ የደረሰበትን የቴክኖሎጂ ደረጃ በሀገራችን ለማስተዋወቅ እድል የሚፈጥር በመሆኑ ለሀገራችን እንደ ልዩ እድል የሚታይ ነው ብለዋል::

በተለያዩ የዓለም ክፍሎች ኤግዚቢሽኖችን በማዘጋጀት የሚታወቀው የዲ ኤም ጂ ኢቨንትስ ምክትል ሥራ አስኪያጅ ቤን ግሬኒሽ እንደተናገሩት፤ ኤግዚቢሽኑ በኮንስትራክሽን ዘርፍ ሰፊ ልምድ ያካበቱ የኮንስትራክሽን ዘርፍ ተዋንያን ከመላው ዓለም በስፋት የሚሳተፉበት ነው:: በኤግዚቢሽኑ ላይ የሚሳተፉ አካላት በግንባታ፣ በግንባታ ዲጂታላይዜሽን እና በሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ላይ የረጅም ዘመን ልምድ ያላቸው መሆናቸውን አንስተዋል:: ኤግዚቢሽኑ ለኮንስትራክሽን ዘርፍ እጅግ ጠቃሚ የሆኑ የመፍትሔ ሀሳቦች የሚቀርቡበት ሲሆን ከዚህ ባለፈም በዘርፉ ያሉ ባለድርሻ አካላት እውቀትንም አንድ ደረጃ ከፍ የሚያደርግ ነው ብለዋል::

በተጨማሪም ዘመኑ የደረሰበትን የሕንጻ ውስጥ ንድፎች እና የፊኒሽንግ ሥራዎች፣ የግንባታ እቃዎች እና መሣሪያዎች፣ የሶላር እና የከተማ ዲዛይን ላይ የፈጠራ ሥራዎቻቸውን እንዲሁም ምርቶቻቸውን ለመጎብኘት እና የንግድ ትስስር ለመፍጠር ምቹ እድል የሚፈጥር እንደሆነም አንስተዋል::

ኤግዚቢሽኑ እነዚህ ባለሙያዎች ከኢትዮጵያ የኮንስትራክሽን ዘርፍ ማኅበረሰብ ጋር እንዲገናኙ እድል እንደሚፈጥር ጠቁመው፤ ባለሙያዎቹ ከኢትዮጵያ የኮንስትራክሽን ዘርፍ ማኅበረሰብ ጋር የሚኖራቸው መስተጋብር የሀገሪቱን የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ አንድ እርምጃ እንደሚያሳድግ ጠቁመዋል::

# ርዕሰ አንቀፅ

## የአሁኑ ትውልድ የጀግኖች አርበኞችን ድል በልማቱ በመድገም የራሱን ደማቅ ታሪክ መጻፍ ይጠበቅበታል!

ኢትዮጵያውያን ጀግኖች አርበኞች ሀገራቸውን ለአምስት ዓመታት በኃይል የወረረውን ፋሽስት ጣሊያንን በዱር በገደል ተዋድቀው በማሸነፍ ሃገራቸውን ነጻ ያደረጉበት 82ኛው የድል በዓል ዛሬ በመላ ኢትዮጵያ እየተከበረ ይገኛል:: ኢትዮጵያን ቅኝ ለመግዛት ያሰፈሰፉት ጣሊያኖች በዓድዋው ጦርነት በኢትዮጵያውያን የደረሰባቸውን ውርደት ለመበቀል አርባ ዓመታት ተዘጋጅተው በዘመናዊ መሣሪያ ተደራጅተው ተመልሰው በመምጣት ኢትዮጵያን ቢወሩም እቅዳቸው ግን አልተሳካም::

ፋሽስቶቹ ሀገሪቱን በመውረር በኢትዮጵያውያን ላይ ያልፈጸሙት የግፍ ዓይነት አልነበረም:: በዚህ ወረራም ማይጨው ላይ የገጠማቸውን የኢትዮጵያ ጦር በዓለም አቀፍ ደረጃ የተከለከለ የጦር መሣሪያ /የመርዝ ጋዝ/ ጭምር በመጠቀም በግፍ ጨፍጭፈዋል:: ግራዚያኒ የካቲት 12 ቀን 1929 ዓ.ም በአዲስ አበባ ነዋሪዎች ላይ ዘግናኝ ጭፍጨፋ እንዲፈጸም አድርጓል:: በዚህ ግፍ የተሞላበት ድርጊት ከ30 ሺ በላይ ኢትዮጵያውያን በአካፋ፣ በዶማና በመሳሰሉት ጭምር በግፍ ተጨፍጭፈዋል:: ጭፍጨፋው ከአዲስ አበባም ወጥቶም ደብረ ሊባኖስ ድረስ በመዝለቅ የበርካታ ኢትዮጵያውያን ሕይወት ነጥቋል::

ኢትዮጵያውያን ግን የቱንም ያህል የፋሽስቶች በትር ቢጸናባቸውም፣ የቱንም ያህል ወገኖቻቸው በግፍ ቢገደሉባቸውም ፋሽቶችን መውጫ መግቢያ መንሳታቸውን አጠናክረው ቀጥለውበታል:: እምቢኝ ለሀገሬ ብለው በዱር በገደሉ ሆነው ፋሽስቶችን ለአምስት ዓመታት በመፈተን ፋሽስቶቹ ተደላድለው እንዳይቆዩ ከማድረግ ባለፈ ሽንፈትን እንዲከናነቡ በማድረግ በ1933 ዓ/ም በዚህ ቀን ከሀገራቸው ጠራርገው አስወጥተዋቸዋል:: የዛሬው የድል በዓልም ይህንን የጀግኖች ኢትዮጵያውያንን ታላቅ ጀግንነት የሚዘከር ነው::

ኢትዮጵያውያን ታላቅ ድል ያስመዘገቡት ዘመናዊ የጦር መሣሪያ ታጥቀው አልነበረም፤ ከሃገር በላይ ምንም የሚቀድም እንደሌለ በመገንዘብ በአንድነት ሆነው በወኔ ተሞልተው ባደረጉት እልህ አስጨራሽ ተጋድሎ ነው:: ይደርስባቸው የነበረው ጭፍጨፋና ስቃይ ጠንክረው እንዲዋጉ አበረታታቸው፣ አንድ አደረጋቸው እንጂ ሸብረክ እንዲሉ አላደረጋቸውም:: በዱር በገድል እየተዘዋወሩ ፋሽስት ጣሊያንን መቆሚያ መቀመጫ ነስተውታል፤ ቁም ስቅሉን አሳይተውታል፤ በመጨረሻም ጠራርገው በማስወጣት ጀግኖች አባቶቻቸው በዓድዋ የተጎናጸፉትን ድል እነሱም ደግመውታል::

ይህን ታላቅ ገድል በመጻፍ እንደ ዓድዋ አባቶቻቸው ሁሉ ሀገራቸው በፋሽስቶች መዳፍ ውስጥ እንዳትገባ በማድረግ ታሪክ ደግመው ጽፈዋል:: ይህ ድል ፊቱንም በዓድዋው ድል የሚታወቁትን ኢትዮጵያውያንን ጀግንነት ድርብ ድርብርብ እንዲሆን አድርጎታል:: የኢትዮጵያውያን ጀግንነት ሌላ ከፍታ እንዲላበስ አድርጓል::

ኢትዮጵያውያን የሀገር ሉዓላዊነትን የሚደፍሩ ድርጊቶች ከውጭ ኃይሎች ሊሰነዘሩ በተሞከሩም ሆነ በተሰነዘሩ ቁጥር ለጠላትም ለወዳጅም በሚል እነዚህ የጦር ሜዳ ገድሎቻቸው ይጠቀሳሉ:: ኢትዮጵያውያን የውጪ ኃይሎች ሀገራቸውን በወረሩበትም ሆነ ሊወሩ ባሰቡበት ወቅት ሁሉ እነዚህ ታሪኮች ይጠቀሳሉ፤ በእነዚህ ታሪኮች ልክ ጠላቶቻቸውን እንደሚያሸንፉም በሚገባ ያምናሉ:: ኢትዮጵያውያን እያንዳንዱን ሙከራ በቀደመው የአያት ቅድመ አያቶቻቸውና አባቶቻቸው የጀግንነት ታሪክ አክሽፈዋል::

በልማቱም መስክ ይህንኑ ጀግንነት ለመድገም ይተባበራሉ:: በዓለምም በአፍሪካም ጭምር ታላቅ የተባለውን የዓባይ ግድብ አሁን ለደረሰበት ወሳኝ ምዕራፍ ያበቁት በዚህ ጀግንነትና ጀግንነቱን በወለደው የአንድነትና የመተባበር ወኔ በመነሳሳት ነው::

ወደፊትም ይሄው ነው የሚሆነው:: ኢትዮጵያውያን ድህነትና ድርቅ ለመቋቋም የሚያስችል ሥራ ለመሥራት ሞክረዋል፤ ከድህነት በላይ ጠላት የለንም ብለው በድህነት ላይ ዘምተዋል::

ኢትዮጵያውያን የዜጎችን ተጠቃሚነት ለማሳደግና የሀገሪቱን ብልጽግና ለማረጋገጥ አሁንም በአንድነትና በመተባበር መሥራት አለባቸው:: እነዚህ ላይ ለመድረስ በመንግሥት በሚከናወኑ ተግባሮች ብቻ ብዙ ርቀት መጓዝ አይቻልም:: የዜጎች በግል መሮጥ አንድ ነገር ሆኖ ባስፈለገ ጊዜ ተባብሮ መሥራትና በአንድነት መቆም ያስፈልጋል::

ትላልቅ ፕሮጀክቶችን አብሮ መፈጸም እንደሚቻል ከዓባይ ግድብ መረዳት ተችሏል:: በቀጣይም መንግሥት ለግዙፍ ፕሮጀክቶቹ እውን መሆን የሚያደርጋቸውን ጥሪዎች በመቀበል በልማት ላይ በንቃት በመሳተፍ ለዜጎችና ለሀገር የበለጠ ተጠቃሚነት መሥራት ዘመኑ የሚጠይቀው ጀግንነት መሆኑን መገንዘብ ይገባል:: በዚህም ጀግኖች አርበኞች በፋሽስቶች ላይ የተጎናጸፉትን ድል ይህ ትውልድ በልማቱ ለመድገም የተጀመሩ ጥረቶችን በመደገፍ የራሱን ታሪክ መጻፍ ይጠበቅበታል::

በልማቱ ድልን ለመጎናጸፍ ልክ ጀግኖች አርበኞች ብዙ ፈተናዎችን አልፈው ድል እንደተጎናጸፉት ሁሉ ይህ ትውልድም በልማቱ ነገሮች አልጋ በአልጋ ላይሆኑ እንደማይችሉ በመገንዘብ ከፈተና መውጫ መንገዶችን በማዘጋጀት በልማቱ ሀገርና ሕዝብን የሚያሻግር ድል ለማስመዝገብ ርብርብ ሊያደርግ ይገባል!

**አዲስ ዘመን**

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ:- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

## ከትናንት ተምረን ጦርነትን በሁለንተናዊ መልኩ ልናወግዝ ይገባል ?

ሶሎሞን በየነ

የጦርነትን አስከፊነትና አውዳሚነት ዓለም ላይ ከኢትዮጵያውያን በላይ ከሊቅ እስከ ደቂቅ በምላሱ ቀምሶ፣ በአይኑ አይቶ፣ በጆሮው ሰምቶ፣ በአፍንጫው አሽትቶ፣ በእጁ ዳሶ በጥቅሉ በአምስቱ የስሜት ሕዋሳት ያረጋገጠ የለም። በተለይ የ1960ዎቹ ትውልድ በተከተሉትና እየተከተሉት ባለው የሴራና የመጠላለፍ ፖለቲካ ሳቢያ ላለፉት ግማሽ ምዕተ ዓመታት በአገሪቱ በዘለቀው የእርስ በእርስ ጦርነት ምክንያት እንደሀገር ወደፊት መጓዝ ተስኖን ባለንበት ቆመናል።

በተፈጥሮ ሀብት እንዲሁም በማዕድን የበለጸገ ለም መሬት ይዘን ሆዳችን ተርቧል። እኛ ከጦርነት አዙሪት መውጣት ተስኖንን ስንዳክር ብዙዎች ግን ከኋላችን ተነስተው ዛሬ ላይ በሳይንስ፣ በቴክኖሎጂ፣ በኢኮኖሚ ... ወዘተ ተመንድገው የት እንደደረሱ እያየን ነው። የጦርነትን አስከፊነትና አውዳሚነት ለኢትዮጵያውያን መናገር ለቀባሪ እንደማርዳት ይቆጠራል። የሰላምን ዋጋ ማስገንዘብም እንዲሁ ።

እሩቅ ሳንሄድ ባለፉት ሁለት ዓመታት በአገሪቱ በሰሜኑ ክፍል በነበረው ጦርነት የአንድ ሀገር ዜጎች እርስ በእርስ ተዋግተው እልፎች ተሰውተዋል። አያሌ ንጹሓን ዜጎች ሕይወታቸውን አጥተዋል። ከሕጻን እስከ ዓለም በቃኝ ብላ እስከመነነች አዛውንት መነኩሴ ድረስ ብዙዎች ተደፍረዋል። የሀገሪቱን ዓመታዊ በጀት በእጥፍ የሚሸፍን ሀብት በጦርነቱ ደቋል። መሠረተ ልማት ወድሟል። አንዳንድ የወደሙ መሠረተ ልማቶችን ወደነበሩበት ለመመለስ ዓመታትን ጭምር ይወስዳሉ።

ሺህዎች ከትምህርት ገበታቸው ተፈናቅለው ከሕይወታቸው ላይ እንደዋዛ ዓመታትን አባክነዋል። መላው የኢትዮጵያ ሕዝብም የሰላም አየር እርቆት ጠዋት ማታ በጦርነት ዜና አዕምሮው ታውኮ ቆይቷል። በጥቅሉ ጦርነቱ ያስከተለውን ዳፋ አይደለም በዚች አጭር መጣጥፍ ቀርቶ በየመስኩ (በማኅበራዊ፣ በታሪክ፣ በኢኮኖሚ፣ በፖለቲካ፣ በሥነ-ልቦና ወ.ዘ.ተ ) አንዳንድ መጽሐፍ ቢዘጋጅ እንኳን ጥንቅቅ አድርጎ የሚገልጸው አይመስለኝም።

ታዲያ "ጦርነት ይብቃ፣ ሰላምን እናጽና" በሚል መሪ ቃል በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል ሲካሄድ የነበረው ጦርነት "በሰጥቶ መቀበል መርሕ" በፕሪቶሪያ ሲደረግ በነበረው ድርድር በሰላም እንዲያልቅ ከፍተኛ ሚና ለተጫወቱ ወገኖች እውቅና በተሰጠበት ማግስት ሆን ብየ የጦርነቱን ጠባሳ ማንሳቴ የሰውን ቁስል ለማስታወስ ፈልጌ አይደለም።

ወይም ሰላም ወርዶ በአገሪቱ የሰላም አየር በመንፈሱ ሳልደሰት ቀርቼ አይደለም። ወይም ደግሞ የጦርነት ነጋዴ ሆኜም አይደለም። እንደአንድ ሰላም ወዳድ ዜጋ የሰላም አየር በመንፈሱ እጅግ ደስተኛ ነኝ። ይልቁንም ትናንት በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል የጥይት ድምፅ ከመሰማቱ በፊት በሰለጠነ መንገድ በጠረጴዛ ዙሪያ ቁጭ ተብሎ ችግሮችን ሰጥቶ በመቀበል መርሕ ተፈትቶ ቢሆን ኖሮ፤ "እንደሀገር የገባንበት ምስቅልቅል ውስጥ ባልገባን፤ ገመናችንም የዓለም አደባባይ ላይ ወጥቶ ባልተሰጣ ነበር" ብሎ ሁሉም ኢትዮጵያዊ እንደሚቆጭ እርግጠኛ ነኝ።

ሌላው ቀርቶ የጦርነቱ ጠንሳሾችና ተዋናዮች እራሱ እንደተቆጩና ሕዝባቸውን ለመካስ በቁርጠኝነት እንደሚሠሩ ከድርድሩ ማግስት ሲናገሩ ተደምጠዋል። ቁጭ ብሎ በጋራ ለመነጋገር "አሻፈረኝ" ሲሉ የነበሩ አካላት ዛሬ ላይ በአንድ ጠረጴዛ ዙሪያ ቁጭ ብለው ችግራቸውን ፈትተው የሰላም አየር እንዲሰፈን ማድረጋቸው በጣም ያስደስታል። ይህ የሰላም ድርድር ይበልጥ ከአውዳሚው ጦርነት በፊት ቢሆን ኖሮ ደግሞ ምን ያህል አገርን ከውድቀት፤ ሕዝብን ከመለያየት ይታደግ እንደነበር መገመጥ የሚከብድ አይሆንም ።

ነገሩ "የሺህ ፍልጥ ማሰሪያው ልጥ" እንደሚባለው የጦርነት መቋጫው ሰላማዊ ድርድር ነው። በመሆኑም በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል የነበረው ጦርነት በድርድር ተፈትቶ ሰላም ሰፍኗል። ዘግይቶም ቢሆን ሰላም እንዲመጣ የበኩላቸውን ሚና የተጫወቱ አካላት ምስጋና ይገባቸዋል። ሰላሙ እስከመጨረሻው የጸና እንዲሆን ሁሉም አካላት የበኩሉን ድርሻ ሊወጣ ይገባል።

> **መንግሥት ከሁሉም በላይ በሀገሪቱ ሰላም እንዲሰፍንና የዜጎች ደህንነት እንዲጠበቅ ከማድረግ ካለን ኃላፊነት አንጻር ችግሮችን በሆደ ሰፊነት በድርድር ለመፍታት የጀመረውንና ትርጉም ያለው ውጤት እያመጣ ባለው አካሄዱ በበለጠ ቁርጠኝነት ሊቀጥልበት ይገባል**

ማኅበረሰቡም የበኩሉን ሚና መጫወት አለበት። ሰላሙ ይበልጥ እንዲጸና ከበላይ አመራሩ ባሻገር ኅብረተሰቡ ተቀራርቦ የሚወያይበት መድረክ ሊፈጠር ይገባል።

በዚህ ጽሑፌ ላነሳው ወደ ፈለኩት ርዕሰ ጉዳይ ስመለስ ፤ ዛሬስ እንደሀገር እና ሕዝብ አይደለም ከትናንት አዳፋ ታሪካችን ከዛሬ ስድስት ወር በፊት በአገሪቱ በሰሜኑ ክፍል ሲካሄድ ከነበረው ጦርነት ከልብ የጦርነትን አስከፊነት ተምረናል ወይ? የሚለው ነው።

ትናንት ችግሮቻችን በሰጥቶ መቀበል መርሕ መፍታት ተስኖን ከገባንበት የጦርነት አዙሪት በቅጡ ሳንወጣ ዛሬም ሌላ የጦርነት ምዕራፍ ለመክፈት እዚህም እዚያም የጦርነት ነጋሪት ሲጎሰም ይሰማል። ትናንት የሰላም አማራጮች ሁሉ ተዘግተው ወደ ጦርነት በመግባቱ ያተረፈ ማነው? ያሸነፈስ ማነው? ...? የአንድ ሀገር ልጆች እርስ በእርስ በመገዳደል አሸናፊም፣ አትራፊም ... እንደሌለ ከአንዴም ሁለት፣ ሶስት ጊዜ ከኛ ከኢትዮጵያውያን በላይ ያየ ማን አለ።

በዚህ በ21ኛው ክፍለ ዘመን ሀሳብን በሀሳብ እንጂ በጠመንጃ ማሸነፍ አይቻልም። ይህን ደግሞ እሩቅ ሳንሄድ በቅርቡ በአገሪቱ በሰሜኑ ክፍል ሲካሄድ በነበረው ጦርነነት ታይቷል። በመሆኑም ልዩነት ያለው ኃይል ሁሉ ከመንግሥት ጋር ቁጭ ብሎ በሰከነ መንፈስ መነጋገር አለበት። ልዩነትን በውይይት እንጂ በመገዳደል መፍታት ያለፈበትና ኃላቀር ፋሽን ነው።

መንግሥት ከሁሉም በላይ በሀገሪቱ ሰላም እንዲሰፍንና የዜጎች ደህንነት እንዲጠበቅ ከማድረግ ካለን ኃላፊነት አንጻር ችግሮችን በሆደ ሰፊነት በድርድር ለመፍታት የጀመረውንና ትርጉም ያለው ውጤት እያመጣ ባለው አካሄዱ በበለጠ ቁርጠኝነት ሊቀጥልበት ይገባል ።

ኅብረተሰቡ የጦርነቶች ዋነኛ ገፈት ቀማሽ እራሱ መሆኑን ከትናንት የጦርነት ታሪኮች በመማር የጦርነት ነጋሪት ጎሳሚዎችን በቃችሁ ሊል ፤ለሰላም ዘብ መቆምና ጦርነትን ባገኛው አጋጣሚ ሁሉ ማውገዝ ይጠበቅበታል።

በአጠቃላይ የዓለም ታሪክ እንደሚያስረዳን ጦርነት ለሰላም በተዘረጉ እጆች እንጂ በመሣሪያ እጦት አይቆምም። እንዲሁም በሰላማዊ ድርድር እንጂ በአሸናፊና በተሸናፊ መንፈስ የተቋጩ ጦርነቶች ዘላቂ ሰላም አያሰፍኑም። ይህንንም በተጨባጭ እኛ ኢትዮጵያውያን ደግሞ ላለፉት ግማሽ ምዕተ ዓመታት እርስ በእርስ ተዋግተን አይተነዋል። በቅርቡም የጦርነትን አስከፊነት አይተነዋል።

ከጦርነቶች ያተረፍነው አንዳች ነገር የለም። ስህተትን በስህተት በመድገም "ታጥቦ ጭቃ" መሆን የለብንም። እንደሀገር ሁለንተናዊ እድገታችን በሰላም እንጂ በጦርነት አይረጋገጥም። ይህንን ተገንዝበን ከትናንት ስህተታችን በመማር በሰጥቶ መቀበል መርሕ የትኛውንም ችግር በድርድር በመፍታት ሰላማችንና አንድነታችን በማጽናት በኅብረት የኢትዮጵያን ብልጽግና እውን የማድረግ ኃላፊነት ከሁሉም ዜጋ የሚጠበቅ ነው።

ማህበራዊ

# እንዲህም ይኖራል

**ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ለተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ለመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፣ ^አስተውሳችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ለአስተያየቶቻችሁ፣ ለመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ለድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።**

## ፍቅርና ተስፋን በሙዳይ

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

ዕለቱ እንደወትሮው ነው:: ልክ እንደትናንቱ ዛሬን ንጋት ተክቶታል:: ወፎቹ ተንጫጭተው ፀሀይ ማልዳ ፈንጥቃለች:: ጨለማው ገፎ ቀኑ ሊጀምር ተሰናድቷል:: ሀሳብ ውሎ የሚያድርበት የወይዘሮዋ ዓይምሮ ዛሬም ከልምዱ አልታቀበም:: አርቆ እያለመ ያቅዳል:: ከጭንቅ ጓዳው ገብቶ የቋጠረውን እየፈታ፣ የፈታውን ዳግም ያስራል::

ወይዘሮዋ ሁሌም ቢሆን እንዲህ ናት:: የጎደለ፣ ያልሞላው ዕልፍኝ ያሳስባታል:: በእጇ ያሉ በርካታ ነፍሶች የእሷ ጉዳይ ከሆኑ ቆይተዋል:: የእነሱ ህልውና፣ የህይወት ጓዛቸው ከትከሻዋ አርፏል:: ሸክሙ ቢያጎብጣትም «ደከመኝ» ይሉትን አታውቅም:: መሸቶ እስኪነጋ ከጎናቸው ትቆማለች:: ህይወቷ ከህይወታቸው፣ ኑሮዋ ከኑሯቸው ተቆራኝቷል:: ለነዚህ ነፍሶች ከፈጣሪ ቀጥሎ ተስፋቸው ናትና ህመማቸው ያማታል፣ መከፋት ማዘናቸው ከልብ ያስነባታል::

### ከአስራ ሁለት ዓመት በፊት

ዛሬም ሌላው ቀን መሽቶ ነግቷል:: አሁንም የወይዘሮ ሙዳይ ልቦና መልካምና ደጉን እያቀደ ያስባል:: ማለዳውን ከበሯ የደረሰችው እንግዳ ከሌሎች ጋር ጠንከር ያለ ወግ ይዛለች:: በዚህ ማለዳ እሷን መሰል እንግዳ ማየት ለሙዳይና ለስራ ባልደረቦቿ ብርቅ አይደለም:: ሁሌም ልጆች ይዘው የሚመጡ፣ ችግራቸውን የሚያስረዱ፣ «እርዱን፣ ተቀበሉን» የሚሉ ወገኖች በርካታ ናቸው::

የእነሱና መሰሎቻቸው ችግር ዕንቅልፍ የነሳት ሙዳይ ምትኩ በልጅነት ዕድሜዋ የወጠነችው በጎነት ዛሬ ከፍሬ ደርሷል:: በርካታ ውጣውረዶችን ተሻግራም ለተቸገሩት ደራሽ፣ ላዘኑት ዕንባ አባሽ ከሆነች ዓመታት ተቆጥረዋል::

የሰዎች መከራና ችግር ሕመም ሆኗት ያቋቋመችው ግብረሰናይ ድርጅት ጥላ የሆናቸው በርካቶች ለችግራቸው መላና መፍትሄ አግኝተዋል:: ዛሬም ወደግቢው የሚመጡ፣ የህይወት ሸክም የከበዳቸው ነፍሶች ጥቂት አይደሉም:: ሙዳይ በማለዳው ከድርጅቱ ሰራተኞች ጋር የምታወጋው ሴት ጉዳይ ከዚሁ ሀሳብ እንደማይርቅ ገምታለች፡ በዛሬዋ እንግዳና በሰራተኞቹ መካከል ያለው ንግግርም ተራ ጨዋታ አለመሆኑ ገብቷታል::

ሙዳይ የምትሮጥ፣ የምትጣደፍበት ብዙ ጉዳዮች አሏት:: ትናንት በይደር የተወችው፣ ለዛሬ የቀጠረችው ብዙ ውጥን አለ:: ልትወጣ ተጣድፋለች:: በድንገት ግን ጆሮዋ ዘው ያለው ቃል ባለችበት አደንዝዞ ከእርምጃዋ አቀባት:: ሴትዮዋ ስለ አንድ ትንሽ ልጅ ታሪክ እያወራች ነው:: እየደጋገመች «እባካችሁ ባይሆን አብሉት፣ አጉርሱት ስትል ትማጸናለች::

ሙዳይ ይህን ቃል መልሳ መስማት አልቻለችም:: ውስጧ በእጅጉ ሲዝል፣ ሲፈተን ተሰማት:: ሴትየዋ እያወራች ያለችው ምግብ ቀምሶ ስለማያውቅ አንድ ትንሽ ልጅ ነው:: ሙዳይ ልማደኛ ዕንባዋ ከዓይኖቿ ተዘርግፎ ደረቷን ገምሶ መውረድ ያዘ::

ህጻን ልጅ ይልሰው ይቀምሰው አጥቶ «አብሉልኝ፣ አጠጡልኝ የመባሉ ተማጽኖ ከልብ አሳዝኗታል:: እሷ ሁሌም ለችግር ደራሽ ነች:: ጆሮዎቿ ክፉ ሰምተው፣ እግሮቿ ተራምደው አያልፉም:: እጀ ሰፊ መዳፏ ከመስጠት ባሻገር የወደቀን ሊያነሳ አይጠየፍም:: ምግብ በልቶ ስለማያውቀው ህጻን የሰማችው እውነት እንደ አዲስ ሆድ አስብሶ እያስለቀሳት ነው::

ሁሉም የእንግዳዋን ያልተለመደ ንግግር አልተቀበሉም:: ልጅ ያለምግብ መኖሩ ፈፅሞ አይታመንም:: እናም ይህች ሴት እርዳታ ለማግኘት ስትል ያመጣችው ሰበብ መሆኑን ገመቱ:: ሙዳይ በሴትየዋ ንግግር ልቧ ቢነካ በዕንባዋ ጭጋግ ምላሹን ልታገኝ ሻተች:: ውስጧ ያለውን ሀሳብ ከጥያቄ አዛምዳም ማብራሪያ ጠየቀች:: እንግዳዋ ስለ ሁሉም አልዘገየችም:: አንድ በአንድ እየተነተነች ታሪኩን



ፎቶ፡ ፀሐይ ንጉሤ

**ትንሹ እሱነህ ዕድሜው ሁለት ዓመት እስኪሞላ ምግብ የሚባል ቀምሶ አያውቅም ነበር፣**

መናገር ጀመረች::

ህጻኑ ብዘዎች እንደገመቱት የእሷ ሳይሆን የጎረቤት ልጅ ነው:: ከተወለደ አንስቶ ምግብ ይሉትን ቀምሶ አያውቅም:: ስለእሱ መኖር ግድ ያላት ይህች ሴት የልጁን ከፊል ታሪክ ለወይዘሮ ሙዳይ አወጋቻት:: ያለችው ሁሉ የሚታመን አይመስልም:: ጥቂት ቆይቶ ሴትየዋ ልጁን በአካል ይዛው እንድትመጣ ተወሰነ:: በዚህ ቃል ተስማምተውም በቀጠሮ ተለያዩ::

### ማግስቱን

እነሆ ዛሬም የወይዘሮ ሙዳይ የሩጫ ቀን ነግቷል:: እንደሁልግዜው ማለዳዋን በተለመደው የስራ ትጋት ጀምራለች:: በክፍሉ በርከት ያሉ ህጻናት ቁርስ ለመብላት ተቀምጠዋል:: ሙዳይ ለትንንሾቹ ወተት እየቀዳች ዳቦ ነክራ ታጎርሳለች:: በድንገት ካጎነበሰችበት ቀና አለች:: የትናንትናዋ ሴት ልጅ አዝላ ቆማለች:: ዓይኗን ከታዘለው ህፃን ሳትነቅል በፈገግታ ተቀበለቻት::

ልጁ ከእንግዳዋ ጀርባ እንደታዘለ ተኝቷል:: የሁለት ዓመት ህጻን ነው:: ሙዳይ ሴትዬዋ የመጣችበትን ጊዜ እንደ መልካም አጋጣሚ ቆጥራዋለች:: በዚህ ሰዓት ልጆቹ ቁርስ ይመገባሉ:: ለሴትዬዋ ልጁን እንድታወርደው ነገረቻት:: ያለቻትን አደረገች:: ያዘለችበትን ጨርቅ ፈትታ ልጁን ማውረድ ስትጀምር ቤቱ በተለየ ክፉ ሽታ ታወደ::

የህጻኑ ልብስ በእጅጉ ቆሽሿል:: ውሀ ነክቶት የማያውቀው አካሉ ከቁስቁልና ተዳምሮ ችግሩን ያሳብቃል:: ልማደኛው የሙዳይ ልብ በሀዘን መድማቱን ያዘ:: የምታየውን አምኖ መቀበል ተሳናት:: ቀረብ ብላ ህጻኑን አስተዋለችው:: እጅግ የሚያምሩት ትላልቅ ዓይኖቹ ያሳሳሉ:: ድፍት ያለ ጥቁር ጸጉሩ የተለየ አድርጎታል::

ወዲያው ልጁን ተቀብላ ልብሱን ቀየረች:: በጥንቃቄ ታቅፋ ከህጻናት ወንበር ደጋግፋ አስቀመጠችው:: ወተት ቀድታ ዳቦ ነከረችና ወደ አፉ ተጠጋች:: መራቡን ስለምታውቅ ፈጥኖ አፉን እንደሚከፍት ገምታለች:: በልጁ ገጽታ የተለየ ስሜት አላየችም:: የምታደርገውን እንዲያውቅ ምልክት ሰጠችው:: የታሰበው አልሆነም:: ልጁ ምግብ ቀምሶ አያውቅምና የማኘክ ሙከራ እንኳን አላሳየም::

እሷን ጨምሮ የግቢው ሰራተኞች በዕንባ ተራጩ:: ተስፋ ያልቆረጠችው ሙዳይ ወተት ያራሰውን ዳቦ ይዛ ዳግም ወደ ልጁ ተጠጋች:: ህፃኑ አሁንም በአፉ ስለደረሰው ምግብ አንዳች ያወቀው የለም:: በጥርሶቹ መሀል ያለውን ዳቦ እንደያዘ ደቂቃዎች ተቆጠሩ:: ህፃኑ በቀን አንዴ ብቻ በጡጦ ከሚቀምሰው የጤፍ አጥሚት በቀር ከምግብ ተገናኝቶ አያውቅም::

ሙዳይ ዛሬም ድረስ የምታለቅስበት ይህ ታሪክ ዕለቱን የነበረው ገጽታ የተለየ እንደነበር ታስታውሳለች:: ልጁ ምግብ ቀምሶ አለማወቁ ከታየ በኋላ ያመጣችው ሴት እያመላለሰች እንድታበላው ተወሰነ:: እንዲያም ሆኖ የልብ አልደረሰም:: ልጁ አሁንም ከጉዳት አላመለጠም:: ሁኔታው አሳሳቢ ቢሆን ሌሎች አማራጮች ሊፈለጉ ግድ ሆነ:: እሱነህን ልትቀበለው ከውሳኔ ደረሰች::

ይህ ከመሆኑ በፊት ሙዳይ ስለልጁ እናት አባት ማወቅ ፈለገች:: እንደ እናት መከታ የሆነችውን የጎረቤት ሴትም ጠየቃቻት:: ለህጻኑ ወላጅ እናት ያልሆነችው ድንቅ እናት ታሪኩን አልደበቀቻትም:: ስለ ትንሹ ልጅና ስለ ወላጆቹ ያለውን ሀቅ አንድ በአንድ ነገረቻት::

### እውነታ

ባልና ሚስቱ ትዳር ይዘው ጎጆ ወጥተዋል:: ኑሯቸው ድህነት ባያጣውም ዓይናቸውን በዓይናቸው ለማየት ይሻሉ:: የጎደለው ህይወት ባይሞላም፣ ወግና ልማድ መቀጠሉ አይቀርም:: የጥንዶቹ ዓለም የልጅ ሳቅና ጨዋታ ነው:: በልጅ ፍሬ የጎደለ ተስፋቸው ይሞላል:: የደበዘዘ ሳቃቸው ይደምቃል:: አሁን የባልና ሚስቱ ውጥን ተሳክቷል:: ወይዘሮዋ ወንድ ልጅ ወልዳ ታቅፋለች::

ለጥንዶቹ ትዳር ደማቅ ብርሀን የሆነው ጨቅላ በዓይን ሊያዩት ያሳሳል፣ ዓይኖቹ፣ ጸጉሩ፣ መላው ሰውነቱ ያምራል:: ይህን ያስተዋሉ ወላጆች ለልጃቸው ይሆናል፣ ይመጥናል ያሉትን ስም ቸሩት «የእሱነው» ብለው ሰየሙት::

ትንሹ የእሱነው በእናቱ ዕቅፍ ተኝቶ ይውላል:: የተለየ ባህርይ የለውም:: ከፍ ማለት ሲጀምር ወላጆቹ ለውጡን አብዝተው ናፈቁ:: ዕድሜውን እየቆጠሩ፣ መዳህ መሮጡን አሰቡ:: ማውራት መሳቁን ጠበቁ:: እሱነህ በእነሱ ምኞት ልክ አልፈጠነም:: እንደዕድሜ እኩዮቹ አልተነሳም፣፤ አልሳቀም፣ አልቦረቀም::

እሱነህ ስድስት ወር ሲሞላው ወላጆቹ እውነቱን አወቁት:: የህጻኑ የሚያምሩ ዓይኖች ፈጽሞ አያዩም፣ ሰውነቱ አይንቀሳቀስም፣ አንደበቱ ቃል አያወጣም:: እናት አባት ተስፋ ቆረጡ:: የአካባቢውን አፍ፣ የመንደሩን ጉምጉምታ ፈሩ::

ውሎ አድሮ ክፉ ወሬ ከጆሯቸው ደረሰ:: የልጃቸው እንዲህ መሆን ከእርግማን፣ ከሀጢያት ብዛት የመጣ መሆኑ ተነገራቸው:: እነሱም ማስተባበሉን አልፈለጉም:: እሱነህ በሀጢያት የመጣ፣ በእርግማን የተገኘ ፍሬ መሆኑን አመኑ::

### ይሙት! በቃ

የእሱነህ እናት አባት የሀጢያት፣ የእርግማን ፍሬ ነው ያሉትን ልጅ ሊያቅፉት፣ ሊንከባከቡት አልፈለጉም:: ስድስት ወር እንደሞላው በዓይኑ ብርሀን ተስፋ ቆረጡ:: ጡት አስጥለው በአንዲት ጡጦ የጤፍ አጥሚት አስለመዱት::

አሁን ራሱን የማያውቅ፣ ዓይኑ የማያይ፣ ልጅ አያስፈልጋቸውም:: እስትንፋሱ እስካለ በህይወት እንዲኖር ፈቅደውለታል:: ከአንድ ጨለማ ቤት ዘግተውበት ሲውል ተለክታ የምትጣልለት አንዲት ጡጦ በአጥሚት ተሞልታ ትጣልለታለች:: እሷን በደመነፍስ እየማገ ከራሱ ዓለም ይታገላል:: መራቡን፣ መሸናት መቃጠሉን የሚያውቅለት፣ የለም::

ትንሹ እሱነህ ዕድሜው ሁለት ዓመት እስኪሞላ ምግብ የሚባል ቀምሶ፣ አላምጦ አያውቅም:: ያለሰው ትንፋሽ በጨለማ ቤት ያሳለፋቸው ቀናት ልጅነቱን ነጥቀውታል:: ከሰውነት ተራ አውጥተው በጉስቁልና አራቁተውታል:: ትንሹ ልጅ ሰው ባለበት ዓለም ከዓለም ተገልሎ፣ በወላጆቹ ተጠልቶ ፈታኝ የመከራ ቀናትን ገፍቷል::

ይህን ሁሉ ግፍ በቅርብ የምታየው የአምስት ልጆች እናት በእሱነህ ጉስቁልና ልቧ ሲያዝን ኖሯል:: እንዳትወስደው አቅሟ አይችልም:: እንዳትቃወም እሱነህ በወላጆቹና በአካባቢው የእርግማን ፍሬ መሆኑ ታምኖበታል:: እንዲያም ሆኖ ዝም አላለችም:: እውነታውን ይዛ፣ ህጻኑን አዝላ ከሙዳይ በጎ አድራጎት ድርጅት ደረሰች::

### አዲስ ዓለም

ወይዘሮ ሙዳይ የእሱነህን ችግር በአይኗ ካየች ወዲህ ዕንቅልፍ ይሉት አጥታለች:: የትንሹን ልጅ የመኖር ተስፋ ልታስቀጥል፣ የዓይኖቹን ጤንነት ልታረጋግጥ ጥረቷን ይዛለች::

አንድ ማለዳ ሙዳይ ህጻኑን ለአንዲት እናት አስይዛ ወደ ሆስፒታል ጉዞ ጀመረች:: እየነዳች ነው:: ሁሌም በመንገዷ ዓይኖቿ ግራ ቀኝ ያያሉ:: በአጋጣሚ ትራንስፖርት የሚጠብቁ አቅመ - ደካሞች ካገኘች ጠርታ ታሳፍራለች:: የዛን ዕለትም አንድ ሽማግሌ በርቀት ብታይ አጠገባቸው ደርሳ ቆመች:: ሰውየው አመስግነው ከመግባታቸው በፊት አንዲት ወጣት ቀድማቸው የጋቢናውን በር ከፍታ ገባች::

ሙዳይ የልጅቷ ድርጊት ቢያስገረማትም አንዳች አላለችም:: ወዲያው ሁሉንም ይዛ ጉዟዋን ወደፊት ቀጠለች:: ከጋቢናው የተቀመጠችው ሴት ለመናገር አልዘገየችም:: ፊቷን ወደኋላ አዞራ ስለህጻኑ ማብራሪያ ጀመረች:: በቅድሚያ ልጁ እንደሆነ ጠየቀቻት:: መልሱን አስከትሰማ አልቆየችም:: የጤና ባለሙያ መሆኗን ነግራት በህጻኑ ላይ ስለሚታየው ችግር ይበልጥ ቅርበት እንዳላትና በሙያዋ ልትረዳት እንደምትፈልግ ነገረቻት:: ቀልጣፋዋ ወጣት ካሰበችው ደርሳ ስትወርድ ሙሉ ማንነቷን የሚገልጽ የአድራሻ ካርድ ትታላት ነበር::

### ሁሉ ሰበብ

ሙዳይ የዛን ቀን ከሆስፒታሉ ደርሳ ስለህጻኑ ችግር ተረዳች:: ለዓይኑ አለማየት ቀዶ ህክምና ቢኖርም ከሂደቱ በኋላ አይኑ ላያይ፣ እሱም ሊሞት እንደሚችል ተነገራት:: ምግብ ለማስለመድም በህክምናው የተካነ የራሱ ባለሙያ እንደሚያስፈልግ ተብራራላት::

ይህን በሰማች ጊዜ ሙዳይ ጠዋት መኪናዋን ከፍታ የገባችውን ወጣት አስተውሳ ስልኳን አነሳች:: ወጣቷ በሀኪሞቹ የተነገራት አይነት በሙያው የተካነች ሴት ነበረች:: ሙዳይ ህልም የመሰላትን እውነት እያሰበች ነው:: የስልክ ጥሪዋን «ሀሎ»ስትል የተቀበለችው ወጣት ለይሁንታዋ እጅግ ፈጣን ሆነችላት::

### ትንሹ ልጅ በሙዳይ

ዛሬ እሱነህ የአስራ ሁለት ዓመት ልጅ ነው:: ሰውነቱ በእጅጉ አምሮ ተለውጧል:: በህክምናው ብዙ ቢሞከርም ውጤቱ እንደታሰበው አልሰመረም:: ልጁ አሁንም መናገር፣ ማየትና መንቀሳቀስ አይችልም:: በእናት አባቱ ይሁንታ ድርጅቱ ልጁን ከተረከበ ወዲህ ከግቢው ቤተሰቦች ጋር ተቀላቅሏል:: የራሱ ተንከባካቢ ሞግዚት አለው:: ህጻኑ ምግቡን ለይቶ የሚያውቀው በሽታና መአዛው ነው:: አመጋገቡ እንደሌሎች አይደለም:: የሚቀምሰው ሁሉ በተለየ ጥንቃቄና ጥራት ይዘጋጅለታል::

ትንሹ ልጅ ለሬዲዮና ሙዚቃ የተለየ ስሜት አለው:: እነዛ ውብ ዓይኖቹ ዛሬም ለብርሀን አልታደሉም:: የሚወደውን ሰው በጭብጨባ ይቀበላል:: የማይፈልገው ሲኖርም ብስጭት መገለጫው ነው:: የሴት ድምጽ ሲሰማ «እማ..» እያለ ይጣራል፣ ከወንድ ድምጽ ቀጥሎም «አባ...» ማለት ልማዱ ነው:: እንዲህ መሆኑ ብቻ ለሙዳይና አጋሮቿ ታላቅ ተስፋ ነው::

ከዓመታት በፊት ከሙዳይ ጋር የመንገድ አጋጣሚ ያገናኛቸው ወጣት ዛሬ የእሱነህ የግል ባለሙያ ነች:: ምግብ መብላትን፣ ራስ ችሎ መቀመጥን በብዙ ጥረት አስለምዳዋለች:: የግቢው ቤተሰብ እሱነውን በተለየ ፍቅር ያየዋል:: በህክምናው ተስፋ ቢያጣም ስለእሱ መኖር ሁሉም በየዕምነቱ ይጸልይለታል:: እሱነህ ትናንት በወላጆቹ፣ በማህበረሰቡ የተጣለ ጨቅላ፣ ባልተገባ አመለካካት «ይሙት በቃ» ተፈርድቦት ሁለት የስቃይና የጨለማ ዓመታትን የገፋ ምስኪን:: ፍጡር መሆኑ ተዘንግቶ ከአፈር ከትቢያ የተጣለ ህጻን:: ዛሬ ክቡር የሰው ልጅ መሆኑ ቢለይ ማንነቱ ሚዛን ደፍቷል:: ታላቅነቱ ተመስክሮም ንጹህ የሙዳይ ወርቅ ሆኗል::

ኢኮኖሚ

# ስኬት

# ከውትድርና የጀመረው የመቶ አለቃው የስኬት ጉዞ

**ፍሬሕይወት አወቀ**

የትውልድ ቦታቸው በቀድሞው ጎጃም ጠቅላይ ግዛት ይልማ እና ዴንሳ አውራጃ ነው። ገና የአምስት ዓመት ሕጻን ሳሉ አጎታቸውን ተከትለው አዲስ አበባን ተዋውቀዋል። አዲስ አበባን በዚህ ዕድሜያቸው የመተዋወቅ ዕድል የገጠማቸው የዕለቱ እንግዳችን የልጅነት ዕድሜያቸውን በጫወታና በትምህርት ማጣጣም የቻሉት በአዲስ አበባ ቢሆንም፣ ትምህርታቸውን ሳያጠናቅቁ በአፍላ ዕድሜያቸው ነው ወታደር ቤት የገቡት። መስዋዕትነትን ጭምር በሚጠይቀው የውትድርናውን ዓለም ሕይወት «ሀ» ብለው ሲማሩ ሥነ-ሥርዓትን፣ ጨዋነትንና ቁርጠኝነትንም ተምረዋል።

ፍጹም ሥነሥርዓትንና የዓላማ ጽናትን ከተማሩበት ወታደር ቤት የነበራቸውን ቆይታ አጠናቅቀው ሲቪል በመሆን ማኅበረሰቡን በተቀላቀሉ ጊዜ አዲስ የሕይወት መስመር ነው የጠበቃቸው። ከወታደር ቤት ውጭ ያለውን ሕይወትም እንዲሁ ለመኖር የሕይወትን ውጣ ውረድ ከዝቅታው ዝቅ ብለው ተምረዋል። ቀልጣፋ፣ ሥራ ወዳድና ፈጣን በመሆናቸው ሕይወትን ከውትድርና ውጭ ለመምራት ብዙም አልተቸገሩም። ለመኖር መሥራት የግድ እንደሆነ በማመን ሥራ ሳይመርጡና ሳይንቁ በድለላ ሥራ ተሰማርተው በርካታ ዕውቀትና ልምድ መቅሰም ችለዋል።

በድለላ ሥራ ጥቂት የማይባሉ ዕውቀት፣ ልምድና ማኅበራዊ ግንኙነትን ማዳበር የቻሉት የዕለቱ የስኬት እንግዳችን በተለያዩ የንግድ ሥራዎች ተሳትፈው ውጤታማ መሆን የቻሉ ታታሪ፣ ትጉህና ጠንካራ ሠራተኛ ናቸው። «ሥራ ሰውን ያስከብራል» የሚል የጸና አመለካከት ያላቸው በመሆኑ ለሚገጥማቸው መሰናክሎች ሁሉ ፊት ሳይሰጡ ከላይ ታች በማለት ትጋታቸው ፍሬያማ መሆን እንዲችል ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል። ጥረታቸው ተሳክቶም ቱአር ኤን ፈርኒቸር የቤትና የቢሮ ዕቃዎች አምራች ድርጅት እንዲሁም ዘመናዊ ሆቴል መገንባት ችለዋል። ትናንት ከውትድርና ተነስተው በድለላ ሥራ ያካበቱትን ዕውቀት ተጠቅመው በተለያዩ የንግድ ሥራዎች ውስጥ ገብተው በመሥራት ዛሬ ከስኬት ማማ ላይ የደረሱት እንግዳችን መቶ አለቃ ሰለሞን አዳሙ ይባላሉ።

ከገጠሪቷ ኢትዮጵያ ወጥተው አዲስ አበባ ጠቅላይ ሰፈር ወይም ኳስ ሜዳ አካባቢ ያደጉት መቶ አለቃ ሰለሞን፤ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን በቀድሞ ስሙ ወሰንሰገድ በአሁን አጠራሩ የካቲት 23 ትምህርት ቤት ተከታትለው በአዲስ ከተማ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በሚከታተሉበት ወቅት ወታደር ቤት መግባታቸውን ያስታውሳሉ።

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ሳያጠናቅቁ ውትድርናን የተቀላቀሉት መቶ አለቃ፤ በ1973 ዓ.ም በቀድሞው 21ኛ ተራራ ክፍለ ጦር በውትድርና ሙያ ተቀጥረው ታጠቅ ጦር ሰፈር የውትድርና ሥልጠናን በተግባር ተከታትለዋል። ወታደር ሆነው ሀገራቸውን ለማገልገል ወጥቶ ማደርን «ሀ» ብለው የጀመሩት መቶ አለቃ ሰለሞን፤ ከ1974 እስከ 1977 ዓ.ም ድረስ ኤርትራ ዘምተዋል። የሕይወት መስዋዕትነትን በሚጠይቀውና ታላቅ ሙያ በሆነው የውትድርና ሙያም በተለያዩ አካባቢዎች በውጊያ ተሳትፈዋል።

ከውጊያ በመለስም በዕጩ መኮንንነት የተወዳደሩት መቶ አለቃ ሰለሞን፤ "ሐረር ሚሊቴሪ አካዳሚ" ወይም "ሁርሶ" ይባል በነበረው ማሰልጠኛ የዕጩ መኮንንነት ሥልጠና መውሰድ የሚያስችላቸውን ውድድር አልፈው ሠልጥነዋል። በሥልጠናው ወቅት ባሳዩት ተሳትፎና ባስመዘገቡት ከፍተኛ ውጤት በማሰልጠኛ ተቋሙ መምህር ሆነው የመቅረት ዕድል አጋጥሟቸዋል። መቶ አለቃ ሰለሞን፤ የደርግ መንግሥት ወድቆ የኢሕአዴግ መንግሥት ሥልጣኑን እስከተቆጣጠረበት 1983 ዓ.ም ድረስ በጦር ትምህርት ቤቱ በካርታ ንባብ ወይም በቶፖግራፊ መምህርነት አገልግለዋል።

ኢሕአዴግ በትረ ሥልጣኑን ሲቆናጠጥ ከጦር ትምህርት ቤቱ በተሰናበቱ ማግስት የሕይወት መስመራቸውን ከውትድርና ወደ ድለላ ሥራ የቀየሩት መቶ አለቃ ሰለሞን፤ ቀልጣፋና ፈጣን በመሆናቸው ሕይወትን ከጦር ቤት ውጭ ለመምራት ያስችለኛል ያሏቸውን በርካታ ሥራዎች ሠርተዋል። በቅድሚያ የድለላ ሥራን ሲቀላቀሉ መርካቶ ውስጥ በሸቀጣ ሸቀጥ ንግድ የተሠማሩ ዘመዶቻቸው ጥሩ መጠጊያ ሆነዋቸው እንደነበር ያስታውሳሉ። ሸቀጣ ሸቀጥን በመደለል የንግድ ሥራን አቀላጥፈው ሠሩ። ወቅቱ ኤርትራ ከኢትዮጵያ የተገነጠለች ቢሆንም፣ ግጭትና ጦርነት አልነበረምና ኤርትራውያኑ ኢትዮጵያ ውስጥ እንደፈለጉ ተንቀሳቅሰው ይነግዱ ነበር፤ ይህም እሳቸው ለጀመሩት የድለላ ሥራ ጥሩ አጋጣሚ ፈጠረላቸው።



ፎቶ፡- ፀሐይ ንጉሴ

**መቶ አለቃ ሰለሞን አዳሙ**

በወቅቱ ኤርትራውያኖች የተለያዩ ሸቀጣ ሸቀጦችን በደሴ በር በኮንትሮባንድ ያስገቡ እንደነበር የሚያስታውሱት መቶ አለቃ ሰለሞን፣ ዕቃዎቹን የሚሸጥላቸው ሰው በሚፈልጉ ጊዜ እርሳቸው አቤት ብለው ከኤርትራውያኖቹ ቀርበዋል። ኤርትራ በነበራቸው ቆይታም ቋንቋቸውንና ባሕል አመላቸውን ማወቅ የቻሉት መቶ አለቃ ሰለሞን፤ እርሱን ማወቃቸው ከኤርትራውያኖች ጋር በቀላሉ ለመግባባትና ለመሥራት ምቹ ሁኔታን ፈጠረላቸው። እናም የድለላ ሥራው አልጋ በአልጋ ሆነላቸው። በወቅቱ ኤርትራውያኖቹ በደሴ በር የሚያስገቡትን የተለያዩ ሸቀጦች መቶ አለቃ ሰለሞን ተረክበው መርካቶ በመሸጥ የንግድ ሥራቸውን ማቀላጠፍ ቻሉ።

የሚያመጡትን ዕቃ ተረክበው መርካቶ ውስጥ በመሸጥ ከፍተኛ ገንዘብ ያገኙ እንደነበር ያስታወሱት መቶ አለቃ ሰለሞን፤ የንግድ ሥራን በዚሁ መንገድ እንደተለማመዱትና ከኤርትራውያኖቹ ጋርም የቤተሰብ ያህል ተቀራርበው በመሥራት ሦስት ሺ ብር ማጠራቀም ቻሉ። ሦስት ሺ ብር በወቅቱ ትልቅ ገንዘብ እንደሆነ ያነሱት መቶ አለቃ ሰለሞን፤ የንግድ ሥራቸውን ለማሳደግ የሲጋራ ጅምላ ንግድ ፈቃድ በማውጣት ወደ ሲጋራ ንግድ ተዘዋውረዋል።

«ሥራ አልመርጥም አጋጣሚው የፈጠረልኝን እና የተመረጠልኝን ሥራ ሁሉ እሠራለሁ» የሚሉት መቶ አለቃ ሰለሞን፤ የሲጋራ ንግዱ ብዙም አላስደሰት አላቸውና ወደ እህል ንግድ ፊታቸውን አዞሩ። ወደ እህል ንግድ ለመግባት ያሰቡት ጤፍ የሚመረትባቸውን የተወሰኑ አካባቢዎች ማወቃቸውን መሠረት በማድረግ እንደሆነ ያስታውሳሉ። በወቅቱ ከሲጋራ ንግድ ያተረፉትን አሥር ሺ ብር ይዘው ሀዲድ ገበያ አካባቢ በአራት መቶ ብር ቆርቆሮ ቤት በመከራየት የእህል ንግዱን ጀመሩ።

የእህል ንግድ ከፍተኛ ገንዘብ የሚፈልግና ወቅትን ተከትሎ የሚሠራ እንደሆነ የሚገልጹት መቶ አለቃ ሰለሞን፤ በቆርቆሮ ቤት ውስጥ በተከማቸው ኩንታል ላይ እየተኙ ዘበኛም ነጋዴም ሆነው አሳልፈዋል። ትንሽ ጊዜ እንደነገዱም አዋጭ አልሆን ሲላቸው ሌሎቹን ንግዶች እንደተውት ሁሉ ከእህል ንግድም ራሳቸውን አሰናበቱ።

ታታሪ፣ ብርቱና ሥራ ወዳድ የሆኑት መቶ አለቃ ሰለሞን፤ በሌላ የንግድ ሥራ ብቅ በማለት መርካቶ ዱባይ ተራም ገብተው ሸንሸን ሱቅ በመከራየት በቡቲክ ንግድ ላይ ሠርተዋል። በወቅቱ ከግብጽና ከሌሎች ሀገራት ጭምር በሻንጣ የሚመጡ የተለያዩ አልባሳት፣ ዊግና ሌሎች ቁሳቁስን ተቀብለው ነግደዋል። ጎን ለጎንም ወደ ድሬዳዋ በማቅናት የጉምሩክ ዕቃዎችን በመጫረት የንግድ ሥራቸውን ማሳለጥ ቀጠሉ። በዚህ ጊዜ ከኮንትሮባድ ጋር በተያያዘ ንብረታቸው በመንግሥት ተወርሶ የንግድ ሥራቸው ወደ ኪሳራ ገጥሞት እንደነበርም አልሸሸጉም።

ይሁንና ከደረሰባቸው ኪሳራ እንዴት መውጣት እንደሚችሉ ያወጡና ያወርዱ እንደነበር ያነሱት መቶ አለቃ ሰለሞን፤ የደረሰባቸውን ችግር የሰሙ ወዳጅ ዘመዶቻቸው በሃሳብም በገንዘብም ያግዟቸው እንደነበር ያስታውሳሉ። በወቅቱ ከወዳጆቻቸው መካከል አንደኛው ለሥራ ማስጀመሪያ በሚል አፈላልጎ 20 ሺ ብር እንደሰጣቸውም ያስታውሳሉ።

መቶ አለቃ ሰለሞንም፤ ይህን ብር በመያዝ ወደ ኪሳራ ያመራውን ንግድ ለማነቃቃት ወደ ድሬዳዋ ሲያቀኑ በጉዟቸው የወታደር ቤት ጓደኛቸውን ያገኛሉ። ይህ አጋጣሚ ዛሬ እያስተዳደሩት ያለውን ቱአር ኤን ፈርኒቸር የቤትና የቢሮ ዕቃዎች ማምረቻ ድርጅትን እንዲያቋቁሙ መሠረት ጥሎላቸው አልፏል። በወቅቱ ወታደር ቤት የሚያውቁት የልብ ወዳጃቸው የጣውላ ሥራ ይሠራ እንደነበር ሲያጫውታቸው ሥራውን በጋራ ለመሥራት የወሰኑት በዛው ቅጽበት ነበር።

የጣውላ ሥራውን በጋራ ለመሥራት በወሰኑ ማግስትም ጣውላው በሚገኝባቸው የተለያዩ አካባቢዎች በመንቀሳቀስ መግዛትና መሸጥ ቀጠሉ። ሁለት ሆነው በጀመሩት የጣውላ ንግድ ሥራ መንገድ ላይ ሌላ የወታደር ቤት ወዳጃቸውን አግኝተው ሦስት ሆነው ሲሠሩ ቆይተዋል።

ሥራው አዋጭ ቢሆንም የኮንትሮባንድ ባሕሪ ያለውና አስቸጋሪ ሥራ መሆኑን በመረዳት ጣውላ ከመሸጥ ይልቅ የጣውላ ምርቶችን መሸጥ የተሻለ እንደሆነ በማመን ጓደኛሞቹ ጣውላ ከመሸጥ ጣውላ ወደ መግዛት ተሸጋገሩ። በዚህ ጊዜ ጣውላ ከሸጡላቸው ደንበኞች ቀሪ ሂሳብ ለመቀበል ወደ መገናኛ ያቀኑት መቶ አለቃ ሰለሞን፤ በዚህም የገበያውን ፍላጎትና አዋጭነቱን መረዳት እንደቻሉ ያስታውሳሉ። ይህን የተረዱት መቶ አለቃ ሰለሞን፤ ሳይውሉ ሳያድሩ መሸጫ ቦታውን አፈላልገው በመከራየት ሞራሌ፣ አንጎላሬ፣ ጣውላ፣ መዝጊያና ክፈፍ የተባሉ ምርቶችን መሸጥ ጀመሩ። በወቅቱ ጓደኛቸውም በግሉ ራሱን ችሎ መነገድ ጀምሮ እንደነበር አጫውተውናል።

ጣውላ ከመሸጥ ወጥተው የጣውላ ምርቶችን በመሸጥ ሦስት አስርት ዓመታትን ያስቆጠሩት መቶ አለቃ ሰለሞን፤ በአሁኑ ወቅት ሁለት ቦታዎች ላይ የተለያዩ የቤትና የቢሮ ዕቃዎች ማምረቻ ፋብሪካዎችን ማቋቋም ችለዋል፤ አንደኛውና የመጀመሪያው ማምረቻ አስኮ፣ ሁለተኛው ወሰን ግሮሰሪ መንገድ አካባቢ፣ ሦስተኛውና መጠነኛ ማምረቻ ያለው ነገር ግን በዋናነት መሸጫ የሆነው ድርጅት ደግሞ መገናኛ ላይ ይገኛል።

ቱአር ኤን ፈርኒቸር የቤትና የቢሮ እቃዎች ማምረቻ ድርጅት በዋናነት የሚያመርተው የቤት ውስጥና የኮንስትራክሽን ፈርኒቸሮችን እንደሆነ የጠቀሱት መቶ አለቃ ሰለሞን፤ ኮንስትራክሽን ፈርኒቸር የሚባሉት እንደ ኪችን ካቢኔት፣ ካፕቦርዶች፣ የግድግዳ ቁምሳጥኖች፣ የደረጃ መወጣጫዎች፣ ፓርኬዎች፣ ምንጣፎችና አጠቃላይ ከግንባታ ጋር አብረው ሊሄዱ የሚችሉ ምርቶችን ያመርታል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ለግንባታ አጋር የሚሆኑ ጣውላዎች፣ ሞራሌና ሌሎችንም አዘጋጅተው ለገበያ ያቀርባሉ። የቤት ውስጥ ፈርኒቸር የሚባሉትን እንደ ሶፋ፣ የምግብ ጠረጴዛና ሌሎችንም ያመርታሉ። የድርጅታቸው ምርቶች በጥራትና በጥንካሬያቸው ተፈላጊ እንደሆኑ የሚናገሩት መቶ አለቃ ሰለሞን፤ ለምርቶቹ ገበያቸውም ቤት የሚሠሩ ግለሰቦችና የተለያዩ ድርጅቶች እንደሆኑ ነው ያስረዱት።

ከውትድርና ውጭ ያለውን ሕይወታቸውን በድለላ ሥራ «ሀ» ብለው የጀመሩት መቶ አለቃ ሰለሞን፤ አንድ ብለው የጀመሩት ሥራ ሁለት፣ ሦስት እያለ ዛሬ ከደረሰበት ደረጃ መድረሱ ለሥራ ባላቸው ትጋትና ቁርጠኝነት እንደሆነ በማንሳት ሰው ከለፋና ከጣረ ከከፍታው ከፍ ማለት እንደሚችል ይናገራሉ። መቶ አለቃ ሰለሞን፤ ዛሬ ከታወቁበት ቱአር ኤን ፈርኒቸር የቤትና የቢሮ ዕቃዎች ማምረቻ ድርጅት በተጨማሪ ዘመናዊ ሆቴል እየገነቡ እንደሆነም ይናገራሉ።

የሆቴል ግንባታውን እያከናወኑ የሚገኙት ከአዲስ አበባ 32 ነጥብ ስድስት ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ሰንዳፋ በኬ ከተማ ሲሆን፤ ሆቴሉ ደረጃውን የጠበቀና ዘመናዊ እንደሆነ ተናግረዋል። 41 ክፍሎች፣ አራት የስብሰባ አዳራሾች እንዲሁም ለአካል ጉዳተኞች ምቹ የሆኑ አራት ክፍሎች ያሉት ነው። አራት ሺ ካሬ ሜትር ስፋት ባለው ቦታ ላይ ያረፈ ሲሆን፣ በአሁኑ ወቅት ግንባታው እየተጠናቀቀ ይገኛል።

የሥራ ዕድል በመፍጠር ረገድም የድርሻቸውን እየተወጡ ያሉት መቶ አለቃ ሰለሞን፤ በፈርኒቸር ብቻ አዲስ አበባ ላይ 120 ለሚደርሱ ዜጎች የሥራ ዕድል ፈጥረዋል፤ አስኮ በሚገኘው ድርጅታቸውና በሆቴል ግንባታው የተሠማሩ ሠራተኞችን ጨምሮ 110 ለሚደርሱ ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር የቻሉ ሲሆን፣ በድምሩ 330 ለሚደርሱ ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር ችለዋል።

መቶ አለቃ ሰለሞን ማኅበራዊ ኃላፊነትን በመወጣት ረገድ በርካታ በጎ ተግባራትን የሚያከናውኑ ቢሆንም በዝርዝር ከመግለጽ ተቆጥበዋል። ይሁንና ወታደር ቤት እያሉ የሚያውቋቸው በተለይም ጉዳት የደረሰባቸው ጓደኞቻቸው ከመቶ አለቃ ሰለሞን በርካታ ድጋፎች እያገኙ እንደሆነና ሌሎች ለተቸገሩ ሰዎችም በተለያየ መንገድ ድጋፍ ሲያደርጉ እንደነበርና አሁንም እያደረጉ እንደሆነ ከጓደኞቻቸው መረዳት ችለናል። ከዚህ በተጨማሪም ግብር በአግባቡ ከመክፈል ባለፈ ሀገራዊ ለሆኑ ማንኛውም ጥሪዎች ፈጣን ምላሽ እንደሚሰጡም አጫውተውናል።

ከውትድርና ተነስተው በድለላና በተለያዩ የንግድ ሥራዎች ያለፉት መቶ አለቃ ሰለሞን፤ ወታደር ሆነው የገነቡት ማንነት ዛሬ ለደረሱበት ደረጃ ወሳኝ መሠረት የጣለ መሆኑን በመጥቀስ፣ ማንኛውም ዜጋ ወታደር ሆኖ ማለፍ እንዳለበት ይመክራሉ፤ «መንግሥት ብሔራዊ ውትድርናን መጀመር አለበት» ሲሉም ነው የሚያስገነዝቡት። እያንዳንዱ ዜጋ ወታደር ሆኖ መውጣት ከቻለ ጨዋነት፣ አገር ወዳድነትና ሕይወትን የሚለውጡ በርካታ ቁምነገሮችን ከውትድርና ሞያ መማር እንደሚችል በመግለጽ ሁሉም ሰው የወታደር ስብዕና ቢኖረው መልካም ነው ይላሉ።

# ስፖርት



# በበጀት እጥረት የተቀዛቀዙ የሀገር ውስጥ ውድድሮች

ብርሃን ፈይሳ

የትኛውም ስፖርታዊ ውድድር ተመጋጋቢ በመሆኑ ለቀጣይ ውድድር የሚኖረው ጠቀሜታ የጎላ ነው። ሥልጠናን ለመገምገም ሆነ ወቅታዊ አቋምን ለማወቅ ምዘናዎችን በየደረጃው ማከናወን ለአንድ ስፖርት አስፈላጊ ነው። ይሁንና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በኢትዮጵያ ይህ ሁኔታ መቀዛቀዝ እየታየበት ነው። የዓለም አቀፍ ውድድሮች ተሳትፎን በሚመለከትም ፌዴሬሽኖች ድጋፍ በማጣት ሃገራቸውን መወከል እየተሳናቸው በተደጋጋሚ ቅሬታ የሚያቀርቡበት ሁኔታ እየተበራከተ ነው።

ይህንን ተከትሎም በኢፌዴሪ ባሕልና ስፖርት ሚኒስትር የስፖርት ልማት መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ ተስፋዬ በቀለ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ በሰጡት ማብራሪያ፣ ዓለም አቀፍ የውድድር ተሳትፎን በሚመለከትም ድጋፍ የሚደረግላቸው ስፖርቶች በዋናነት በአህጉርም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ውጤታማ ለሆኑ ስፖርቶች ብቻ መሆኑን ጠቁመዋል። ቡድን መሪው እንደሚያብራሩት የስፖርት ማኅበራቱ ድጋፍ እንዲደረግላቸው ጥያቄ በሚያቀርቡበት ጊዜ ይሁንታ ሊያገኙ የሚችሉት፤ ውጤታማነታቸው፣ ለሃገር ገጽታ ግንባታ የሚያበረክቱት አስተዋፅዖ እንዲሁም የዲፕሎማሲ ግንኙነትን ማስፋት መቻላቸው ተመዝኖ ነው።

በዚህ መንገድ ካልሆነ ግን በሃገሪቷ ላሉት ከ31 በላይ የስፖርት ማኅበራት፤ ለውድድር ከሚመደበው 22 ሚሊዮን ብር ላይ መደገፍ አዳጋች ነው። በመሆኑም ማኅበራቱን በመስፈርቱ መሠረት በመለየት የገንዘብ ድጋፍ አሊያም የትብብር ደብዳቤ በማዘጋጀት ተገቢውን ድጋፍ ለማድረግ ጥረት ይደረጋል። ያም ሆኖ እንደ እግር ኳስ ያሉ የስፖርት ማኅበራት በሚሰጣቸው ድጋፍ መሠረት ውጤታማ ሲሆኑ አይስተዋልም። በመሆኑም ከዚህ በኋላ ድጋፍ ለማድረግም ሆነ ድጋፉን ለማስቀረት መነሻ የሚሆን ጥናት በመካሄድ ላይ ይገኛል። ይኸውም ውጤት ላለመመዝገቡ ትክክለኛው ምክንያት ምን ሊሆን ይችላል የሚለውን ለመለየት ሚኒስትር መሥሪያ ቤቱ ባለሙያዎችን በማሰባሰብ በሚያካሂደው ጥናት ነው።



አቶ ተስፋዬ በቀለ፣

ከገንዘብ ጋር በተያያዘ ያለውን ችግር ለመቅረፍም አማራጭ መፈለግ አስፈላጊ በመሆኑ ሚኒስትሩ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን በማከናወን ላይ ይገኛል። በዚህም የተለያዩ ሃገራት ኤምባሲዎችን ድጋፍ እንዲያደርጉለት በማነጋገር በመረጡት ሁኔታ ድጋፍ ማድረግ የሚያስችላቸው የምክክር መድረክ ይዘጋጃል። ይህም ከሌሎች ሃገራት ልምዶች በመነሳት መሆኑንም ሥራ አስፈጻሚው አመላክተዋል። የስፖርት ማኅበራቱም ይህንን በመመልከት ተመሳሳይ እርምጃ መውሰድ እንዲችሉ መንገድ ከፋች መፍትሔ ነው ተብሎ ታምኖበታል። ከዚህ ባሻገር በአንዳንድ የስፖርት ማኅበራት የሚታዩና ለሌሎችም ተምሳሌት መሆን ከሚችሉ የማኅበራት ሥራ አስፈጻሚዎች ልምድ መውሰድ አስፈላጊ ነው።

ሃገር አቀፍ ውድድሮችን በሚመለከትም በተያዘው ዓመት የተሠራው ስኬታማ አለመሆኑን ሥራ አስፈጻሚው አልሸሸጉም። በሚኒስትሩ አዘጋጅነት የሚደረጉ ሃገር አቀፍ ውድድሮች ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ተቋርጠዋል። ለዚህም ምክንያት የሆነውም የሃገሪቷ ወቅታዊ የፀጥታ ሁኔታ ሲሆን፤ ለሰላም መሣሪያ የሆነው ስፖርት በተቃራኒው የጠብ መሣሪያ ሲሆን የሚስተዋልበት አጋጣሚ ስጋት ሆናል። ነገር ግን በመጪው ዓመት የመላ ኢትዮጵያ ጨዋታዎችን ለማስጀመር ዕቅድ ተይዟል፤ በዚህም ከስፖርታዊ ውድድርነት ባለፈ የዲፕሎማሲ መሣሪያ እንዲሆንም ይሠራል ተብሏል። ውድድሩ ከቀድሞ በተለየ መልክ እንዲካሄድም የተለያዩ ዘዴዎች ተግባራዊ ይሆናሉ። በተጨማሪም የተማሪዎች ውድድርን ከትምህርት ሚኒስትር ጋር በመሆን እንዲሁም የሴቶችና የአርሶ አደር ውድድሮችንም ለማካሄድ ታቅዶ እየተሠራ ነው።

በሌላ በኩል የስፖርት ማኅበራትም ውድድሮችን እንደቀድሞ እያዘጋጁ አለመሆኑ ይስተዋላል። አቅም ያላቸው ፌዴሬሽኖች በበኩላቸው ውድድር እያዘጋጁ ሲሆን፤ አቅሙ የሌላቸው ግን ማካሄድ አልቻሉም። ለዚህም ፌዴሬሽኖች በገቢ ራሳቸውን ለመቻል የሚያደርጉት እንቅስቃሴ እጅግ ዝቅተኛ በመሆኑ እንደሆነ ሥራ አስፈጻሚው ይናገራሉ። ሚኒስትሩ የሚያደርግላቸውን የበጀት ድጋፍ አስፈላጊ በሆኑ ነገሮች ላይ ከማዋል ይልቅ እያባከኑ መሆኑ ስለደረሰበትም ኦዲት መደረግ እንደሚገባቸው ተወስኗል። ከዚህ ጋር በተያያዘ ፌዴሬሽኖች ሕጋዊ እውቅና እና ፈቃድ በየጊዜው ማግኘት እንዳለባቸው ቢወሰንም አብዛኛዎቹ ጋር የሚስተዋለው ሽሽት ነው። ይህ ሁሉ ሲሆን ፈቃደኛ ያልነበሩት እነዚህ ፌዴሬሽኖች ዓለም አቀፍ ውድድሮች ሲኖሩባቸው ደግሞ ድጋፍ ፍለጋ ወደ ሚኒስትር መሥሪያ ቤቱ ያቀናሉ።

ሚኒስትር መሥሪያ ቤቱ በቅርቡ ተግባራዊ ባደረገው መዋቅር መሠረት ፌዴሬሽኖች ራሳቸውን እንዲችሉ፣ የማይችሉ ደግሞ በተዘጋጀው አማራጭ እንዲንቀሳቀሱ ተደርጓል። ይኸው ከአደረጃጀት ጋር ተያይዞ የመጣው አለመረጋጋትም በዓመቱ ውድድሮች አስፈላጊ በሆነ መልክ እንዳይካሄዱ ምክንያት ሆኗል። ተከታታይና ተመጋጋቢ የሆኑ ውድድሮችን ማካሄድ አለመቻል በዓለም አቀፍ ደረጃ ሃገርን ውጤታማ እንዳትሆን ያደርጋል። ይኸው የበጀት እጥረት እና የአመለካከት ችግርም በተፈለገው መልክ ለመራመድ አዳጋች እንዳደረገውም አቶ ተስፋዬ አስረድተዋል።


ሕብረት ባንክ
Hibret Bank

**ለጂዲ ኢንተርናሽናል ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር ፣ዳዊት ብርሀኑ፣ሳምራዊት ንጉሴ ቤዛወርቅ በየነ፣ዮሴፍ አየለ፣ሽታዬ መላ፣ ገረመው ነጋሽ፣ አንንች መሰለ፣ሜሮን ፋንታሁን፣አዲስዓለም ልሳነወርቅ እና ዳንኤል አዲስዓለም በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሰረት የተሰጠ ማስጠንቀቂያ**

ጂዲኢንተርናሽናልትሬዲንግኃ/የተ/የግልማህበርየተባለውድርጅትከሕብረትባንክአ.ማ.የተበደረውን ብድር ወቅቱን ጠብቆ መክፈል ባለመቻሉ የተዘጋጀውን ማስጠንቀቂያ ለተበዳሪው፣ለንብረት አስያዦች እና ለአንድነትና ነጠላ ዋሶች በአካል አግኝተን ለመስጠት ጥረት ብናደርግም ለመስጠት አልቻልንም በመሆኑምይህማስጠንቀቂያበጋዜጣታትሞከወጣበትቀንጀምሮባሉትሰላሳ/30/ቀናትውስጥድርጅቱ ያለበትን እዳ በጠቅላላው እንዲከፍል እያሳሰብን፤ የማይከፍል ከሆነ ግን በመያዣነት የተመዘገቡትን ንብረቶች በሐራጅ በመሸጥ ገንዘቡን ለብድሩ መክፈያ ለማዋል ባንኩ የሚገደድ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**ሕብረት ባንክ አ.ማ.**

## ማስታወቂያ

“አናሲሞስ የበጎ አድራጎት ድርጅት” “የተባለ” ቦርድ መር ድርጅት “ ሆኖ ለመመዝገብ ለሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን የምዝገባ ጥያቄ አቅርቧል ተቃዋሚ ካለ እስከ ግንቦት 04 ቀን 2015 ዓ.ም. በኢፌዴሪ ለሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን ህብረት ኢንሹራንስ ህንፃ 4ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 407 ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት ይቅረብ፡፡

**የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን**

## ማስታወቂያ

“ሆፕ ኮምፕረሄንሲቭ ሪሊፍ ቻሪቲ ኦርጋናይዜሽን /ሆኮሪቻኦ/ “የተባለ አገር በቀል ድርጅት ሆኖ ለመመዝገብ ለሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን የምዝገባ ጥያቄ አቅርቧል፡ ተቃዋሚ ካለ እስከ ግንቦት 5 ቀን 2015 ዓ.ም. በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ለሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን ህብረት ኢሹራንስ ህንፃ 4ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 407 ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት ይቅረብ፡፡

**የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን**

## አዲስ አበባ አስተዳደር

በአመልካች ወሮ ሀረግነሽ መሀሪ እና በተጠሪዎች እነ ወ/ሮ አልማዝ መሰለ (3ሰዎች) መካከል ስላለው የውል ክርክር ጉዳይ አቶ ሀዲስ ውብነህ ለ09/09/2015 ዓ.ም ለሆነው ቀጠሮ ፌ/ጠ/ፍ/ቤት 2ኛ ሰበር ችሎት ቢሮ ቁጥር 409 ከጠዋቱ 4፡30 ሰዓት እንዲቀርቡ ፍርድ ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት**

በአመልካች ወ/ሮ አፀደ አሊ እና በተጠሪ አቶ ኪዳኔ ገ/ህይወት መካከል ስላለው የፍታብሄር ክርክር ጉዳይ ተጠሪ አቶ ኪዳኔ ገ/ህይወት ለ16/09/15 ዓ.ም ለሆነው ቀጠሮ ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት አራዳ ምድብ 1ኛ ቤተሰብ ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**

የባለንብረት ስም ከድጃ መሀመድ ሀሰን የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-A36515 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር JAAKP34H4G7P18665. ሞዴል NPR6SN የሞተር ቁጥር 4HG1-470285. የሊብሬ ቁጥር 449743 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ 20/8/2015 አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳውን ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የአዲስ ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

በከሳሽ/አመልካች/በፍ/ባለመብት ኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና በተከሳሾች/ተጠሪዎች/በፍ/ባለዕዳዎች 1ኛ እነ አዳም ጎሹ ታዬ 2ኛ ራሄል ገ/መስቀል 3ኛ ገ/ክርስቶስ ገ/ፃዲቅ ይህደጎ መካከል ስላለው የፍትሐብሄር ክርክር ጉዳይ ፍ/ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ ተከሳሾች በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ 1ኛ ባ/ኢ. ችሎት እየታየ መሆኑን በዚህ ጋዜጣ ማስታወቂያ ጥሪ አውቀው መልሱን በጽሑፍ በ07/09/2015 ዓ.ም. በ4፡00 ሰዓት በሬጅስትራር በኩል እንዲያቀርቡ እና ክስ ለመስማት ለ08/09/2015 ዓ.ም. በ4፡30 ሰዓት ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ ችሎት**

በአመልካች ኮምቦልቻ ጨርቃ ጨርቅ አ/ማ እና በተጠሪ ልጉዲ እርሻ ኃ/የተ/የግ/ማህበር መካከል ስላለው ፍ/ብሔር ክርክር ጉዳይ ፍ/ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ ተጠሪ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ቂርቆስ ምድብ 1ኛ ፍ/ር ችሎት እየታየ መሆኑን በዚህ ጋዜጣ ማስታወቂያ አውቀው መልስዎን በጽሁፍ ለ11/09/2015 ዓ.ም. በ4፡00 ሰዓት ይዘው እንዲያቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**